# ፍኖተ እግዚአብሔር

*ተጽሕፈ እም አሐዱ ሊቅ ኢትዮጵያዊ ኀሩይ ወመፈክራዊ*



*ጌታው አለቃ ኅሩይ*

አዘጋጅና አቅራቢ መምህር ልዑለ ቃል አካሉ

አሳታሚ ቅዱስ ያሬድ የጥናትና ተራድኦ ማዕከል

2001 ዓ.ም

2009 U.S.A.

www.kidusyared.org



*ስመ ጥሩው ሊቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ፤ ርዕሰ ሊቃውንት መምህረ መምህራን ሊቀ ሊቃውንት ጌታው አለቃ ኀሩይ አራቀው ተራቀው ትምህርተ ሃይማኖት ያስተማሩበት ምዕላደ ሃይማኖት ነው።*

*ምስጋና*

1. *የቀደሙትን አባቶቻችንን ሥራ ለውሉድ እንድናቀርብ ያነሣሣንን አምላክ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።*

2. *ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የኦሪገን ጳጳስ ጹሑፉን በማረም ፊደሉን በማስተካከል ኢይዞአችሁ በርቱ በማለት ስለሰጡን አባታዊ ድጋፍ ብፁዕነታቸውን ከልብ አመሰግናለሁ።*

3. *ወጣት ሰሎሞን አምባው ይህን ጹሑፍ ታይፕ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላበረከተ በረከተ አበው አይለየው እላለሁ።*

4. *በዚህ የአበውን ጥበብ እና የድካም ፍሬ ለትውልድ በማስተዋወቁ  ሥራ ላይ ለሥራው አብራ በመሰለፍ በማበረታታት ጽሑፉን ታይፕ በማድረግ በመልቀም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተችውን ለዚህ አገልግሎት የቅርብ መሣሪያ የሆነችውን ውድ ባለቤቴን ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አምባውን አመሰግናለሁ።*

5. *የጥናት ማዕከሉን በማገዝ ላይ ያሉትን እና ይህን የማዕከሉን የመጀመሪያ ፍሬ የሆነ መጽሐፍ እንዲታተም ተሳትፎ ያደረጉትን የቅዱስ ያሬድ የጥናትና ተራድኦ ማዕከል አባላት የአባቶቻችን በረከት አይለያችሁ እላለሁ።*

አዘጋጅ መምህር ልዑለ ቃል አካሉ

አሳታሚ ቅዱስ ያሬድ የጥናትና ተራድኦ ማዕከል

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ©2001ዓ.ም

*Editor Leulekal Akalu Alemu*

*Publisher Kidus Yared Research and Aid Foundation*

*Address*

*Kidus Yared Research and Aid foundation*

*P. O. Box 505*

*Stone Mountain, GA 30086*

***Copyright © 2009 by Saint Yared and Aid Research***

## መከስተ አርዕስት


*፩. ቅዱስ ያሬድ የጥናትና ተራድኦ ማዕከል ዓላማ እና መግለጫ*

*፪. መቅድመ ቃል "ፍኖተ እግዚአብሔር" በሚል ርዕስ አለቃ ኀሩይ ያዘጋጁት የዚህ ጽሑፍ ይዞታና አቀራረብ (ከአዘጋጁ)*

*፫. ጠቅላላ መግቢያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ትናንት እና ዛሬ*

*፬. የታላቁ ሊቅ ጌታ አለቃ ኅሩይ ሕያው ታሪክ*

*፭. መቅድም*

*፮. መግቢያ*

*፯. አንቀጽ አንድ*

*፰. አንቀጽ ሁለት*

*አንቀጽ ሁለት ክፍል ፩*

*አንቀጽ ሁለት ክፍል ፪*

*፱. አንቀጽ ሦስት*

*፲. አንቀጽ አራት*

*፲፩. አንቀጽ አምስት*

*፲፪. አንቀጽ ስድስት*

*፲፫. አንቀጽ ሰባት*

*፲፬. አንቀጽ ስምንት*

፲፭. አንቀጽ ዘጠኝ

፲፮. አንቀጽ አሥር

፲፯. አንቀጽ አሥራ አንድ

፲፰. አንቀጽ አሥራ ሁለት

፲፱. አንቀጽ አሥራ ሦስት

፳. አንቀጽ አሥራ አራት

አንቀጽ አሥራ አራት ክፍል ፩

አንቀጽ አሥራ አራት ክፍል ፪

፳፩. አንቀጽ አሥራ አምስት ምዕዳንና አኰቴት

፳፪. የቃላት መፍቻ

፳፫. ዋቢ መጻሕፍት

*****************************************************

## *መቅድመ ቃል*

*ይህ በታላቁ ሊቅ በአለቃ ኀሩይ የተዘጋጀው "ፍኖተ እግዚአብሔር" የተሰኘው ትምህርተ ሃይማኖት አሥራ አምስት አናቅጽ (መከፈያ ክፍሎች) ያሉት፤ የራሱ የሆነ መግቢያ እና መቅድም ኖሮት እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደ አንቀጹ ስፋትና መጠን አልፎ አልፎ አንቀጾችን የሚከፍሉ ክፍላት(ክፍሎች) ያሉት ሆኖ የተዘጋጀ በጣም ጠቃሚ የሆነ መድበል ወይም ምዕላድ ነው። መጽሐፉ በገጽ ብዙም ባይሆን ከፍተኛ የሆነ ትምህርተ መለኮት በከፍተኛ ደረጃ የተገለጸበት፤ የቀደሙትን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አስተምህሮ እና የሃይማኖት ርቃቄ የሚያሳይ ነው። ሊቁ አለቃ ኀሩይ እንዳሉት “በቅጥነተ ሕሊና” የሚታየውን ትምህርተ ሥላሴ የሚያራቅቅ፣ ከመናፍቃን ኑፋቄ የሚጠብቅ ትምህርት ይዟል። መጽሐፉ ከቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ እና ከልዩ ልዩ መጻሕፍተ ሊቃውንት መረጃዎችን በመጥቀስ በመረጃ የታገዘ ብስል መጽሐፍ ነው።*

*የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ምሥጢረ ሥላሴን መግለጽ ነው። ስለ “ስመ አካል”፣ ስለ “ስመ ኩነት”፣ ስለ “ስመ ግብር” በግልጽ ያስተምራል። ይህ መጽሐፍ "ወላዲ መለኮት" "ተወላዲ መለኮት" "ሠራጺ መለኮት" ማለት እንደማይገባ ይናገራል። (አንቀጽ አንድ) በአንድ መለኮት ሦስት ኩነት እንዳለ ይናገራል። የመለኮት አንድነት አካላትን እንደማይጠቀልል የአካላትም ሦስትነት መለኮትን እንደማይከፍል ያስረዳል። ይህ መጽሐፍ ሥላሴ በመለኮት አንድ የሚሆኑበትን ምሥጢር ያሳያል። ከዚህም በተጨማሪ ሥላሴ በግብር በአካል በባሕርይ የሚጠሩበትን ስም ለይቶ ያሳያል። ስለ ስመ ተረክቦ እግዚአብሔርም ማለት መለኮት ከማለት ጋር አንድ ሲሆን ልዩነት እንዳለው ይናገራል። እንዲሁም የሥላሴ መንግሥት በአካል ከሦስት የማይከፈል አንድ መሆኑን ይናገራል። "አብ" ማለት እና "ወላዲ"*

*ማለት "ወልድ" ማለት እና "ተወላዲ" ማለት "መንፈስ ቅዱስ" ማለትና "ሠራጺ" ማለት ልዩ ልዩ እንደሆነ ይናገራል። ወልድ ከሦስቱ አካላት አንዱ ሲሆን በተለየ አካሉ ሰው የሆነበትን ምሥጢር ያሳያል። መለኮት የሚለውን ቃል በልዩ ልዩ ሥልት ተርጉሞ ያሳያል። "ኃይል" "ክሂል" "ሥልጣንም" በአካል ከሦስት የማይከፈሉ መሆናቸውን ያስተምራል። በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ለትምህርተ መለኮት ደቀ መዛሙርት እና በሃይማኖት ለማደግ በትምህርተ ሥላሴ ለመራቀቅ በሃይማኖት ትምህርት ለመላቅ ለሚፈልጉ ሁሉ ግሩምና ድንቅ መልዕክት የያዘ መጽሐፍ ነው።*

*እኔም ይህን ጽሑፍ ለማንበብ ባገኘሁት ጊዜ ለንባብ በሚያዳግት ታይፕ ተጽፎ አንድ መቶ ገጽ ያለው ሆኖ አገኘሁት። በአነበብኩት ጊዜ በጣም የበሰለ "ትምህርተ መለኮት" የተገለጠበት ትምህርተ ሊቃውንት ሆኖ አገኘሁት። በመሆኑም የቀደሙት ሊቃውንት አስተምህሮ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንደገና አቅንቼ ጽፌ ለአንባቢ በሚመች መንገድ አቅርቤዋለሁ። ሊቁ የጠቀሷቸው መጻሕፍት ከታተሙት መጻሕፍት ጋር በምዕራፍ እና በቁጥር ስለማይገናኙ ከታተሙት መጻሕፍት ኃይለ ቃሉ የሚገኝበትን አብዛኛውን ምዕራፍ እና ቁጥር በመፈለግ ለማዛመድ ሞክሬአለሁ። የዚህን ጽሑፍ ባለቤት የጌታውን የታላቁ አለቃ ኀሩይ ታሪክም ከልዩ ልዩ ጽሑፎች አፈላልጌ በማግኘቴ አብሬ አሰባስቤ አሳትሜዋለሁ። የቀደሙትን ሊቃውንት ትምህርት ለማግኘት ዕድል ያጋጠማቸው ደቀ መዛሙርት በየእጃቸው የሚያገኙትን ጹሑፎች በማሳተም ከአበው አስተምህሮ ትውልዱ እንዲሳተፍ እንዲያደርጉ ትልቅ ምሳሌ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ከዚህም ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን የአስተምህሮ ሂደትና ስልት እንዲሁም የአስተምህሮ ምንጮችን ለመግለጽ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ትናንት እና ዛሬ " በሚል ርዕስ ጠቅላላ መግቢያ ሠርቸለታለሁ። ይህም ወደፊት ለሚታተሙት መድበሎች ሁሉ*

*ተቀዳሚ እንደ እሸት የሚቆጠር ሥራና ታላቅ ምሳሌ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።*

*ልዑለ ቃል አካሉ*

## *የአለቃ ኀሩይ ታሪክ*

***ልደት*** *:- ከ፲፰፻፶፰-፲፱፻፵፰ (1855-1948) አለቃ ኀሩይ ፈንታ በጎንደር ክፍለ ሀገር በበጌምድር የሊቃውንት ምንጭ የድጓ ማስመስከሪያ የሊቃውንት መነሃሪያ በሆነችው በቤተልሔም ተወለዱ።*

*የተወለዱት በ፲፰፶፰ ዓ.ም መስከረም ፲፯ ነበር። አባታቸው የተማሩ ሊቅ ከመሆናቸውም ባሻገር የቤተልሔምና የአካባቢዋ ሊቀ ካህናት ነበሩ። ስማቸውም ሊቀ ካህናት ፈንታ ይባል ነበር። እናታቸው ወይዘሮ ብሪቱ ይባሉ ነበር። የአለቃ ኀሩይ ወላጆች ብዑላነ ጸጋ (ባለ ጸጎች) እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ስለ ጌታው አለቃ ኀሩይ በጻፉት አጭር የሕይወት ታሪክ ላይ "አባታቸው የወይን ጠጅ ድረስ የሚያጠጡ ባለጸጋ ነበሩ" ብለው በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ከታደሉ ቅዱሳን ሰዎች መገኘታቸውን ተናግረዋል።*[1]

***ዕድገት*** *:- የአለቃ ኀሩይ አባት የሊቀ ካህናት ፈንታ ድንገተኛ ሞትና የእናታቸው የወ/ሮ ብሪቱ ትጋት የአለቃ ኀሩይ ዕድገት፡-*

*ሊቀ ካህናቱ አባታቸው በድንገት ስላረፉ በሕፃንነታቸው አባታቸውን ያጡትን ሕፃን በመልካም አስተዳደግ ለማሳደግና ለቁም ነገር ለማብቃት ወ/ሮ ብሪቱ በትጋት መሥራት ጀመሩ። እንደ አባት እንደ እናት ሆነው በቁም ነገር በሥርዓት አሳድገው ትምህርት ቤት አስገቧቸው። ብሩህ አእምሮ የነበራቸው የቀለም ሰው ስለነበሩ በአጭር ቀን ውስጥ ከንባብ እስከ ዜማ ያለውን ትምህርት አጠናቀቁ። መላከ ብርሃን ይህን ሁኔታ "አእምሮአቸው እንደተዳመጠ ብራና ቀለም የሚቀበል ስለሆነ ከንባብ እስከ ዜማ ያለውን ትምህርት*

[1] አድማሱ ጀምበሬ ዝክረ ሊቃውንት ፲፱፻፰፫ ዓ.ም

*በትንሽ ቀን አጥንተው በዚያው ወራት ቅጽል ከባለቤት ለይተው ዘርፍ ከባለቤት አስማምተው ተነሽና ወዳቂ ጠንቅቀው ሲያነቡ ዕጨጌ ቴዎፍሎስ ሰምተው ይህ ልጅ ታላቅ መምህር ይሆናል ብለው ትንቢት ተናግረውላቸዋል" በማለት ነበር የሊቁን የቀለም ሰውነት የሃይማኖት ዐምድ እንዲሆኑ ከእግዚአብሔር በተፈጥሮ ለእውቀት የታደሉ እንደነበሩ የገለጹት፡፡*

*ክብርት እናታቸው ወ/ሮ ብሪቱም በልጅነቱ አባቱን ያጣው ሕፃን ረዳት አጥቶ በችግር ተፈቶ ትምህርቱን ትቶ የእናቱን ቤት ተመኝቶ ወደ ኋላ እንዳይመለስ ለትምህርት ጎጃም ሲሄዱ ጎጃም ድረስ ወደ ጎንደር ከተማም ሲሄዱ ጎንደር ከተማው ድረስ በበቅሎ በአህያ ስንቅ እያስጫኑ "ተማር የአባትህን ስም እንድታስጠራ ለቤተ ክርስቲያን ብርሃን እንድትሆን እኔ እናትህ እያለሁ ምንም የሚቸግርህ ነገር የለም" እያሉ እያበረታቱ በትምህርታቸው እንዲገፉበት ለዚህም ማዕረግ እንዲበቁ አደረጉአቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ አለቃ ኅሩይ ምንም እንኳ ሰው የተባለውን (የሆነውን) ሁሉ የሚወዱ ፍቅረ ቢጽ የተሰጣቸው ለሁሉም አክብሮትና ፍቅር ያላቸው የፍቅር ሐዋርያ ቢሆኑም ለእናታቸው ያላቸው ፍቅር የተለየ ነበር፡፡*

*ይኸውም ሊታወቅ ጌታው አለቃ ኅሩይ አዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ አጠገብ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በሰጧቸው ማረፊያ ቤት እያሉ የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑት ታላቅ ወንድማቸው ሊጠይቋቸው ከቤተልሔም ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡ አለቃ ኅሩይ "ሁሉን ልትነግረኝ ትችላለህ እናቴን ግን ሞተች ብለህ እንዳትነግረኝ፡፡ የእናቴን ሞት ሳልሰማ እኔ መሞት እፈልጋለሁ" ስላሏቸው የእናታቸውን ሞት ሊያረዱ የመጡት ወንድማቸው ሳይነግሯቸው ተመልሰው ሄዱ፡፡ ሌላም ጊዜ ሲመጡ ተመሳሳይ ነገር ስለተናገሯቸው ታላቅ ወንድማቸው አዝነው "እኔ እንዲህ ሸምግዬ እያየ እንዴት እናታችን በሕይወት ትኖራለች ብሎ ይገምታል" ብለው አዝነው ተመልሰው ሄደዋል፡፡ እንዲህ እያሉ የመጣውን ሰው ሁሉ እየመለሱ*

*የእናታቸውን መሞት ሳይሰሙ እርሳቸው አርፈዋል:: ይህም ለእናታቸው የነበራቸውን ፍጹም ፍቅር ያስታውሰናል::* [2]

## *ትምህርት ቤት*

*ዕጨጌ ቴዎፍሎስና አለቃ ኀሩይ:- ከላይ እንዳየነው ዕጨጌ ቴዎፍሎስ የአለቃ ኀሩይን የተፈጥሮ ጸጋ ከተረዱ በኋላ በመንፈሳዊ አባትነታቸው አስበው የሊቀ ካህናቱን የአባታቸውን መሞት አውቀው ስለነበር ከእናታቸው ድጋፍ በተጨማሪ በችግር ምክንያት ትምህርታቸው እንዳይቋረጥ በማሰብ ቀለብ አዘውላቸው ነበር:: በወቅቱ የድጓ ምስክር ከነበሩት ከመምህር ደርሶ "ዜማ" እንዲማሩ ያደረጓቸው ዕጨጌ ቴዎፍሎስ ናቸው:: የአለቃ ኀሩይን የትምህርት ቤት ሕይወት ስለ አለቃ ኀሩይ ታሪክ ከጻፉት ሊቃውንት መካከል ጥሩ አድርገው የጻፉት “ዘወትር ከጉባኤያቸው እየተገኙ የተሰወረውን ምሥጢር የምሥጢር ባለቤት ከሆኑት ከአለቃ ኀሩይ ይረዱ ነበር” ብለው ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ (አቡነ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ ዘጎንደር) ስለአለቃ ኀሩይ ታሪክ ሲጽፉ የጠቀሷቸው የዲማው ሊቅ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ናቸው:: መላከ ብርሃን አድማሱ "ዕጨጌ ቴዎፍሎስ ቀለብ ሰጥተው የድጓ ምስክር ከነበሩት ከመምህር ደርሶ ዜማ እንዲማሩ አድርገዋቸዋል:: እሳቸውም (አለቃ ኀሩይ) በዚህ ትምህርት ቤት ድጓ አንድ ጊዜ ከዘለቁ በኋላ ተድባበ ማርያም ሂደው አለቃ ወረደ ቃል ከሚባሉት መምህር ቅኔ ተምረው ተቀኝተው እንደገና ጎጃም ተሻግረው ኢጋሜና ቢሰውር ከሚባሉት ስመ ጥር መምህራን ቅኔውን አስፍተው እስከ አገባቡ ጠንቅቀው አውቀው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እንደገና ድጓውን መላልሰው አጥንተው ለምስክርነት ተመርቀዋል:: መምህር ደርሶም በእኔ እግር ተተክቶ የድጓ ምስክር ይሆናል እያሉ ሲያስቡ ልቦናቸው ወደ መጻሕፍት ትምህርት ስላዘነበለ ጎጃም ተሻግረው ደብረ ጽላሎ*

[2] ብፁዕ አቡነ ሚልከ ጼዴቅ በቃል የነገሩኝ 1999 ዓ.ም

ከአለቃ እንግዳ ብሉያትን አጠኑ:: ከዚያም ጎንደር ሂደው ከታላቁ መምህር ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል በጥቂት ቀን የሐዲሳትን ትርጓሜ አጥንተዋል:: በዚያው ጊዜ (ጎንደር ሳሉ) አዕምሮ ከሚባሉ የአቋቋም መምህር አቋቋም ተምረዋል:: ድምፃቸው በተፈጥሮ መልካም ከመሆኑም በላይ ዜማ ያሸው ስለሆነ በጎንደር ባህል ሲዘሙ ሲመረግዱ ዚቅ ሲያወርዱ መልስ ሲመልሱ "እንስማው" የሚባሉ እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ" ብለው ጽፈውላቸዋል:: [3]

## ***ጎንደርን ድርቡሽ እንዳጠፋው ሊቃውንት እንደተሰደዱ***

*ለብዙ ዘመናት የኢትዮጵያ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥልጣኔ፣ አስተዳደር፣ ዕውቀት ማዕከል፣ የሊቃውንት መንደር፣ የመላው የኢትዮጵያ መናገሻ ማዕከል ሆና ትኖር የነበረችውን ጎንደርን የእስላም ኃይል ገብቶ ባቃጠላት ጊዜ ሊቃውንቱ እያዘኑ እያለቀሱ ከእሳትና ስለት የቀሩት ለዘር ይተርፉ ዘንድ ተሰደዱ:: እነ መምህር ወልደ አብ ወልደ ሚካኤልን ጨምሮ ብዙ ሊቃውንት በእስላሞች ሰይፍ ታረዱ::*

*ከሞት የተረፉትም ብሶታቸውንና የሀገራቸውን ጥፋት*

*በቅኔያቸው እያስታወሱ እያለቀሱ ተሰደዱ:: በ፲፰፻፹፰ (1888)*

*ዓ.ም ጎንደርን ድርቡሽ ባቃጠላት ጊዜ ከአንድ ሊቅ የተደረሰ የሐዘን እና የጸጸት* ***መወድስ ቅኔ*** *እነሆ:-*

*ሠናይተ ሠራሬ ጎንደር ተሰፋ ኑዳያን*

*ወተሰፋ መኳንንት ጎንደር እንበለ መሥፈርት ወአቅም::*

*ርግበ ዮሐንስ ጎንደር ርኅርኅተ ልብ እም::*

*ጎንደር ዘበላዕሌሃ ኢሀሎ ሕማም::*

---

[3] ዝኒ ከማሁ አድማሱ ጀምበሬ (መላከ ብርሃን) ዝክረ ሊቃውንት በ፲፱፻፷፫

ዓ.ም

*ጎንደር እድምተ ስም።*

*መካነ ተድላ ጎንደር ወመካነ መብልዕ ጥዑም።*

*ጎንደር ቤተ ኢያሱ ወቤተ በካፋ ግሩም።*

*ጎንደር ዘትሤንያ ለሀገረ ዳዊት ምድረ ሰላም።*

*መሐድምተ ትኩን እስከ ለዓለም።*

*እፎኑ ተመዝብረት እንበለ ፍዳሃ ከመ ሶዶም።* [4]

*በዚህ ክፉ ዘመን ከተሰደዱት መካከል አንዱ አለቃ ኀሩይ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ጋራ ወደ ቤተልሔም ወደ መካነ ትውልዳቸው ተመለሱ። "ቤተልሔም ጥቂት ቀን ከቆዩ በኋላ ወደ ግሸን ሄደው የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜና አቋቋም ሲያስተምሩ ቆይተው ወደ ደብረ ሊባኖስም በመሔድ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር ራስ ዳርጌ የሊቁን ብቃት በመመልከት የሥሬ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አለቃ እንዲሆኑ የጠየቁአቸው። እርሳቸው ግን መናኝ በመሆናቸው መጽሐፍ በመመልከት ዘመናቸውን እንዲፈጽሙ ስለወሰኑ ሹመቱን አልፈልግም ብለው ትተውት ወደ አዲስ አበባ መጥተው መዝሙር ካሣ ከሚባሉት ከጎንደሩ ሊቅ መጽሕፍተ ሊቃውንትን አጠኑ። ከዚያም ደብረ በግዕ ወርደው ከአለቃ ወልደ ማርያም ሊቃውንትን አደረሱ።" (አስመሰከሩ) በማለት መላከ ብርሃን አድማሱ የአለቃን ታሪክ በጻፉበት አምዳቸው ዘግበዋል። ከዚህ በመቀጠል የታላቁን ሊቅ የጌታው አለቃ ኀሩይን ትጋትና ምሥጢር ለማደላደል ለማራቀቅ ነገረ እግዚአብሔርን ያውቁ ከነበሩት ሊቃውንት ጋር በመወያየት የልቦና*

---

[4] አድማሱ ጀምበሬ (መላከ ብርሃን) ዝክረ ሊቃውንት፲፱፻፹፫ ዓ.ም

*ደስታ ያገኙበት እንደነበር፣ ዕለት ከዕለት ከኃይል ወደ ኃይል ይራመዱበት፣ መጻሕፍትን ማንበብ ዋና የዕለት ተለት ተግባራቸው ሁኖ ይኖሩ እንደነበር ሲያስገነዝቡ "ከዚህ በኃላ ወደ ጎጃም ተሻገሩ:: በዚያን ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ነበሩና አክብረው ተቀብለዋቸዋል:: እርሳቸው ግን በመጻሕፍት ፍቅር ብቻ የተወሰኑ ስለሆኑ ደጅ ልጥና ልሾም ልሸለም ሳይሉ ብሉያትን ከብሉይ መምህራን ከነ መምህር ሰውአገኘሁ፣ ከእነ መምህር ጸበሉ፣ ከእነ አለቃ ገብረ ኤልያስ፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ከእነ አለቃ ተስፋ፣ ከእነ ሊቀ ጠበብት ወልደ ሥላሴ፣ ከእነ መልአከ ሰላም ገብረ ማርያም፣ ከእነ መምህር እንግዳ እሸት ጋራ እየተጨዋወቱ ሐሳብ ለሐሳብ ከተለዋወጡ በኋላ አዋልድ መጻሕፍት በያይነቱ ከሚገኙባቸው ደሴቶችና ገዳማት በነዘጌ፣ በነክብራን፣ በጣና ቂርቆስና በዲማ እየተዘዋወሩ ተመለከቱ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ብዙ ተማሪ ይከተላቸው ነበርና አንድም ቀን ጉባኤ ፈትተው አያውቁም" በማለት መላከ ብርሃን የጌታው አለቃ ኀሩይን የቀለም ሰውነት፣ አንባቢ ተመራማሪ የትርጓሜ ሰው እንደነበሩ መስክረዋል:: መላከ ብርሃን አድማሱ በጉባኤያቸው እየተገኙ ማወቅ የሚፈልጉትን ምሥጢር ለመጠየቅ ከአለቃ ኀሩይ ጉባኤ ቤት ይገኙ ስለነበር በዓይናቸው ያዩትን በጆሮአቸው የሰሙትን የታላቁን ሊቅ የጌታው አለቃ ኀሩይን የዕውቀት ብቃት፣ የአእምሮ ምጥቀት፣ የአስተሳሰብ ብስለት፣ የትርጓሜ ስልት ባለቤትነት፣ የጠፋ መገኛ የተሰወረ መገለጫ፣ አንቀጸ መጻሕፍት መሆናቸውን ሲገልጹ "የተፈጥሮ እውቀታቸውን በትምህርት ስላስፋፉት ትምህርታቸውንም መጽሐፍ በመመልከት ስላደረጁት የጠፋ ንባብ የተሰወረ ምሥጢር ከእርሳቸው ይገኝ ነበር:: አለቃ ኀሩይንም ጠይቆ ሳይረዳ የሚሄድ አልነበርም" በማለት ሊቁ መላከ ብርሃን ያዩትን መስክረዋል:: አለቃ ኀሩይ በ፲፱፻፬ (1904) ዓ.ም ከጎጃም ወደ ጎንደር ሄደው ነበር:: በወቅቱ የነበሩት ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስም አክብረው ተቀብለው ጸዳ እግዚአብሔር አብን ልቅና ልስጠዎት ይሾሙ ቢሉአቸው አይሆንም ስላሉአቸው የሹመት ፍላጎት የጠፋላቸው ቅዱስ ሰው መሆናቸውን*

*አውቀው ሸልመው ከእነ ተማሪያቸው የሚመገቡትን ቀለብ ሰጥተዋቸው በጎንደር ለሦስት ዓመታት ጉባኤ ዘርግተው አስተምረዋል።*

### *የኢየሩሳሌም ጉዞ*

*ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም መጥተው ኢየሩሳሌምን እጅ ነሥተው ተመልሰዋል። ከዚህ በኋላ ደብረ ሊባኖስ ገብተው ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ከዚያም በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት እየተተረጎሙ ሲታተሙ ተጠርተው መጥተው ከሌሎች ሊቃውንት ጋር ሆነው ወንጌልን ተርጉመው አሳትመዋል። መላከ ብርሃን እንደገለጹት ከመጻሕፍተ ሊቃውንትም ቄርሎስን ንባቡን ከነትርጓሜው አዘጋጅተው አስረክበዋል። ከዚህ በተጨማሪ "የቤተ ክርስቲያን ጸሎት" በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የቀረበው በስደት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ትጠቀምበት የነበረው መጽሐፍ አዘጋጆች ከሆኑት አንዱ አለቃ ኅሩይ ነበሩ። ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህም "ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጻሕፉቸው "ሐዲስ ኪዳንን የተረጎሙት ንቡረ ዕድ ተክሌ (ሐዲስ ተክሌ)፣ አለቃ ኅሩይ ዘጎንደር፣ አለቃ ለማ ዘመካነ ሥላሴ፣ አለቃ ቀጸላ ዘእንጦጦ ማርያም፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆነው በየክፍላቸው በቅንነት ሠርተው ያበረከቱ ናቸው። ሥራቸውም ቋሚና ዘላቂ ሆኖ እነርሱንና ንጉሠ ነገሥቱን ሲያስታውስ ይገኛል" ብለው ለቤተክርስቲያን መጻሕፍትን በመተርጎም ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ዕውቅና ታላቅ ሊቅ እንደነበሩ ከላይ  የተመለከትናቸው መላከ ብርሃንና ሊቀ ሥልጣናቱ*

*ቋሚ ምስክሮች በመሆን ሊቁን በሥራቸው እንድናውቃቸው አድርገዋል።* [5]

*ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያት የደከሙባቸው መጻሕፍት ለኅትመት አልበቁም። አለቃ ኅሩይ አበ ብዙኅን ናቸው። "ዕድለ መልካም ሊቅ ስለነበሩ በጉባኤ የወለዷቸው ደቀ መዛሙርት እጅግ ብዙዎች ናቸው" ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ሊቃውንትን የሚያፈሩ ሊቃውንት የሳቸው የቀለም ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው። ደቀ መዝሙራቸው የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ ስለ አለቃ ኅሩይ ሲጽፉ "ታላቁ ሊቅ አለቃ ኅሩይ መጻሕፍተ ሐዲሳትንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን  የዕለት ተግባራቸው አድርገው በጉባኤ ሲያስተምሩ አርባ ዘመን ያህል ቆይተዋል። መጻሕፍተ ሐዲሳትን በማስተማር እስከ ዕለተ መቃብር ቆይተዋል። በዚህ ድካማቸው ጊዜ ብዙ ደቀ መዛሙርትን ተከተዋል" ካሉ በኋላ ለምሳሌ ያህል የስምንት ሊቃውንትን ስም ዘርዝረዋል። ታላቁን ሊቅ ጌታው ዶክተር አለቃ አየለን ጨምሮ ሊቀ ሊቃውንት መኀሪ ትርፌ (ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ ዘጎንደር) ፣ አባ ዘካርያስ ንቡረ ዕድ መኩሪያ፣ መምህር ወንድም አገኘሁ፣ አባ ጌድዮን፣ አለቃ ገ/መድኅን፣ አባ ገ/አምላክ ከደቀ መዛሙርቶቻቸው መካከል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። አለቃ ኅሩይ ፍፁም መናኝ ነበሩ። "አለቃ ኅሩይ ከዚህ  ዓለም ክብር የራቁ በመሆናቸው ከቶ አንድ ጥሪት አልነበራቸውም" ካሉ በኋላ ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ ከአፄ ኃ/ሥላሴ ጋር ስለነበራቸው ቀረቤታና በጉባኤያቸው ተገኝተው የከበዳቸውን ምሥጢር ይጠይቁ ስለነበሩ ሊቃውንት፣ ስለተሰጣቸው ዕሜተ አንብዕ፣ ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ጋራ ስለነበራቸው ጽኑ ፍቅር እና ስለመጨረሻው ዕረፍታችው የሚከተለውን ጽፈዋል።*

*አለቃ ኅሩይ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የጠበቁ እውነተኛ መምህር ስለነበሩ ግርማዊነታቸው ከዕልፍኛቸው አስቀምጠው በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እየረዱ በየዕለቱ ይጎበኟቸው ነበር። አለቃ*

---

[5] ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት

*ኀሩይ ግርማዊነታቸውን በሚያዩበት ጊዜ ሁሉ ከፍቅራቸው ጽንዓት የተነሳ ደዌያቸውን ሁሉ ይዘነጉት ነበር፡፡ አለቃ ኀሩይ ዕሜተ አንብዕ የተሰጣቸው ስለነበሩ በቅድስት ሥላሴ አጠገብ ግርማዊነታቸው በሰጧቸው ቤት ሳሉ ትሕትና ገንዘባቸው የሚሆን ግርማዊነታቸው ሊጠይቋቸው ሲሄዱ ለማናገር በሩ በተከፈተ ጊዜ ዕንባቸው በሚጸልዩበት አርጋኖን ላይ ሲንጠባጠብ ታይቷል...*

*ሊቃውንቱን የሚንከባከቡ ግርማዊነታቸው እኒህን ሊቅ እንደ ዐይናቸው ብሌን ይንከባከቧቸው ስለነበረ አስታመው አማውተው እስከ መቃብር ሸኝተው ተመልሰዋል፡፡ ...የአለቃ ኀሩይ ሞት ሞት አይባልም ከልባቸው ፈልቆ የአርድእትን ልቡና ያረካው ትርጓሜያቸው አካል ገዝቶ ስለተገኘላቸው፡፡ አለቃ ኀሩይ ከትዕግሥታቸው ብዛት የተነሳ የሐረሩ ሊቅ አለቃ ገብረ አብ ዲያብሎስ ቅሉ ድል ሊነሣቸው አይችልም ብለው የተናገሩት ነገር ሲነገር ይኖራል፡፡ አለቃ ኀሩይ በነበሩበት ጊዜ በአዲስ ዓለም ማርያም የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በዕየለቱ ሊጠይቋቸው ሲመጡ የነበረ ፍቅር ልክ አልነበረውም፡፡ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ  እንደ አረፉ በሰሙ ጊዜ ጉባኤውን አጥፈው በኀዘን ቆይተው የፍቅራቸው ብዛት ሊታወቅ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በዐረፉ በአርባ ቀን አለቃ ኀሩይ ዐርፈው በደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ፡፡ የሐረር ሥላሴ አለቃ፣ አለቃ ለማም ከአለቃ አየለ ሃይማኖተ አበውን ለመስማት ዘወትር ከአለቃ ኀሩይ ጉባኤ ይገኙ ነበር፡፡ የዲማው ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱም ዘወትር ከጉባኤያቸው እየተገኙ የተሰወረውን ምሥጢር የምሥጢር ባለቤት ከሆኑት ከአለቃ ኀሩይ ይረዱ ነበር፡፡ የአለቃ ኀሩይ ታሪክ ብዙ ነበር፡፡ ከብዙ በጥቂቱ በዚህ መጽሐፍ ገልጸነዋል፡፡[6]*

*በማለት ነው አባታችን ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቋሚ ምስክርነታቸውን የተውልን፡፡*

---

[6] *ሠለስቱ ሐዲሳት ገጽ ፬፻፹፰*

በተመሳሳይ መንገድ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬም የአለቃ ኀሩይን አጭር የሕይወት ታሪክ ሲያጠቃልሉ "በእንደዚህ ያለ አኳኋን ከቆዩ በኋላ እርጅና ከደዌ ጋር ተጭኗቸው ከቤት በዋሉ ጊዜ የሰው ውለታ የማይቀርባቸው ግ/ቀ/ኃ/ሥላሴ በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ የተሰናዳ ማረፊያ ቦታ ሰጥተው እጅግ በተመቻቸ ኢያያዝ ሲረዱ ቆይተው በ፺፫ ዓመታቸው በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ሐምሌ ፲፰ ቀን ዐርፈው በደብረ ሊባኖስ ተቀብረዋል" ብለዋል። በሃይማኖት ወደ ሚናፍቋት በቃለ መጻሕፍት ወደ ለመደ ት ወደ ርስተ ቅዱሳን ወደ ሕጽነ አብርሃም ወደ ማታልፈው መንግሥተ እግዚአብሔር ሄደዋል።

ይህንንም በተመለከተ መምህር አባ ዓለሙ በላይ የብፁዕ አቡነ

መርሐ ክርስቶስ ባልንጀራ በቃል ከብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ

የሰሙትን ታሕሣስ 18 2001 ዓ.ም እንደሚከተለው

አጫውተውኝ ነበር፤ “አለቃ ኀሩይ ማክሰኞ ሊያርፉ እሁድ ቀን

መምህር ያሬድ (አቡነ መርሐ ክርስቶስ) ምሥጢር እየጠየቁ ሳለ “እኽ ሳላመልጥህ ጠይቅ፤ ላመልጥህ ነው ጠይቀኝ” አሏቸው አለቃ፤ አቡነ መርሐም ጌታው እድሜዎ ሰፊ ነው፤ ይበቃዎታል ግን እኔ የሃይማኖተ አበውን ምሥጢሩን ሳልረዳው የተማርኩትን ከፊትዎ አንብቤ ሳልዘልቀው በመሞትዎ ብቻ ነው የማዝነው አሏቸው፤ “አዎ እኔም ለብዙ አስቤህ ነበር ግን ሐዲሳቱን አውቀኸዋል፤ ከሐዲሳቱ የወጣ ምሥጢር በሃይማኖተ አበው የለም፤ ያንኑ ምሥጢሩን በምሳሌ ማብዛት መግለጽ ነው እንጂ፤ ለሁሉም ምዕላዱን አንብበው፤ ነገር ያለበትን እና ኃይለ ቃሉን በምዕላዱ ላይ አውጥቼዋለሁ” አሏቸው፤ ሰኞ እንደበታቸው ተያዘ፤ ማክሰኞ አረፉ፤ ቀደም ብለው ራሳ ካሳ መጥተው “ቀብርዎት የት ቢሆን ይወዳሉ ቅድስት ሥላሴ ይሁን ወይስ ደብረ ሊባኖስ ነው የሚፈቅዱት” አሏቸው፤  አለቃም “ፈቃዴ ደብረ ሊባኖስ ቢሆን ነው፤ ግን ፈራሽ ሥጋ ተሸከሙ አልልም፤ እግዚአብሔር ከፈቀደው ይውደቅ” አሉ፤ ከዚህ በኋላ ሲያርፉ የቤተ ክርስቲያኑ ደወል ተደወለ፤ ቅድስት

*ሥላሴ ከቤተልሄሙ መቃብር ተቆፍሮ ነበር፤ ነገር ግን ራስ ካሳ በኋላ ደረሱና “የለም አይሆንም ደብረ ሊባኖስ ነው የሚሄዱ” ብለው ደብረ ሊባኖስ ወስደው ቀበሩአቸው፤ አጼ ኃይለ ሥላሴም ደብረ ጽጌ ድረስ ሸኝተው ተመልሰዋል” ብለውኛል።*

*ቅዱስ ያሬድ የጥናት እና የተራድኦ ማዕከል የቀደሙትን አባቶቻችንን ትምህርት፣ ጥበብ፣ ታሪክ ለትውልድ ለማስተዋወቅ ለማቆየት የጀመረው የሥራ ፍሬ በታላቁ ሊቅ በጌታው አለቃ ኀሩይ ታሪክ እና ትምህርተ ሃይማኖት በመጀመሩ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል።*

*በረከተ አበው መምህራን አይለየን!*

*ቅኔዎች*

*ለመታሰቢያ ከቀረቡት ከአለቃ ኀሩይ ቅኔዎች ጥቂቶቹ*

*መወድስ ፩*

*ሰብዓ አዝማነ አርድተ ብካይ*

*እም ሕዝበ ዘመኑ ዮሐንስ ለስብከተ ሐዘን ሐረየ፤*

*ወማዕከለ ኀዘን ፍኖቱ ለእመ ጸምአ ብካየ፤*

*አምነ ሳምራዊት ሰአለ ዐይነ ወንጌላዊ ከመ ይስተይ ማየ፤*

*ሕዋሳቲሁ ሐዋርያት እስመ ሀገረ ሞት በኢ ለተሳይጦ ሲሳየ፤*

ተጋብኡሂ ገጻቲሁ ማዕከለ አዕይት ዝየ፤

ላዕለ ዕፅ ከመ ይሰቅሉ ህሊና ዘኢጌገየ፤

ወውስተ ካልዑ መብልዕ ሐሞተ ምሳሌ ወደየ፤

በሕለተ ወይን ትርጉሜሁ ስታየ ስሙ እስመ ዐበየ፤

መወድስ ፪

ሞተ ፍጡራን ተምህረ ገቢረ ትሕትና

አንቃዕዲዮ ኢይርአይ ገጸ አረጋዊ በዐይኑ፤

ባህቱ ይብለነ ዉስተ ደብረ ዳሞ መካኑ፤

እንበለ ውእቱ አረጋዊ

ሥጋ ሰብእ ለቢሶ ዘሞአኒ መኑ፤

ንንግር ወንዜኑ፤

ከመ ከመ ሊቁ ኤልያስ ለአረጋዊ መጠኑ፤

ለሕያዉኒ ገብረ ክርስቶስ ላዕካነ ምሥጢር ይኩኑ፤

ካህናተ ሰማይ ሕማማት መንበረ ሥጋሁ ዘየትጥኑ፤

ወእም ሐዋርያት ገድላት እለ ተአመኑ ዮሐንስ ዐፄ ሥጋ ዘረፈቀ
ውስተ ሕፅኑ፤[7]

---

[7] የግዕዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ ንባብና ትርጓሜው ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ 1980

*መወድስ ፫*

*አሣዕነ ገባዖን ነሥአ ውስተ ደብረ ዘይት*

*መከልአ ምድያም ቃል መግቦተ ርእሱ ኀበ አእመረ፤*

*ወበአልባሰ ብርት ገባዖን ዕርቃነ መልአክ ሰወረ፤*

*ለኢየሩሳሌም እንዘ ቅርብት መላክ በጊዜ ነገደ ርህቅተ ምድረ፤*

*ኢያሱ እስከ ሰአለ ለማዕረረ ቃሉ ድንግል ከመ ይፈኑ ገባረ፤*

*ወገባዖን ቀዳማዊ ድኅረ በምሳሌ አንጸረ፤*

*ጸወርተ ዕፀው ከመ ይኩኑ ለቤተመቅደስ ዘተመዝበረ፤*

*ሥጋ ወቃል ተሰናዕዎ ዕፅ አንበረ፤*

*እብነ ዘለፉ መልዕልተ ወርቅ ብልጣሶር ዘአንበረ፤*[8]

***ማስታዎሻ*** ፦ከዚህ በኋላ ያለው ሙሉው መጽሐፍ ከግርጌ ማስታዎሻውና ከመፍትሔ ቃሉ በቀር በኣለቃ ኃሩይ የተጣፈ ነው። የመጥሐፉም ሙሉ ዓለማ በምሥጢረ ሥላሴ ላይ ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት እያሉ የሚያስተምሩትን ትምህርት የሚርምና መልስ የሚሰጥ ነው። መልካም ንባብ።

[8] አድማሱ ጀንበሬ:: መጽሐፈ ቅኔ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም

## *መቅድም*

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ዘለዓለም ሥላሴ::

*ንባብ* :- ንጽሕፍ መቅድመ አሠሩ ወፍኖቱ ለእግዚአብሔር በረድኤት አምላካዊት ከሃሊተ ኵሉ፣ ከሂሎታኒ አኮ ባሕቲቱ በአበው ለባውያን ወማእምራን፣ አላ ዓዲ በሕፃናትኒ የዋሃን፣ በከመ ቃሉ ለእግዚእነ "አእኵተከ አባ እግዚአ ሰማይ ወምድር፣ እስመ ኀባእኮ ለዝንቱ እማእምራን ወእምጠቢባን፣ ወከሠትኮ ለሕፃናት እስመ ከማሁ ኮነ ሥምረትከ በቅድሜከ"

*ትርጉም* :- ከአምላክ በምትገኝ፣ ሁሉን ማድረግ በሚቻላት ረድኤት የእግዚአብሔርን የጎዳናውንና የፍለጋውን መቅድም እንጽፋለን:: ችሎታዋም በዐዋቆችና በልበኞች ብቻ አድራ አይደለም፣ አላዋቆች በሆኑ ሕፃናትም አድራ ነው እንጂ:: ጌታችን እንዲህ ብሎ እንደተናገረ፣ "አመሰግንሃለሁ አባት ሆይ የሰማይና የምድር ጌታ፣ ይህን ከዐዋቆችና ከልበኞች ሰውረህ ለሕፃናት ገልጠኸዋልና፣ እንዲህ በፊትህ ፈቃድህ ስለሆነ"[9]

*ንባብ* :- በእንተ ዝንቱ ፈቀድነ ንጽሐፍ ኀዳጠ እምነ ብዙኅ፣ በእንተ እማሬሃ ለይእቲ ፍኖት ሠናይት:: ፍኖትሂ ሠናይት ሃይማኖት ይእቲ ብሂለ አሐዱ መለኮት ወሠለስቱ አካላት፣ ባቲ ያጽንዐነ እግዚአብሔር ሎቱ ስብሐት እስከ እስትንፋስ ደሃሪት ለዓለመ ዓለም አሜን::

---

[9] ማቴ ፲፩ : ፳፭-፳፮

*ትርጓሜ*:- ለሕፃናተ አእምሮ ምሥጢርን የሚገልጽ ስለሆነ የዚችን ቅን ጎዳና ነገር ለማስረዳት፣ ከብዙ በጥቂቱ ልንጽፍ ወደድነ:: መልካም ጎዳና የተባለችም ሃይማኖት ናት:: ይህችውም በአንድ መለኮት፣ ሦስት አካላት ብሎ ማመን ናት:: እስከ ጊዜ ሞት ድረስ በርስዋ ያጽናን እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ለዘለዓለም አሜን::

ከጌታችን ከኢየሱስ የተገኘች ሃይማኖት አንዲት ነበረች:: ለዚኸውም ማስረጃ ሐዋርያው ጳውሎስ "ሃይማኖት አንዲት ናት" ብሎ ተናግሮአል:: ኤፌሶን ፬፡፭ ነገር ግን የሰው ጥንተ ጠላቱ ሰይጣን በአንዳንድ ሰዎች እያደረ በዓላማው ስሕተት የሃይማኖት መለያየት መጣ::

*ማስረጃ ጌታችን በወንጌል*

*ንባብ* :- *“ወእንዘ ይነውሙ ሰብኡ መጽአ ጸላኢ ወዘርዐ ክርዳደ ማዕከለ ሥርናይ ወኀለፈ”*

*ትርጉም* :- “ሰዎች በተኙ ጊዜ ጠላት መጥቶ በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶበት ሄደ እንዳለ” ማቴ ፲፫፡፳፭

ንባብ:- *“ፀጋሰ ኢትትወሀብ ዘእንበለ ለትሑታን ወፈድፋደሰ ለምኑናን ወለየዋሃን”*

ትርጉም:- “የዕውቀት ሀብት ለተዋረዱ፣ ይልቁንም ለተናቁና፣ ቅንነት ላላቸው ነው እንጂ፣ ለትዕቢተኞች አትሰጥም” [10]ያለውን በመዘንጋቱ በፍቅርና በትሕትና ፀንቶ ወንድም ከወንድም ጋራ ሐሳብ ለሐሳብ እየተግባባ፣ በስምምነት ሃይማኖትን ወደጥንተ ቦታዋ፣ ወደ አንድነት

[10] ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን 3

በመመለስ ፈንታ፣ እኔ ያልሁት ይሁን ማለትን ስለወደደና፣ መለያየት ስለተስፋፋ፣ መነቃቀፍ ያመጣው የወገን ስም መለያየት ተፈጠረ::

ይልቁንም ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራፂ መለኮት የማለትና፣ መለኮትንም መንግሥትንም በአካል ሦስት የማለት እንግዳ ትምህርት ስለመጣ፣ ይህንም አንዳንድ ሰዎች አክብረው ስለተቀበሉት፣ አንዲት የኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከብዙ ከፋፈላት::

*የመጣበትም ምክንያት እንዲህ ነው*

*የኢትዮጵያ ሊቃውንት :-* ወንጌላዊ "ቃል ሥጋ ኮነ" [11] ያለውን ንባብ ከምሥጢር ተመልክተው፣ መለኮትና ትስብእት ተዋሕደው አንድ አካልና አንድ ባሕርይ በመሆናቸው፣ ክርስቶስ የአምላክነትንም የሰውነትንም ሥራ በአንድ ፈቃድ ይሠራል ብለው፣ እምነታቸውን ስለገለጡና ስላስተማሩ፣ በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች:- "ባሕርይ ተዋሐደ ከተባለ፣ ባሕርየ ሥላሴ አንድ ነውና፣ ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ" ያሰኛል ብለው ሲከራከሩ፣ ምሥጢሩን ያላስተዋሉ ሰዎች "መለኮት በአካል ሦስት" በማለትና "ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሰራጺ መለኮት" በማለት፣ የሐዲስ ትምህርት መንገድን አውጥተዋል:: ነገር ግን ይህ የሐዲስ ትምህርት መንገድ ዮሐንስ ተዐቃቢ የሔደበት ያልቀና መንገድ ነው:: ስለዚህ አስተዋዮች በቅን አስተያየት ተመልክተው በዚህ ባልቀና መንገድ ከመሄድ እንዲጠበቁበትና፣ "አንድ መለኮት በሦስት አካላት አለ" ወደ ማለት ቅን ጎዳና እግረ ልቦናቸውን እንዲያቃኑበት ይችን ትንሽ መጽሐፍ እንጽፋለን::

የዚችም መጽሐፍ ጥርጊያ ጎዳና "በአካል ሦስት በመለኮት አንድ አሰኝቶ፣ መለኮት አንድ ከሆነ፣ ሦስቱ ሰው ሆኑ ያሰኛል ብሎ

[11] ዮሐንስ ፩፡ ፲፬

ከመፍራት ጠብቆ "ከሦስት አካላት አንድ አካል ወልድ ብቻ ሰው ሆነ" ወደ ማለት ያለችግር በቀጥታ የሚያደርስ ስለሆነ ስሟ “ፍኖተ እግዚአብሔር” ተባለ::

## *አሠረ ፍኖት*

*ንባብ*:- “ኲሉ ማዕመቅ የምላዕ፣ ወኲሉ ደብር ወአውግር ይተሐት ወይኩን መብዕስ መጽያህተ ርቱዐ፣ ወይዕሪ ፍኖት መብዕስ፣ ወይርአይ ኲሉ ዘነፍስ አድኅኖቶ ለእግዚአብሔር”

*ትርጓሜ*:- “ዝቅ ያለው ሁሉ ከፍ ይበል፣ ተራራው ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል:: ጠማማውም ይቅና:: አቀበቱም ሜዳ ይሁን:: *ሥጋን* የለበሰ ሁሉም የእግዚአብሔርን ትድግናውን ይይ” [12] “ማዕምቅ እንደ ሰባልዮስ አንድ ገጽ የሚል አንድ ገጽ ማለቱን ትቶ ባሕርየ መለኮት አንድ በሚያደርጋቸው በሦስቱ አካላትና በሦስቱ ገጻት ይመን”

*ማስረጃ*:- *ዮሐንስ ዘአንጾኪያ* "ንትአመን በሠለስቱ አካላት ወበሠለስቱ ገጻት፣ እንተ አሐዱ ባሕርየ መለኮት" [13]ብሏልና::

---

[12] ኢሳ ፵፡-፬፭

[13] ፍቹ "በሦስት አካላት በሦስት ገጾች አንድ ባሕርይ ማእከት ባለው እንታመናለን" ማለት ነው::

*ደብር (ተራራ)*

እንደ ዮሐንስ ተዐቃቢ ዘጠኝ መለኮት ወይም ሦስት አማልክት ዘጠኝ አካላት ከማለት የሚያደርስ መለኮትና መንግሥት በአካል ሦስት የማለት እምነትን የያዘ ይህን አርቆ ሥላሴ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ፣ መንግሥታቸውም በአካል ከሦስት የማትከፈል አንዲት ብቻ እንደሆነች ይመን::

*ማስረጃ:- የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ዲዮናስዮስ*

"ወኢንበውእ ውስተ ከፊለ መለኮት ወመንግሥት አላ ንብል አሐዱ መለኮት ወአሐዱ መንግሥት ይትወሐዱ በመለኮት ወይሤለሱ በአካላት"[14] እንዳለ::

*ሠለስቱ ምዕትም:-*

"ሥሉስ ፍጹም በአሐዱ መለኮት እስከ ለዓለም አሐዱ እግዚእ ወአሐቲ መንግሥት እንተ ኢትትከፈል ወኢትትፋለስ"[15] ብለዋል::

*ፍኖት መብዕስ (ያልቀና መንገድ)*

---

[14] "ማለኮትን ወደ ማካፈል አንገባም:: መንግሥትንም አንከፍልም

አንድ ማለኮት አንድ መንግሥት እንላለን እንጅ በማለኮት አንድ

ናቸው በአካል ሦስት ናቸው" ማለት ነው:: (ሃይማኖተ አበው)

[15] "ፍጹም ሦስትን፣ በአንድ ማለኮት፣ እስከ ዘለዓለም አንድ ጌታ፣ አንዲት መንግሥት፣ የማትከፈል እና የማትፋለስ" ማለት ነው። (ሃ. አበው)

ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት የማለት ትምህርትም አንድ መለኮት በሦስት አካላት ሕልው ሆኖ ሦስቱን አካላት ያገናዝባል በማለት የቀና ይሁን የተካከለም::

*ማስረጃ ንባብ*:- ዮሐንስ ዘአንጾኪያ

"ወበሠለስቲሆሙ ሀሎ ፩ መለኮት"[16] ብሎአል::

"ይርአይ ኲሉ ዘነፍስ" በነፍስ ዕውቀት ፀዋቂ ሆኖ የሚኖር ሁሉ ወንጌላዊት ሃይማኖትን ለመግለጽ እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት በሊቃውንት በየአንቀጹ ያናገረው የአካላትን ሦስትነት፣ የመለኮትንና የመንግሥትንም አንድነት የሚያስረዳውን ኃይለ ቃል "ፍኖተ እግዚአብሔር" በተባለች በዚች ትንሽ መጽሐፍ ለተመልካች በቅርብ እንዲገኝለት በመደረጉ፣ በቅን ኅሊና የሚመለከታት ከብዙ ስሕተት መዳኑን ይወቅ:: ተመልካችዋም ቃሏን ተመልክቶ ተቀብሎ ከስሕተት የሚድንበትንና የዘለዓለም ድኅነት የሚያገኝበት ጊዜ እነሆ ከሞት በፊት ዛሬ ነው::

*ማስረጃ*:- ቅዱስ ዳውሎስ

"በዕለት ኅሪት ሰማዕኩከ ወበዕለተ መድኅኒት ረዳዕኩከ"[17] ያለውን የኢሳይያስን ትንቢት ከጠቀሰበት:: ኢሳ ፵፱፥፰

*ንባብ*:- "ወናሁ ይእዜ ዕለት ኅሪት፣ ወናሁ ዮም ዕለተ አድኅኖት"

*ትርጓሜ*:- "የተመረጠች ቀን ድኅነት የሚገኝባትም ጊዜ ዛሬ

[16] "በሦስቱ አንድ መለኮት አለ" ማለት ነው:: (ሃ. አበው)

[17] "በተመረጠች ቃል ሰማሁህ በዕለተ ድኅነት እረዳሁህ" ማለት ነው::

ናት'' እንዳለ:: ፪ኛ ቆሮ ፲፥፪

የዘለዓለም ድኅነት የተባለችም፣ ዕሪናቸው በአካል፣ መመሳሰላቸው በኀብረ መልክዕ፣ ህልውናቸው በኩልነት፣ ተዋሕዶዋቸው በመለኮት የሚነገር ሥላሴ፣ በአብ ልብነት ለባውያን፣ በወልድ ቃልነት ነባብያን፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያዋን መሆናቸውን አውቆ ተረድቶ አንድ የባሕርይ አምለክ ብሎ ማመን ናት::

ማስረጃ:- ባለቤቱ ጌታችን

ንባብ:- "አባ በጽሐ ጊዜሁ ከመትሰብሆ ለወልድከ፣ ወከመ ወልድከኒ ይሰብሕከ፣ በከመ አኮንኮ ላዕለ ኩሉ ዘሥጋ ወነፍስ ከመ የሀቦሙ ሕይወተ ዘለዓለም ለኩሎሙ እለ ወሀብካሁ ወዛቲ ይእቲ ሕይወት ዘለዓለም ከመ ያእምሩከ ለከ ለአሐዱ ዘበአማን አምላከ ወለዘፈነውኮ ኢየሱስ ክርስቶስ'' ብሎአል::

ትርጓሜ :- "አባት ሆይ ልጅህን ትገልጸው ዘንድ፣ ልጅህም አንተን ይገልጽህ ዘንድ፣ የምትገልጽበት ጊዜውም ደረሰ፣ ለሰጠኸው ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ፣ በሥጋዊና በነፍሳዊ ሁሉ ላይ እንዳሠለጠንኸው መጠን፣ የዘለዓለም ሕይወት ይች ናት:: ያውቁህ ዘንድ አንተ ብቻህ /እውነተኛ/ የባሕርይ አምላክ እንደሆንህ የላከኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን'' ብሏልና:: ዮሐ ፲፯፥፩-፫

የባሕርይ አምላክ እንደሆነም የሚያውቁበትን ዕውቀት የሚገልጽ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስረዳ:-

ንባብ:- "ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ ዘይፌኑ አብ በስምየ፣ ውእቱ ይሜረክሙ ኩሎ፣ ወያዜክረክሙ ኩሎ ዘነገርኩክሙ አነ"

ትርጓሜ:- “አብ በእኔ ስም የሚሰድላችሁ የሚያፅና መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምራችኋል ይገልጽላችኋል/ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል'' ብሏል:: ዮሐ ፲፬፥፳

በማቴዎስ ወንጌልም:-

ንባብ:- “እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ እለ ትትናገሩ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ውእቱ ይትናገር በላዕሌክሙ”

ትርጓሜ:- “እናንተ የምትናገሩ አይደላችሁም ያባታችሁ መንፈስ በእናንተ አድሮ ይናገራል እንጂ'' ብሏል:: ማቴ ፲፥፳

ጳውሎስም:-

ንባብ ፡- “ወአልቦ ዘይክል ብሂለ እግዚእ ኢየሱስ ዘእንበለ ዘመንፈስ ቅዱስ ላዕሌሁ”

ትርጓሜ:- “መንፈስ ቅዱስ ካደረበት ሰው በቀር ኢየሱስ የባሕርይ አምላክ ነው የሚል የለም” ብሏል:: ፩ኛ ቆሮ ፲፪፥፫

ነገር ግን የበጎ ሃይማኖት የምሥጢሩን ፍለጋ ለሚከታተል ሰው በቅዱሳት መጻሕፍትና በሊቃውንት የተጻፈውን በጎ ትምህርት ይዞ ምሥጢሩን እንዲገልጽለት የአምላክ መሆን ይገባዋል እንጂ የመጻሕፈት ንባባቸውንና ምሥጢራቸውን አፍርሶ ስህተትን ሲያንጽ፣ አስተዋይ ልቦና ለሌላቸው ሰዎች የቀና መስሎ ወደሚታይ ክፉ ጠማማ ሃይማኖት በመሳብ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን አይገባም::

ማስረጃ:- ሐዋርያው ጳውሎስ:-

ንባብ፡- “ወኢታምዕዎ ለመንፈስ ቅዱስ ዘቦቱ ዐተቡክሙ አመ

ድኅንክሙ''

ትርጓሜ:- "ከክህደት በዳናችሁ ጊዜ የታተማችሁበትን መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑት" እንዳለ:: ኤፌ ፬:-፴ የሰው ኅሊናው ወደ በጎ ሃይማኖት ሳያስብ የሃይማኖት ምሥጢርን በመግለጽ የእግዚአብሔር ፀጋ ሰውን አትረዳውምና::

ማስረጃ:- ፊልክስዩስ "እምቅድመ ትጽንን ኅሊናሁ ለስብእ ለኂሩት ወለእከይ፣ ኢትረድኦ ወኢትርሕቅ እምኔሁ'' እንዳለ:: /ክፍል ፪ ተስእሎ ፲፬/

ትርጉም:- "ወደ በጎና ወደ ክፉ ሳይጸን በመካከል ሳለ /ፈዞ ማለት ነው/ አትረዳውም አትርቀውም" ብሎአል:: ስለዚህ አምላካዊ የሆነ የሃይማኖትን ምሥጢር ለመረዳት

አምላካችን ወደ በጎ ሃይማኖት የሚሳብ በጎ ኅሊናን ይስጠን አሜን::

## *ፍኖተ እግዚአብሔር*

### *፭ኛ አንቀጽ*

### *ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት ማለት እንዳይገባ ይናገራል*

ጥያቄ፡- ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት ማለት አይገባምን?

መልስ፡- ምንም ቢሆን ወላዲው፣ ተወላዲ ሠራጺ፣ ተወላዲውም፣ ወላዲ ሠራጺ፣ ሠራጺውም፣ ወላዲ ተወላዲ ሊሆን የማይችል ነው:: አካላትን ቅሉ፣ ልዩ ልዩ የሚያሰኛቸው ይህ ወላዲ፣ ተወለዲ፣ ሠራጺ የሚለው ንባብ ነው:: መለኮትን አካላት በሚለያዩበት ስም ጠርቶ ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሠራጺ መለኮት ማለት መለኮትን እንደ አካላት ሦስት ማለት እንደሆነ አስተዋይ ልቦና ይረዳዋል:: እንዲህም ከሆነ ሊቃውንት በየአንቀጹ “ይሤለሱ በአካላት፣ ወይትወሐዱ በመለኮት'' ያሉት ንባብ ሐሰት ሆነ ማለት ነዋ:: መለኮት በራሱ ወላዲ፣ ተወላዲ፣ ሠራጺ ከተባለ፣ ሦስት በመሆኑ የመንገዱ ጥርጊያ ወደ ዮሐንስ ተዐቃቢ ቤት የሚያገባ መሆኑ አይጠረጠርም:: መለኮትን ወላዲ፣ ተወለዲ፣ ሠራጺ ማለትም፣ ሦስቱ አካላት መለኮት፣ መለኮት፣ መለኮት፣ የተባሉበትን ምሥጢር ባለማስተዋል የታሰበ ስሕተት ነው:: ሊቃውንት ሦስቱን አካላት መለኮት፣ መለኮት፣ መለኮት፣ ብለው ማመናቸው መለኮት በአካል ልዩ ነው ብለው አይደለም:: አንድ መለኮት በሦስት አካላት ልዩ ነው ብለው

አይደለም:: አንድ መለኮት በሦስት አካላት ህልው ነው ብለው ነው እንጂ::

<u>ማስረጃ</u>፡- ፳፯ኛ ሊቅ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት:-

<u>ንባብ</u>፡- “ወኢይትህበሉ ሕጉላን ያብኡ ውስተ ቅድስት ሥላሴ ፍልጠተ መለኮት፣ ወኢድማሬ አካላት፣ ወኢንሰግድ ለ፫ቱ አማልክት፣ አላ ለ፩ አምላክ:: ወንሰምዮሙ በ፫ አስማት፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፣ ፩ መለኮት፣ ወ ፩ ኃይል፣ እንዘ ፫ አካላት እኁዛን በጽምረተ ፩ መለኮት ወህላዌ”

<u>ትርጓሜ</u>፡- "ከዕውቀት የተሳሳቱ ሰዎች ልዩ በሆነች ሦስትነት፣ የመለኮትን ልዩነት፣ የአካላትን አንድነት አግብተው ይናገሩ ዘንድ አይድፈሩ፣ ለአንድ አምላክ እንሰግዳለን እንጂ ፣ለሦስት አማልክት አንሰግድምና፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ብለን በሦስት ስሞች እንጠራቸዋለን:: እኒህም ሦስቱ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ባንድ መለኮትና/ሕይወት/ በአንድ ሕልውና አንድነት የተገናዘቡ ሦስት ሲሆኑ፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ ኃይል ናቸው" ብሏልና:: (ድርሳን ፩ ሃይማኖተ አበው)[18]

ባስልዮስ ዘአንጾኪያም ፵፩ኛ:-

<u>ንባብ</u>፡- “እንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር፣ ዕብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ እስመ አሐዱ ውእቱ መለኮተ ሥላሴ፣ ወሠለስቲሆሙ አሐዱ እሙንቱ በመለኮት፣ ወእሙነ እብል ከመ እሙንቱ መለኮት ወህላዌ፣ ወለለ አሐዱ እምአካላተ ሠላሴ፣ ያበጽሕ

[18] ከታተመውሃይማኖተ አበው ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ምዕ ፳፥ ፮–፯ ይመልከቱ

ፍጹመ መለኮት፣ ምስለ ዚአሁ አካል ወስም'' (ክፍል ፩ ሃይማኖተ አበው) [19]

<u>ትርጓሜ</u>፡- "እኔ እግዚአብሔር ባልሁ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ማለትን ስለ አብ፣ ስለ ወልድ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ:: የሦስቱ መለኮት አንድ ነውና:: ሦስቱም በመለኮት አንድ ናቸው:: እኒህም መለኮትና/ሕይወት/ ሕልውና/ባሕርይ/ እንዲባሉ በእውነት እናገራለሁ:: ልዩ ሦስትነት ካላቸው አካላትም፣ አንዱም አንዱም ከገንዘቡ አካልና ከገንዘቡ ስም ጋራ ፍጹም መለኮትን ገንዘብ ያደርጋሉ" ብሏል::

፫ኛው ሊቅ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያም:-

<u>ንባብ</u>፡- “እሉ ሠለስቱ አካላት ፍጹማን ዲበ መንበረ ስብሐት፣ ወእኁዛን በፅምረተ አሐዱ መለኮት፣ ዘውእቱ አሐዱ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ሥላሴ”

<u>ትርጓሜ</u>፡- “እኒህ ሦስቱ አካላት በጌትነት ዙፋን ላይ ያሉ ፍጹማን ናቸው:: በአንዱ መለኮት አንድ አድራጊነትም የተገናዘቡ ናቸው:: ይህም መለኮት/ባሕርይ/ የአካል ሦስትነት ከሱ የሚገኝለት አንድ ብርሃን ነው” ብሏል:: (ክፍል ፩ ሃይማኖተ አበው) [20]

አቡሊዲስ ዘሮምም.፲፫ ሊቅ:-

<u>ንባብ</u>፡- “ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ መንፈሶሙ ለአብ ወወልድ፣ ወበዝንቱ አእምርነ ከመ ፩መለኮተ ሥላሴ፣ ወሎቱ ንሰግድ፣ ወአበዊነሂ እለተጋብኡ በኒቅያ

---

[19] ዝኒ ከማሁ ሃይማኖተ አበው ም፴ ፷፮፥ ፮–፯

[20] ከታተመው ሃይማኖተ አበው ም፴ ፲፩፥ ፳–፱ ይመልከቱ

ይቤሉ እመቦ ዘይፈልጥ መለኮቶ ለእግዚአብሔር አብ እምወልድ ወእም መንፈስ ቅዱስ ውጉዘ ለይኩን::"

ትርጓሜ፡- "ወልድ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው:: በዚህም የምንሰግድለት የሦስቱ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ እንደሆነ አወቅን:: በኒቅያ የተሰበሰቡ አባቶቻችንም የአብን መለኮት ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ የሚለይ ሰው ቢኖር የተለየ ይሁን ብለዋል" ብሏል:: (ክፍል ፳ ሃይማኖተ አበው)[21] ይህን የመሰለ በየአንቀጹ የተነገረ ብዙ ነው::

*ሐተታ*

ሦስቱ መለኮት፣ መለኮት፣ መለኮት መባላቸው አንድ መለኮት በሦስቱ አካላት ሕልው ሆኖ፣ ሦስቱን አካላት ስለአገናዘበ ነው እንጂ መለኮት በአካል የተለየ ሆኖ እንዳይደለ አስተዋይ ልቦና ያለው ሰው መጻሕፍትን በጥንቃቄ ቢመረምር ይረዳዋል:: መለኮት በአካል የተለየ ቢሆን፣ ሦስቱ ሁሉ ባልተጠሩበትም ነበር:: አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ መባል ግን፣ በአካል የተለየ ቢሆን በየራሳቸው ተጠሩበት እንጂ ሦስቱ ሁሉ እንዳልተጠሩበት።

[21] ዝኒ ከማሁ ሃይማኖተ አበው ምዕ ፴፱፥፳–፱

*፪ኛ አንቀጽ*

*በአንድ መለኮት ሦስት ኩነት እንዳለ፣ የኩነትም ሦስትነቱ፣ እንደ አካላት እንዳይደለ፣ ይናገራል*

ጥያቄ፡- መለኮትን በአካል ሦስት ብሎ መለኮት የተባለ አካል ነው ማለት ይገባልን?

መልስ:- አይገባም፤ መለኮትን አካል ብሎ፣ አካል ለአካል ሦስት ማለት፣ ዘጠኝ አካላት ከማለት የሚያደርስ መሆኑ አይጠረጠርምና።

ጥያቄ፡- መለኮትን በአካል ሦስት ማለት ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ ከማለት አይጠብቅምን?

መልስ፡- አዎን አይጠብቅም፤ ሦስት አማልክት ዘጠኝ አካላት ያሰኛል እንጅ፤ ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ ከማለት የሚጠብቅስ በአንድ መለኮት ሦስት አካላትና ሦስት ኩነታት እንዳሉ ማመን ነው።

ማስረጃ፡ ሠለስቱ ምዕት፡-

ንባብ፡- "በስመ እግዚአብሔር ዋሕድ በመለኮት ዘይሴለስ በአካላት ወኩነታት"

ትርጉም፡- "በመለኮት አንድ፣ በአካላትና በኩነታት ሦስት፣ በሚሆን በእግዚአብሔር ስም እናምናለን” እንዳሉ። /መጽሐፈ ሥርዓት ፩ኛ አንቀጽ/ እንዲህ ግን ስለሆነ የኩነታት ሦስትነት እንደ አካላት አይደለም፤ አካላት መጠቅለልና መቀላቀል ሳይኖርባቸው፣ በተከፍሎ በተፈልጦ፣ በፍጹም ገጽ፣ በፍጹም መልክ፣ በየራሳቸው የሚቆሙ ናቸው፤ ኩነታት ግን ተፈልጦ ተከፍሎ /መለየት መከፈል/ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶና በተጋብኦ በአንድነት አካላትን በሕልውና /በአኗኗር/ እያገናዘቡ፣ በአንድ መለኮት የነበሩ፣ ያሉ፣ የሚኖሩ ናቸው፤ እሊህም ከዊነ አብ፣ ከዊነ ቃል፣ ከዊነ እስትንፋስ ናቸው። “ከዊነ አብ” በአብ መሠረትነት እራሱ ለባዊ ሆኖ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት /ማወቂያ/ መሆን ነው። “ከዊነ ቃል” በአብ መሠረትነት ለራሱ ነባቢ ሆኖ፤ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ /ማናገሪያ/ መሆን ነው። “ከዊነ እስትንፋስ” በአብ መሠረትነት ለራሱ ሕያው ሆኖ፣ ለአብና ለወልድ ሕይወት መሆን ነው። ሦስት ኩነታት ያልናቸው እሊህ ናቸው። የሊህም ኩነታት ምሥጢር፣ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" [22] ያለውን ንባብ /ዘፍ ፩፥፳፮/ መሠረት አድርጎ፣ የነፍስን የአካሏንና የባሕርይዋን ከዊን ቢመረምሩ ይታወቃል ይረዳልም። ሲመረመርም የባሕርያቸው ከዊን በአካሏ ከዊን፤ የአካለቸውም ከዊን፣ በባሕርይዋ ከዊን፣ ይመረምረዋል፣ ነፍስ በአካሏ፣ ከሦስት የማትከፈል ከዊን አላት። ይኸውም ከዊነ ልብ፥ ከዊነ ቃል፥ ከዊነ እስትንፋስ ነው:: በባሕርይዋ ሦስት ከዊን ያላት መሆንዋ፤ አካሏን ከሦስት አይከፍለውም:: እንዲህ ሳትከፈል፣ የልብነትዋ ከዊን /ልብ መሆንዋ/ ከቃሏና ከእስትንፋሷ ከዊን ሳይለይ፣ በራስዋ ከዊን ከሥጋዊ ልብ ጋር ይዋሐዳል። በቃልነትዋም ከዊን /የቃሏም ከዊን/ ከልብነትዋ ከዊንና ከእስትንፋስዋ ከዊን ሳይለይ፤ በራሱ ከዊን ከሥጋ አንደበት ጋራ ይዋሐዳል:: የእስትንፋሷም ከዊን

[22] "ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር"

ከልብነትዋ ከዊንና ከቃልዋም ከዊን ሳይለይ፣ በራሱ ከዊን ከሥጋ እስትንፋስ ጋር ይዋሐዳል:: እንዲህ አድርጎ የሥላሴን ከዊን በነፍስ ከዊን ቢመረምሩ፣ ሦስቱ ሰው ሆኑ ከማለት ይጠብቃል::

መለኮትን በአካል ሦስት ማለት ግን፤ ሊቃውንት ሁሉ በየአንቀጹ፣ "ይሤለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት"[23] ያሉትን አፍርሶ፣ ሦስት አማልክት፣ ዘጠኝ አካላት፥ ከማለት ያደርሳል እንጅ፣ ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ ከማለት የሚጠብቅ አይደለም።

*ክፍል ፭*

ዳግመኛም ይኸው በነፍስ ከዊን የተገለጠው የሥላሴ ከዊን፥ በእሳትና በፀሐይ በቀላይም ከዊን ይገለጣል:: እሳት አንድ ባሕርይ ሲሆን፣ ሦስት ከዊን አለው።

ይኸውም ነበልባል፤ብርሃን፤ ዋዕይ ነው:: በነበልባሉ አብ፥ በብርሃኑ ወልድ፥ በዋዕዩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ:: ይኸውም ተፈልጦ ተከፍሎ ሳይኖርበት፣ በአንድ ሕላዌ የሚኖር ነው::

<u>አናዋሩ</u>፦ ነበልባሉ ከእንጨት ወይም ከፈትልና ከዘይት ጋራ ብርሃኑንና ሙቀቱን ይሰጣል:: ብርሃን ከነበልባልና ከዋዕይ ተከፍሎ ሳይኖርበት፣ በራሱ ከዊን ከዓይን ብርሃን ጋራ ይዋሐዳል:: እንደዚሁም ወልድ በቃልነቱ ከዊን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ፣ በተለየ አካሉ ሰው ሆነ:: ብርሃነ እሳት ከዓይን ጋራ በተዋሐደ ጊዜ፣ ነበልባልና ዋዕይ እንዳልተዋሐዱ፣ ወልድም ሰው በሆነ ጊዜ፣ መለኮት አንድ ስለሆነ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ተዋሐዱ አያሰኝም፤ ባሕርይ አንድ ሲሆን ከዊን

---

23 "በአካል ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ናቸው" (ሃ. አበው)

ይለየዋልና:: ይህንም የሚያስረዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንዋርህ እንዴት ነው ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ቢጠይቀው፣

ንባብ፡- “አቡየ እሳት ውእቱ ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስ ቅዱስ

ዋዕዩ’’

ትርጉም፡- “አባቴ እሳት/ነበልባል/ ነው፣ እኔ ብርሃን ነኝ፣ መንፈስ ቅዱስም ዋዕዩ /ሙቀቱ/ ነው'' ብሎ የአንድነቱንና የሦስትነቱን አኗኗዋር በእሳት መስሎ ነግሮታል:: /ቀሌምንጦስ/

ሠለስቱ ምዕትም:-

ንባብ፡- “አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ፣ እሳት ወነበልባል፣ ወፉሕም” አለ ጌታ ብለዋል::

ቅዳሴ አባ ሕርያቆስም:-

ንባብ፡- “አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም" ብሏል። (ቅዳሴ ማርያም)

በልዕልና ያለ አንድ የሕይወት እሳት ማለቱ ነው:: ፀሐይም አንድ ባሕርይ ሲሆን ሦስት ከዊን አለው:: ይኸውም ክበብ፣ ብርሃን፣ ዋዕይ ነው:: በክበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በዋዕዩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ:: ብርሃነ ፀሐይ ከክበቡና ከዋዕዩ ተፈልጦ ተከፍሎ ሳይኖርበት፣ በራሱ ከዊን ከዓይን ብርሃን ጋራ ይዋሐዳል:: እንዲሁም ወልድ በቃልነቱ ከዊን፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ፣ በተለየ አካሉ ሰው ሆነ:: ብርሃነ ፀሐይ ከዓይን ጋራ በተዋሐደ ጊዜ፣ ክበብና ዋዕዩ እንዳይዋሐዱ፣ ወልድ ሰው በሆነ ጊዜም መለኮት አንድ ስለሆነ፣ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ አያሰኝም::

ማስረጃ፦ ባለቤቱ ጌታችን ክርስቶስ በቀሌምንጦስ:-

ንባብ፦ “አቡየ ፀሐይ፣ ወአነ ብርሃኑ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ::"

ትርጉም፦ “አባቴ ፀሐይ ነው፣ እኔም ብርሃኑ ነኝ፣ መንፈስ ቅዱስም ዋዕየ ነው'' እንዳለ::

ሠለስቱ ምዕትም:-

ንባብ፦ “አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሐይ/ክበብ/ ወብርሃን፣ ወዋዕዩ/ሙቀት/ '' ብለዋል ::

ቅዳሴ አባ ሕርያቆስም:-

ንባብ፦ “አብ ፀሐይ ወልድ ፀሐይ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሐይ አሐዱ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘላዕለ ኲሉ'' ብሏል:: /ቅዳሴ/

ከሁሉ በላይ የሚሆን አንድ ፀሐየ ጽድቅ ማለት ነው::ባሕርም፣ አንድ ባሕር ሲሆን ሦስት ከዊን አለው:: ይኸውም ስፋት፣ ርጥበት፣ ሁከት ነው:: በስፋቱ አብ፣ በርጥበቱ ወልድ፣ በሁከቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ:: ሰው ከባሕር ገብቶ ዋኝቶ ሲወጣ ፣ በአካሉ ላይ ርጥበት ይገኛል እንጂ ፣ ስፋትና ሁከት እንዳይገኙ፣ ወልድም በቃልነቱ ከዊን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ፣ በተለየ አካሉ ሰው በሆነ ጊዜ፣ በመለኮት አንድ ስለሆነ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ አያሰኝም:: የዚህንም ምሳሌነቱ በአረጋዊ መንፈሳዊ እንደተነገረ፣ በአሥራ አንደኛው አንቀጽ እናመጣዋለን:: ይህን ሁሉ ተመልክተን መለኮት በአካል ሦስት ከማለት ርቀን፣ በአንድ መለኮት ሦስት አካላትና ሦስት ኩነታት እንዳሉ አምነን፣ ወልድ በተለየ አካሉ ከአንድ መለኮት ተፈልጦ ስሌለበት በቃልነቱ ከዊን ሰው ሆነ ብለን ብናምን ሦስቱ ሰው

ሆኑ እንዳያሰኝ የሚያስረዳ ነገር፣ ፭ኛ ሊቅ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት አግናጥዮስ እንደሚከተለው ተናግሯዋል::

<u>ንባብ</u>፡- "ኀደረ አሐዱ አካል እም ሠለስቱ አካላት ውስተ ከርሣ ለድንግል ማርያም:: ወበእንተ ተዋሕዶተ መለኮት ዘንትናገር በዝየ፣ ዘህልው በወልድ፣ ወአኮ በእንተ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወኢንቤ ግሙራ ከመ እሙንቱ ኀደሩ ለተሰብኦ ውስተ ከርሣ ለድንግል፣ ዘእንበለ ዳእሙ ወልድ ባሕቲቱ አሐዱ አካል እም ሠለስቱ አካላት::"

<u>ትርጉም</u>፡- "ሦስቱ አካለት አንዱ አካል በማኅጸነ ማርያም አደረ:: በዚህ አንቀጽ ኀደረ ብለን የምንናገረው የመለኮት ተዋሕዶ፣ በወልድ በቃልነቱ ስላለው ከዊን አይደለም፣ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ብቻ ሰው ለመሆኑ በማኅጸነ ድንግል አደረ እንላለን እንጂ፣ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው በመሆን አደሩ አንልምና" ብሏል:: (አንደኛ መልዕክት ሃይማኖተ አበው)[24]

መለኮት ዘሕልው በወልድ ያለው፣ የወልድ የቃልነቱ ከዊን እንድሆነ እዝነ ልቦና ያለው ሰው በቅጥነተ ልብ ሆኖ ያስተውል::

*ክፍል ፪*

*የመለኮት አንድነት አካላትን እንዳይጠቀልል፣ የአካላትም ሦስትነት መለኮትን እንዳይከፍል የሚያስረዳ ነገር*

የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ ፵፱ኛ እንዲህ ሲል

ተናገረ፡-

<u>ንባብ</u>፡- "ወሶበሂ ንቤ አሐዱ እግዚአብሔር፣ ወ፩ዱ ሕላዌ፣ ወ ፩ዱ መለኮት፣ አኮ ዘያበጥል ላዕሌነ ዝንቱ ተስምዮተ ፫ አካላት:: እስመ

---

[24] ሃይማኖት አበው ምዕራፍ ፲፩፥፫

ለለ፩ እም ፫ አካላት ሃላውያን በበአካላቲሆሙ:: ወመለኮትሂ ሕልው በሕላዌሁ፣ ወኢይትፈለጥ ለከዊነ ፫ መለኮት፣ እስመ ቅድስት ሥላሴ ፩ እሙንቱ በተዋሕዶ እንበለ ፍልጠት” [25]

<u>ትርጓሜ</u>፡- "አንድ እግዚአብሔር አንድ ሕላዌ አንድ መለኮት ብንል፣ አንድ ማለታችን ፫ አካላት ማለትን የሚፈርስብን አይደለም:: ሦስት አካላት ማለታችንም መለኮትን ከሦስት የሚከፍልብን አይደለም:: ከሦስቱም አካላት አንዱም አንዱ በየአካላቸው ፀንተው የሚኖሩ ናቸውና፣ መለኮትም በአንድነቱ ፀንቶ የሚኖር ነው እንጂ:: ሦስት መለኮት ለመሆን የሚከፈል አይደለም፣ ቅድስት ሥላሴ ያለመለያየት በተዋሕዶ አንድ ናቸውና" ብሏል:: (ሃይ. አበው፣ እመልዕክተ ሲኖዲቆስ ፴፪ኛ ክፍል ፩)። የእንስክድሪያ ሊቀ ጳጳሳት ሱንትዮስም ይህን የአትናቴዎስን ቃል በሙሉ ተናግሮታል፤[26]

፴፫ኛ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳትም- ዲዮናስዮስ:-

<u>ንባብ</u>፡- "ወንትአመን በዝንቱ ሕላዌ ወንሰግድ አሐተ ስግድተ እስመ መለኮትሰ ፩ ውእቱ ዘሠለስቲሆሙ::  ወሠለስቲሆሙ: ፩ዱ እሙንቱ በመለኮት፤ ወዝንቱ የአክል ለዘቦቱ ልብ ወአእምሮ፤ ይትዋሐዱ በመለኮት ወይሤለሱ በአካላት:: በከመ ይቤ ጎርጎርዩስ ነባቤ መለኮት፣ እስመ መለኮትሰ አኮ ውፁዕ እም ፫ አካላት ከመ ኢይባእ ተጋብኦተ አማልክት ወኢነ አምን ካልአ እምዝንቱ ወኢንበል ፫ተ አማልክተ ወኢመለኮት ፍሉጠ:: ወእመሰ ንቤ ፍሉጥ መለኮት፣ንከውን ዐላውያነ ወናመጽእ ድካመ ለመለኮት:: ወሶበሂ ንሬሲ ቅድስተ ሥላሴ ፍሉጣነ መለኮት፣በከመ አካላቲሆሙ፣ ንትአመን እምነተ ሰይጣናዌ ከመ አይሁድ እለ አልበሙ አምላከ”

---

[25] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፸፮፥፳–፱

[26] እሜልዕክተ ሲኖዲቆን ሃይማኖተ አበው ምዕ ፸፩

ትርጉም፡- “በዚህ ባሕርይ እናምናለን አንዲት ስግደትም እንሰግዳለን:: የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ ነውና:: ሦስቱም በመለኮት አንድ ናቸውና:: ዕውቀትና አእምሮ ላለው በመለኮት አንድ በአካል ሦስት ናቸው ብሎ ማመን ይበቃል:: የመለኮትን ነገር የሚናገር ጎርጎርዮስ በመለኮት አንድ በአካል ሦስት ናቸው ብሎ እንደተናገረ መለኮትስ ከሦስቱ አካላት የወጣ ልዩ አይደለም:: ብዙ አማልክት አሉ ማለት በሰው ልቦና እንዳያድር ከዚህ ሌላ አናምንም:: ሦስት አማልክት አንልም:: መለኮትንም ልዩ ነው አንልም:: መለኮትን እንደ አካላት ልዩ ነው ብንል ግን ከሐድያን እንሆናለን:: በመለኮትም ድካምን እናመጣለን:: ቅድስት ሥላሴን እንደ አካላቸው በመለኮት ልዩ ብናደርግ፣ አምላክ የለም እንደሚሉ እንደ አይሁድ ከሰይጣን የተገኘ እምነትን እናምናለን” ብሏል:: /እመልእክተ ሲኖዲቆን/

፶፬ኛ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ክርስቶዶሉም አትናቴዎስና ሱኑትዩስ የተናገሩትን ንባብ ተናግሮታል:: እመልክተ ሲኖዲቆን። ይህን የመሰለ የተናገሩ ሊቃውንት ብዙ ናቸው:: በየአንቀጹ መመልከት ነው::

## ፫ኛ አንቀጽ

ሥላሴ በመለኮት አንድ የሚሆንበትን ምሥጢር ያሳያል

ሐተታ- ሥላሴ በመለኮት አንድ መባላቸው በብዕል አንዱ ከአንዱ ሳይበልጥ አንዱም ከአንዱ ሳያንስ የሚተካከሉ ባለጸጎች፣ ብዕላቸው በየቤታቸው ሳለ በመተካከላቸው አንድ እንዲባሉ መለኮታቸው በየአካላቸው ሳለ በክብር ስለተካከሉበት ነው ማለት ይገባናልን?

መልስ፡- አይገባም:: ሥላሴ በመለኮት አንድ መባላቸውስ፣ መለኮት እንደ አካላት ተከፍሎ ሳይኖርበት፣ በአንድነቱ ፀንቶ፣ አካላትን በተከፍሎ ሳሉ በሕልውና እያገናዘበ፣ አንድ ልብ፣ አንድ ቃል፣ አንድ እስትንፋስ ስላደረጋቸው ነው እንጂ በክብር ስላስተካከላቸው አይደለም:: መለኮት ከአካል ጋር ከሦስት የሚከፈልስ ከሆነ አንድ ልብ፣ አንድ ቃል፣ አንድ እስትንፋስ መሆን የለም:: ይህም ከሌለ በአብ ለባውያን፣ በወልድ ነባብያን፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን መባል አይገኝም::

እንዲህም ከሆነ በአንደኛው አንቀጽ የተጠቀሰው አቡሊድስ:-

ንባብ፡- “ወልድኒ ቃሉሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስኒ መንፈሶሙ ለአብ ወለወልድ"[27] ያለው ሐሰት ሆኖ በየራሳቸው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ አላቸው በማለት እንደ ዮሐንስ ተዐቃቢ ዘጠኝ

[27] "ወልድም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው (ሕይወታቸው) ነው" ሃ. አበው

መለኮት ያሰኛል:: ዮሐንስ ተዐቃቢ ከዚህ ሌላ አልተናገረምና:: ሕልውናም እንዲያገናዝባቸው:: [28]

ማስረጃ፡- ባለቤቱ ጌታችን:-

ንባብ፡- "ለግብርየ እመኑ ከመ ታእምሩ ወትጠይቁ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ::''

ትርጉም፡- ''በሥራዬ እመኑ ታውቁ ትረዱም ዘንድ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ'' ብሏልና:: ዮሐ ፲፥፴፰

ንባብ፡- ዳግመኛ "ኢተአምንሁ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ፣ ወዝኒ ቃል ዘአነ ነገርኩክሙ አኮ ዘ   እምኀቤየ ዘነበብኩ አላ አብ ዘሀሎ ብየ ውእቱ ይገብሮ ለዝንቱ ግብር"

ትርጉም፡- "አታምንምን እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ:: ይህ ለእናንተ የምነግራችሁ ነገር ከኔ ከራሴ የተናገርኩት አይደለም:: በእኔ ያለ እርሱ አብ ይህን ሥራ ይሠራዋል እንጂ" ብሎ ለፊልጶስ ነግሮታል:: ዮሐ ፲፬፥፲

ዮሐንስ ዘአንጾኪያም ፵፫ኛ:-

ንባብ፡- "አንኮ ዘንተአመን በ፫ እደው በ፫ አማልክት ወኢ በ፫ መለኮት አላ ንትአመን በ፫ አካላት ወበ፫ ገጻት እንተ ፩ ባሕርየ መለኮት"

[28] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፫፱፥፰-፱

ትርጉም፡- "መገናዘብ እንደሌላቸው እንደ ፫ ሰዎች አድርገን በሦስት ሰዎች፣ በሦስት አማልክት፣ በሦስት መለኮት የምናምን አይደለንም:: ባሕርየ መለኮት አንድ በሚያደርጋቸው በሦስት አካላት በሦስት ገጻት እናምናለን እንጂ'' ብሏል:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፩)[29]

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ:-

ንባብ፡- “ንሕነ ንትአመን ከመ አብ ሕልው በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድኒ ሕልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወመንፈስ ቅዱስኒ ሕልው በአብ ወወልድ''

ትርጉም፡- “አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሕልው እንደሆነ፣ ወልድ በአብና በመንፈስ ቅዱስ ሕልው እንደሆነ፣ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ሕልው እንደሆነ እኛ እናምናለን'' ብሏል:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፯)[30]

ዲዮናስዮስም መለኮትን እንደ አካላት ብንለይ፣ ሰይጣናዊ እምነትን እናምናለን ማለቱ፣ መለኮትን ሦስት ብሎ፣ ሦስትነት ያለው አኃዝ በመለኮት ከተነገረ፣ መንገዱ የዮሐንስ ተዐቃቢ ነውና እምነቱ ሰይጣናዊ መሆኑን ሲያስረዳ ነው:: መጻሕፍት ሁሉ “ይትወሐዱ በመለኮት” እያሉ፣ ለአካላት ማስረጃ ያደርጉታል እንጂ መለኮትን ሦስት ብለው የሚከፍሉበት አንቀጽ አይገኝም:: ስለዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መጻሕፍት ከተናገሩት ትምህርት ሳይወጡ ማመን ይገባል:: በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መጻሐፍትን በድፍረትና በትዕቢት ሳይሆን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በትሕትና ሆኖ የሚመለከታቸውን በአካል ሦስት፣ በመለኮት አንድ የሚያሰኘውን የሃይማኖት ምስጢር በመግለጽ ይጠቅማሉና::

[29] ሃይ. አበው ምዕ ፻፲፬፥፮–፯
[30] ሃይ. አበው ምዕ ፺፥፲፩

ማስረጃ፡- ቅዱስ ጳውሎስ:-

<u>ንባብ</u>፡- “ወኲሉ መጽሐፍ ዘበመንፈሰ እግዚአብሔር ተጽሕፈ ይበቁዕ በኲሉ ትምህርት ወተግሣጽ ወአርትኦ ወአጥብቦ ወጽድቅ፣ ከመ ይትገሠጽ ብእሴ እግዚአብሔር ውስተ ኲሉ ምግባረ ሠናይ::''

<u>ትርጉም</u>፡- “በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ ሁሉ፣ ፍፁም ትምህርትንና ምክርን በመሆን፣ ልቦናን በማቅናትና በማራቀቅ ጽድቅንም በማሠራት ይረባል ይጠቅማል፣ የእግዚአብሔር ሰው በጎ ሥራን ሁሉ ይማር ዘንድ'' እንዳለ:: ፪ኛ ጢሞ. ፫:፲፮-፲፯

*፬ኛ አንቀጽ*

*ሥላሴን በባሕርይና በአካል፣ በግብርም የሚጠሩበትን ስም ለይቶ ያሳያል*

ከብዙ ስሕተት የሚያደርስ የሥላሴ የስማቸውን ምሥጢር ለይቶ አለማወቅ ነው:: በባሕርይ የሚጠሩበት ስም አለ:: በአካል የሚጠሩበት ስም አለ፣ በግብር የሚጠሩበት ስም አለ:: በባሕርይ የሚጠሩበትን ስም ለአካልና ለግብር፣ በአካል የሚጠሩበትን ስም ለባሕርይና ለግብር፣ በግብር የሚጠሩበትን ስም ለባሕርይና ለአካል ሰጥተው ሲናገሩ የአንድነታቸው፣ የሦስትነታቸው ምሥጢር ፈራሽ ሆኖ ይገኛል:: ስለዚህ ጠንቅቆ አስተውሎ መመልከት ይገባል:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መባል የአካል ስም ነው:: አብ ማለት ጥንት መሠረት መገኛ ማለት ነው:: ጥንት መሠረት መገኛ በመሆንም ወላዲ አሥራጺ ይባላል:: ጥንት መሠረት አስገኚ በመሆን ወላዲ አሥራጺ ተባለ እንጅ ወላዲ አሥራጺ በመሆኑ አብ የተባለ አይደለም:: ይህንም ለመረዳት ጎርጎርዮስ <u>፲፰ኛ</u> የተናገረውን መመልከት ነው::

ንባብ፡- "አእምር ኵሎ ግብረ፣ እም፫ ግብራት፣ ዘውእቶሙ አስማት፣ ወውእቱ ፍጥረት ወስም ወዘመድ ዘይተበሀል ሰብእ ወገብር ወመጋቢ:: ሰብእሰ በእንተ ፍጥረተ ጠባይዒሁ ወገብርኒ በእንተ ግብርናቲሁ ወመጋቢኒ በእንተ ስም ዘተሠይመ:: ወናሁ ንቤ ካዕበ በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወአኮ እሉ አስማት ዘቦኡ ላዕሌሆሙ ድኅረ አላ እሙንቱ አካላት:: ወብሂለ ሰብእሂ አኮ ውእቱ ስም ዳዕሙ ውእቱ ፍጥረቱ:: እስመ ለኵሎሙ ሰብእ ቦሙ ፩ ስም በበይናቲሆሙ ለለ፩ እምኔሆሙ:: እሉ እሙንቱ አዳም አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ:: ወአቃኒመ እግዚአብሔርሰ እሙንቱ አስማት ወአስማትኒ እሙንቱ አቃኒም እስመ ትርጓሜሁ ለአቃኒም፣ አካላት ጽኑዓን ወቀዋምያን ፍጹማነ ገጽ ወመልክዕ ብሂል:: ወሥሉስ ቅዱስ ይሰመዩ አስማተ ጽኑዐነ::''

ትርጉም፡- "በ፫ አካላት ያለውን ግብር ሁሉ በሦስት ግብራት እወቅ እነህም ፍጥረት፣ ስም፣ ዘመድ የሚባሉ ስሞች ናቸው:: ፍጥረት የተባለው ሰብእ (ሰው) መባል ነው:: ስም የተባለው ገብር (አገልጋይ) መባል ነው:: ዘመድ የተባለውም መጋቢ መባል ነው:: ሰብእ መባሉ ስለ ባሕርዩ መገኘት ነው:: ገብር መባሉም ተገዥ ስለሆነ ነው:: መጋቢ መባሉ ስለተሾመ ነው:: ሰው ስለ አካሉ መገኘት "ሰብእ" እንደተባለ ስለ አካላቸው ሕላዌ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ:: ስለ ተገዛ ገብር፣ ስለ ተሾመም "መጋቢ" እንዲባል ስለ ወለደ ወላዲ፣ ስለ ተወለደ ተወላዲ፣ ስለ ሠረጸ ሠራጺ እንላለን:: እኒህም ስሞች አካላት ሲኖሩ የኖሩ ናቸው እንጂ ኑረው ኑረው ኋላ የተጠሩባቸው አይደሉም:: ሰብእ መባልም በተፈጥሮው የወጣ ስም ነው እንጂ ኋላ የወጣ ስም አይደለም:: ለሰዎች ሁሉ እያንዳንዳቸው የሚጠሩበት ኋላ የወጣላቸው ስም አለና:: ይኸውም አዳም፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣

ያዕቆብ እንዳለው ነው:: የእግዚአብሔር ዓቃኒም ግን አስማት ናቸው:: አስማትም ዓቃኒም ናቸው:: የዓቃኒም ትርጓሜ በመልክ፣ በገጽ፣ ፍጹማን ሆነው፣ ፀንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነውና:: ልዩ ሦስት የሚሆኑ አካላትም ፀንተው በሚኖሩ በነዚህ ስሞች ይጠራሉ'' ብሏል:: (ሃይማኖተ አበው ድርሳን ፩ኛ)[31]

መቃርዮስ ዘእስክንድርያም ፵፫:-

<u>ንባብ</u>፡- "ወአስማቲሆሙ ለአካላት አኮ ግብር ከንቱ ሶበ ንሰምዮ ለአብ አበ፣ በእንተ ዘኮነ ወላዲ ወለ ወልድኒ ወልደ በእንተ ዘተወልደ እምአብ፣ ወለመንፈስ ቅድስኒ መንፈስ ቅድስ በእንተ ዘውጽአ እምአብ::''

<u>ትርጉም</u>፡- "አብ ስለ ወለደ አብ ብንለው፣ ወልድንም ከአብ ስለተወለደ ወልድ ብንለው፣ መንፈስ ቅዱስንም ከአብ ስለሠረፀ መንፈስ ቅዱስ ብንለውም አካላት ስማቸው ግብር የሌለው ከንቱ አይደለም'' ብሏል:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፩)[32]

ነገር ግን አንባቢ ሆይ አብን በእንተ ዘኮነ ወላዲ፣ ወልድንም በእንተ ዘተወልደ፣ መንፈስ ቅዱስም በእንተ ዘሠረጸ ስላለ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) የግብር ስም መስሎህ እንዳትሳሳት:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት የአካል ስም መሆኑን አስተውል:: አካል ግብርን ያስገኛል እንጂ ግብር አካልን የሚያስገኝ አይደለምና መጻሕፍትም የፊቱን ወደ ኋላ የኋላውን ወደ ፊት ማድረግ ልማድ ነው::

---

[31] ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምራት ሃ.አበው ምዕ ፲፫ ክፍል ፩ ቁ. ፬-፮
[32] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፺፰፥ ክፍል ፩ ቁ. ፬

ማስረጃ፡- ጌታችን:-

<u>ንባብ</u>፡- “አልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወልደ እጓለ እመሕያው::''

<u>ትርጉም</u>፡- “ማንም ወደ ሰማይ የወጣ የለም:: ከሰማይ የወረደው ነው እንጂ፣ እርሱም የሰው ልጅ በሰማይ የሚኖር'' እንዳለ ዮሐ ፫ ፤ ፲፫::

<u>ንባብ</u>፡-ጳውሎስም:- “ክርስቶስ ውእቱ ዘወረደ እም ሰማይ''

<u>ትርጉም</u>፡- “ከሰማይ የወረደ ክርስቶስ ነው'' እንዳለ:: ሮሜ ፲፥፯

ዳግመኛም

<u>ንባብ</u>፡- “ወዳግም ብእሲ እምሰማይ ሰማያዊ''

<u>ትርጉም</u>፡- “ከሰማይ የመጣው ሁለተኛው ሰው ሰማያዊ ነው''

እንዳለ:: ፩ኛ ቆሮ ፲፭ ፤ ፵፯

ይህን የመሰለ በየአንቀጹ ብዙ አለና ያስተውሏል:: አካል በመለኮት ከዊን ይገናዘባልና መለኮት ተብሎ ይጠራል:: የአካል ግብር አይገናዘብምና ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሠራጺ መለኮት ሊባል አይገባም:: የሚለያዩበትም የግብር ስም በመሆኑ ሦስት መለኮት ከማለት የሚያደርስ ይመስላልና/ያደርሳልና/ አብ መለኮት፣ ወልድ መለኮት መንፈስ ቅዱስ መለኮት ቢል ግን አካል በመለኮት ከዊን የሚገናዘብ ስለሆነ አያስነቅፍም::

አንባቢ ሆይ ሥላሴ በባሕርይና በባሕርይ ግብር፣ በአካልና በአካል ግብር፣ የሚጠሩበት ስም አለና:: በባሕርይ የሚጠሩበትን በአካል ከሚጠሩበት፣ በአካል የሚጠሩበትን በባሕርይ ከሚጠሩበት፣ በባሕርይ ግብር የሚጠሩበትን በአካል ግብር ከሚጠሩበት፣ በአካል

ግብር የሚጠሩበትን በባሕርይ ግብር ከሚጠሩበት ስም እያቀላቀልህ እንዳትቸገር በቅጥነተ ሕሊና ሁነህ አስተውል:: የመጻሕፍትን ከላይ መነሻቸውን ከታች መድረሻቸውን ጠንቅቀህ ተመልከት:: አንዳንድ ጊዜ ስለ አንዳንድ ነገር በንባብ የሚገናኙበት ምክንያት አይታጣምና እንዳትሳሳት:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት የአካል ስም እንደሆነ ወላዲ፣ ተወላዲ፣ ሠራጺ ማለት ግን የግብር ስም እንደሆነ በዚህም ልዩነት እንዳለበት በላይኛው አርእስት የተናገረውን በትሕትና በፈሪሃ እግዚአብሔር ሆነህ ተመልከት::

*www.kidusyared.org*

## *፫ኛ አንቀጽ*

### *ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ማለት ተከፍሎ በሌለባት በአንዲት ባሕርይ ያለ የከዊን ስም ነው*

ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ[33] ማለት ተከፍሎ በሌለባት በአንዲት ባሕርይ ያለ የከዊን ስም ነው:: ይኸውም ልዩነት ሳለበት አንድነት አንድነትም ሳለበት ልዩነት አለበት:: ልዩነቱ በከዊን ነው አንድነቱ ግን በሕልውና መገናዘብ ነው:: ወልድ ሰው ሆነ በተባለ ጊዜ አካል ተዋሐደ እንጂ ባሕርይ አልተዋሐደም እንዳይባል ወንጌላዊ ቃል ሥጋ ኮነ አለ እንጂ ወልድ ሥጋ ኮነ አላለም:: ባሕርይም ከተዋሐደ የሥላሴ ባሕርይ አንድ ነውና:: ፫ቱ ሰው ሆኑ እንዳያሰኝ ከልብና ከእስትንፋስ ለይቶ “ቃል ሥጋ ኮነ” አለ:: ቃልም ማለት በአካለ አብና በአካለ መንፈስ ቅዱስ በኮዊን የምትለይ በሕልውና የምትገናዘብ እንደሆነች "ነገር በምሳሌ መዝሙር በሃሌ'' እንደተባለው አስቀድመን ምሳሌውን መርምረን

---

[33] የከዊን ስም "ልብ" አብ ለራሱ ለባዊ አዋቂው (አዋቂ) ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡና (ዕውቀት) መሆኑን የሚያመለክት ስም ነው:: ቃልም የወልድ የከዊን ስም ነው:: ለራሱ ነባቢ (ተናጋሪ) ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ መሆኑ የሚገለጽበት የከዊን (ቃል የመሆን) ስሙ ነው:: እስትንፋስ የመንፈስ ቅዱስ የከዊን ስሙ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለራሱ ሕያው ሆኖ ለአብና ለወልድ ሕይወት እንደሆነ የምናውቅበት የከዊን (ሕይወተ አብ ወወልድ) የመሆን ስሙ ነው::

በሁለተኛው አንቀጽ በነፋስና በፀሐይ በእሳትና በቀላይ መስለን ተናግረናልና በማስተዋል ይመለከቷል::

መለኮት እንደ አካላት ከ፫ ይከፈላል የሚል ሰው ይህን ነገር ከራሱ አንቅቶ በልብ-ወለድ ቃል ተናግሮታል እንጂ መጻሕፍት ከተናገሩት ኃይለ ቃልና ከመሰሉት ምሳሌ ምስክር አምጥቶ ለማስረዳት አይችልም:: የሥላሴን ባሕርይና አካል እንደ ሰው ባሕርይና አካል አድረጎ አካል የሌለው ባሕርይ፣ ባሕርይም የሌለው አካል የለምና ባሕርይ፣ አካልን ተከትሎ ከሦስት ይከፈላል ይላል::

መልስ:- ባያስተውለው ነው እንጂ ይህ ነገር ከሰማይና ከምድር ይልቅ የተራራቀ ነው:: የሰው ባሕርይ በአካል ቢከፈል በየራሱ ልብ፣ በየራሱ ቃል፣ በየራሱ እስትንፋስ ያለው ሆኖ በየራሱ ልዩ ልዩ ሥራውን ይሠራል:: አንዳንድ ቅዱሳንም በፀጋ ቢተዋወቁና አንዳንድ ሥራ ቢሠሩ ያደረባቸው መንፈስ ቅዱስ በሀብት አገናኝቷቸው ነው እንጂ የባሕርይና የሕልውና አንድነት ኖሯቸው አይደለም::ሥላሴ ግን አካላቸው የተለየ ሲሆን ባሕርያቸው ተከፍሎ የሌለበት አንድ ለመሆኑ ማስረጃው የሦስቱ ልብ አንድ አብ ሆኖ አንድ ዕውቀትን ያውቃሉ:: የሦስቱ ቃል አንድ ወልድ ሆኖ አንድ ነገርን ይናገራሉ:: የሦስቱ እስትንፋስ አንድ መንፈስ ቅዱስ ሆኖ አንድ የሕይወትን ሥራ ይሠራሉ:: እንዲህም ከሆነ ሊቃውንት “ይሜለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት” ያሉትን ተመልክቶ ይልቁንም “አጤን ይበልጡ ቃለ አጤ'' እንዲሉ እርሱ ባለቤቱ “አነ ወአብ ፩ ንሕነ''[34] ዮሐ ፲፤፴:: “አነ በአብ ወአብ ብየ'' [35] ዮሐ ፲፬፤፲:: ያለውን ተረድቶ ባሕርየ መለኮት በአካል ከሦስት የማይከፈል መሆኑን ማመን ይገባል:: ከዚህ ግን ወጥቶ መለኮት እንደ አካላት ከሦስት ይከፈላል ማለት ግን አብን ልብ ወልድን ቃል መንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ ማለትን ትቶ፣

[34] "እኔና አብ አንድ ነን"

[35] "እኔ በአብ ሕልው ነኝ አብም በእኔ ሕልው ነው"

ለሦስቱ በየራሳቸው ልብ ቃል እስትንፋስ አላቸው ብሎ፣ ሦስት አማልክት በማለት የዮሐንስ ተዐቃቢን ሃይማኖት መመስከር ነው::

ይወልደዋል አይቀድመውም ማለት ቅሉ አካል በተከፍሎ ሲለይ፣ አንድ ባሕርየ መለኮት ተከፍሎ ሳይኖርበት፣ ሦስቱን አካላት በማገናዘብ /ማዋሐድ/ በቅድምና የነበረ ስለሆነ ነው:: ይህንም ለመረዳት:- ባስልዮስ ዘቂሣርያ የተናገረውን ይመልከቱ::

፲፪ኛ ንባብ:- "ይደልወነ ናእምር ኅበ ኅብረተ ተዋሕዶተ መለኮት ዘ ፫ አካላት፣ ወናስተዋሕድ በአኀብሮ ዘዚአሆሙ ፩መለኮት:: ንእመን በሃይማኖት ከመ ይትወሐድ  መለኮት በአብ:: እስመ እምኀበ አብ ተወልደ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስሂ ወፅአ እምኔሁ:: እንዘ ኢይቀድም ፩እምካልኡ፣ ወካልኡ እምሣልሱ፣ ወበልደተ ወልድ ወበጸአተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ፣ ይትወሐድ መለኮተ ሥላሴሁ ለአምላክነ"

ትርጉም:- "በአንድ መለኮት ተዋሕዶ የሦስቱን አካላት መገናዘብ ልናውቅ ይገባል:: በአንድ መለኮት በማገናዘብም ልዩ ልዩ የሆነ አካላትን እናዋሕድ:: መለኮት አንድ እንደሆነ በማመን፣ በአብ ያለ መለኮት ወልድን መንፈስ ቅዱስን እንዲዋሐድ እንመን:: አብ ከወልድ ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይቀድም፣ ወልድ ከአብ ተወልድዋልና፣ መንፈስ ቅዱስም ከርሱ ሠርፆአል፣ ከአብ ወልድ በመወለዱ፣ መንፈስ ቅዱስም በመሥረፁ፣ የአምላካችን የሦስትነቱን አካል መለኮት ይዋሐዳል" ብሏልና:: (ክፍል ፪ )[36]

[36] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፴፪፥ ክፍል ፪ ቁ. ፬–፮

አሁን በዚህ መስመር ያነበብውን የባስልስዮስን ቃል አስተውሎ የሚመለከት ሰው:- መለኮትን በአካል ሦስት ማለት ከሚያመጣው ፫ልብ፣ ፫ቃል፣ ፫እስትንፋስ ከማለት ተጠብቆ በአብ ልብነት ለባውያን፣ በወልድ ቃልነት ነባብያን፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያዋን ብሎ በአካል ፫ በመለኮት አንድ በምታሰኝ ሃይማኖት ይፀናል:: መለኮት እንደ አካላት ከሦስት ይከፈላል የሚል ሰው ግን ወልድ ከአብ የሚወለደው ልደት ሰው ሁሉ ከአባቱ እንደሚወለደው ልደት ነው ማለቱ እንደሆነ ጠንቅቆ ማስተዋል ያሻዋል:: ማናቸውም ልጅ ከአባቱ ሲወለድ ባሕርዩ በአካል የሚከፈልና የሚለይ ስለሆነ አባት ከልጁ ይቀድማል ይበልጣልም::

ማስረጃ:- ቴዎዶጦስ ዘእንቆራ ፳ኛ:-

<u>ንባብ</u>:- “ወእመሰ ኮነ ብእሲ አበ፣ ክሡት ነገሩ ከመ የዐቢ አብ እምወልድ:: ወስሞሂ ያጤይቅ ከመ ውእቱ እምቅድመ ወልዱ::''

<u>ትርጉም</u>:- “ሰው አባት ሲባል ከልጁ እንዲበልጥ ነገሩ የታወቀ ነው:: አባት መባሉም ከልጁ አስቀድሞ እንደነበረ ያስረዳል'' እንዳለ:: [37]

ወልድ ግን ከአብ ሲወለድ አካሉ በተከፍሎ ቢለይም ሕላዌ መለኮት በተከፍሎ መለየት የለበትም:: አወላለዱም ብርሃን ፀሐይ ተከፍሎ መለየት ሳይኖርበት ከክበብ እንዲገኝ በሕላዌ መለኮት ከአብ ተከፍሎ መለየት ሳይኖርበት ነውና፣ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ የለበትም::

አሁን ማስረጃ አድርገን የጠራነው ቴዎዶጦስ:-

<u>ንባብ</u>:- “ወለነሰሂ ይደልወነ ነሐሊ ዘንተ በሕላዌ መለኮት:: አላ ነአምን በወልድ ዋሕድ ከመ ውእቱ ቀዳማዊ ምስለ አብ በኲሉ ዘመን፣

[37] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፶፫፥ ክፍል ፩ ቁ. ፳

ወወልደ አብ ዋሕድ ይሰመይ ብርሃነ፣ እስመ ብርሃን ዘተወልደ እም ብርሃን፣ ኢይትበሀል ተወልደ እምድኅረ ብርሃን አላ በጊዜ ዘኮነ ቦቱ ውእቱ ብርሃን፣ ይትረከብ ብርሃን ዘተወልደ እምኔሁ፣ ወወትረ ሕልው ምስሌሁ:: ብርሃንኒ ያጤይቀከ አምሳሊሁ ለወልድ ዘውእቱ ሕልው ምስለ አብ በኩሉ ጊዜ እምቅድመ ኩሉ ዓለም::"

ትርጉም:- "በመለኮት ባሕርይ ይህን ማሰብ ለእኛ አይገባንም፣ ወልድ ዋሕድ በዘመን ሁሉ ከአብ ጋር የነበረ ቀዳማዊ እንደሆነ እናምናለን እንጂ፣ ከአብ የተወለደ ዋሕድ ቃልም ብርሃን ይባላል:: ከክበብ የተገኘ ብርሃን ከክበብ በኋላ ተገኘ አይባልምና:: ብርሃን ክበብ በተገኘበት ጊዜ ተገኝቶ ከክበብ ሳይለይ አብሮ ይኖራል እንጂ፣ ብርሃንም የወልድ ምሳሌነቱን ያስረዳሃል ይኸውም ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ከአብ ጋራ ሁልጊዜ የነበረ ነው" እንዳለ:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፩)[38]

ይህን ምሳሌ ጠንቅቀን ብንመለከት አማናዊውን አጉልቶ ያሳየናል:: የሰውም ቃል በተወለደ ጊዜ አወላለዱ አሁን በተናገርነው በብርሃንና በክበብ አምሳል ነው:: ቃል ከልብ በተከፍሎ መለየት ሳይኖርበት፣ በአካል ከዊን ይወለዳል፣ በአካል ከዊን ተለይቶ መወለዱንም የሚያስረዳ ነገር፣ ከብራና ላይ በቀለም በተጻፈ ጊዜ አካል ገዝቶ ይታያል ይነበባልም:: ባሕርዩ ግን በተከፍሎ መለየት የለበትምና በልብ ውስጥ ሕልው ሆኖ ሲታሰብ ይኖራል::

ማስረጃ:- ቴዎዶጦስ ዘእንቀራ ፳፫ኛ:-

ንባብ:- "ወለከሂ ቃልከ ዘይትወለድ እምልብከ ይሄሉ ውስቴትከ ተወሊዶ እምልብከ::"

[38] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፺፫ ክፍል ፩ ቁ. ፱

ትርጉም:- "ያንተስ ስንኳ ከልብህ የሚገኝ ቃልህ፣ ከልብህ ተገኝቶ፣ በልብህ ውስጥ ሕልው ሆኖ ይኖራል'' እንዳለ:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፩) [39]

ንባብ:- ዳግመኛም "ወህየንተ ልብ ዘዝየ ነአምሮ ለአብ ህየ፣ ወህየንተ ቃል ዘዝየ ነአምሮ ለቃል ዘእግዚአብሔር ከመ ቦቱ ሕላዌ ወቦቱ አካል በፍጹም ገጽ ወመልክዕ፣ ዘከመ ገጻ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ እስመ ውእቱ ወልዱ ለአብ::''

ትርጉም:- "በኛ ባለ በልብ አምሳል አብን እናውቀዋለን:: እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ባለ በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክዕ አካልና ባሕርይ እንዳለው፣ በእኛ ባለ በቃል አምሳል ቃለ እግዚአብሔር ወልድን እናውቃለን፣ አብን አህሎ መስሎ የተወለደ የአብ ልጅ ነውና" ብሎ የአብ ልብነት በልብ፣ የወልድ ቃልነት በቃል፣ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ በእስትንፋስ መመሰላቸውን ያስረዳል:: (ሃይማኖተ አበው ክፍል ፩)[40]

ልጅ ከአባቱ ባሕርይ በአካል ተለይቶ የሚከፈል ስለሆነ አባትና ልጅ አንድ ልብ አንድ ቃል አንድ እስትንፋስ በመሆን አይገኙም:: ወልድ ግን ከአብ ሲወለድ፣ ባሕርይ እንደ አካሉ የማይከፈል አንድ ስለሆነ፣ ሦስት አካላት በአንድ ልብ በአንድ ቃል በአንድ እስትንፋስ ተገናዝበው ይኖራሉ:: ይህንም ለመረዳት በየአንቀጹ የተነገረውን መመልከት ነው::

*www.kidusyared.org*

---

[39] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፺፫ ክፍል ፩ ቁ. ፲፯

[40] ዝኒ ከማሁ ቁ ፳

## *፩ኛ አንቀጽ*

### *ወልድ ማለት የተረክቦ[41] ስሙ እንደሆነ ይናገራል*

ወልድ ማለት አካሉ በቃልነቱ ከዊን ተድኅሮ[42] ሳይኖርበት አብን አህሎ መስሎ ከአብ አካል በመገኘቱ የሚጠራበት የተረክቦ ስሙ ነው:: ተረክቦውም ተፈልጦ ሳይኖርበት በሕልውና እያለ ነው:: የነፍስ ቃሏ ከልብነቷ ተገኝቶ ሳይለይ በአካሏ ሕልው ሆኖ እንደሚኖር ማነጻጸር ነው::

ማስረጃ:- ቄርሎስ በእስተጉቡእ:

<u>ንባብ</u>:- “ወልድ ዋሕድ በሕላዌሁ ዘእምኀበ እግዚአብሔር አብ ይሰመይ ቃለ፣ እስመ ፩ ውእቱ ተወለደ እም ፩ አብ::"

<u>ትርጉም</u>:- “ወልድ ዋሕድ ከእግዚአብሔር አብ ተወልዶ በአብ ሕልው ሆኖ በሚኖርበት ባሕርዩ ቃል ይባላል:: “አንዱ እርሱ ከአንድ አብ ተወልዷልና" ብሏል::

ተወላዲ ማለት ግን በተከፍሎ የሚጠራበት የግብር ስሙ ነው:: ወልድ ማለትና ተወላዲ ማለት በግሥ አንቀጽ መልክ ፊደሉ አንድ ሲመስል፣ የምሥጢር ልዩነት እንዳለው አሁን የተናገርነውን የተረክቦንና የተከፍሎን ምሥጢር ጠንቅቆ ማስተዋል ነው:: ተረክቦ ያልነውም

---

41 ተረክቦ ማለት ማኘት ማለት ነው

42 ወደ ኋላ ሳይቀር

የአካሉ ሕላዌ ከአብ አካል የተለየ ሆኖ በፍጹም ገጽና በፍጹም መልክ መታወቁ ነው እንጂ፤ እግዚአበሔር የተገኘበት ጊዜ አይደለም::

ማስረጃ:- ሱኑትዩስ:-

<u>ንባብ</u>:- "ወኢይትረከብ ሀልዎቱ እምኃበ ወኢምንትኒ"

<u>ትርጉም</u>:- "አኗኗሩ ከምንም ከምን አይገኝም" እንዳለ::

"ከምንም ተገኘ  አይባልም"[43]

ሠለስቱ ምዕትም በቅዳሴ:-

<u>ንባብ</u>:- "ኢይክል መኑሂ ይባዕ ማዕከለ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ ያዕምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ፣ ወለዶ አብ ለወልዱ ኢይትበሀል ዘጊዜ ወበዘከመዝ መዋዕል ወለዶ፤ ኢይትአመር ልደቱ እም አብ እስመ ዕፁብ ውእቱ፣ ወኢይትአወቅ ህላዌሁ እስመ ስውር ውእቱ"

<u>ትርጉም</u>:- "ማንም ማን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ሊገባ አይችልም:: አኗኗሩ እንደምንም እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፣ አብ ልጁን ወልዶታል:: ነገር ግን አብ ልጁን በዚህ ጊዜ እንዲህም ባለ ዘመን ወለደው አይባልም፤ ከአብ መወለዱ አይመረመርም፣ የሚያስጨንቅ ነውና፤ አኗኗሩ አይታወቅም የተሰወረ ነውና፤" እንዲሉ::  ተከፍሎም በመለየት እንደሆነ የሚያስረዳ ሊቃውንት በብዙ አንቀጽ ገልጸዋል::

<u>ንባብ</u>:- "ተጋብአ በተከፍሎ ወተከፍሎ በተጋብአ"

---

[43] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፻፲ ክፍል ፪ ቁ. ፬

ትርጉም:- "አንድነት በመለየት መለየትም በአንድነት አለ"[44]

፵፱ኛ አትናቴዎስ ዘአንጾኪያ

፶፪ኛ ሱኑትዩስ ዘእስክንድርያ

፶፩ኛ ክርስቶዶሉ ዘእስክንድርያ

እመልዕክተ ሲኖዲቆን አንቀጽ ሁለተኛ አይ ፩. ፪. ፫.

ንባብ፡- "ኅቡራን እንበለ ተሌልዮ ወሊሉያን እንበለ ትድምርት"

ትርጉም:- "ባለመለያየት አንድ ናቸውና አንድ ባለመሆንም ልዩ ናቸው፣" እያሉ ይናገራሉና:: (ቆዝሞስ ዘእስክንድርያ ክፍል ፩ኛ ሃይ. አበው ፵፪ኛ)[45] ወልድ ማለትና ተወላዲ ማለት፣ በምሥጢር ልዩነት እንዳለበት በዚህ ማስተዋል ነው::

*፫ኛ አንቀጽ*

*እግዚአብሔር ማለትና መለኮት ማለት አንድ ሲሆን፣ ልዩነት እንዳለበት ይናገራል*

እግዚአብሔር ማለትና መለኮት ማለት አንድ ሲሆን፣ ልዩነት አለበት፤ ልዩነት እንዳለበት የሚያስረዳ ነገር እናሳያለን:: መለኮት ማለት እንዲህ ነው ተብሎ በማይነገርና በማይታወቅ ጠባይ የሚጠራበት ስም ነው:: እግዚአብሔር ማለት ግን፤ አካል በአካልነቱ ግብር ሳይሆን፣ በባሕርይ ግብሩ የሚጠራበት የግብር ስም ነው:: እግዚአብሔር የማለትም

---

44 ሃይማኖተ አበው ምዕ ፻፯፥ ፫

45 ሃይማኖተ አበው ምዕ ፺፰፥፫

ትርጓሜው በአንድነትና በሦስትነት ፈጥሮ የሚገዛ፣ ቅድመ ዓለም ያለ ጥንት የነበረ፣ ድኅረ ዓለም ያለ ፍጻሜ የሚኖር ዘላለማዊ አምላክ ማለት ነው:: ሊቃውንትም እግዚአብሔር ማለትም አንቀጽ ተቀባይ ባለቤት፤ መለኮትን ማድረጊያ እያደረጉ "በ" የሚባል አገባብ እየጫኑ ይነግሩናል:: “እግዚአብሔር አሐዱ በመለኮት”[46] ይላል እንጂ፤ “መለኮት አሐዱ በእግዚአብሔር”[47] አይልም፤ ይሄለሱ በአካላት ብሎ ይትወሐዱ በመለኮት[48] ይላል እንጂ፣ “ይትወሐዱ በእግዚአብሔር”[49] የሚል አይገኝም:: ይኸውም እግዚአብሔርና መለኮት የማለት ስም አንድ ሲሆን፣ ልዩነትን ያስረዳል:: እንዲህ ከሆነ መጻሕፍት ማዋሐጃ አድርገው የተናገሩትን መለኮት፣ መለኮትን አንቀጽ ተቀባይ ባለቤት አድርጎ፣ መለኮት በአካል ሦስት ማለት ስህተት እንደሆነ አስተዋይ ልቡና ሳይረዳው አይቀርም::

*www.kidusyared.org*

[46] እግዚአብሔር በመለኮት አንድ ነው ይላል እንጅ
[47] መለኮት በእግዚአብሔር አንድ ነው አይባልም (አይልም)
[48] በአካል ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ይሆናሉ
[49] በእግዚአብሔር አንድ ይሆናሉ: :

*፳ኛ አንቀጽ*

የሥላሴ መንግሥት በአካል ከሦስት የማይከፈል አንድ መሆኑን ይናገራል

ጥያቄ:- የሥላሴ መንግሥት በአካል ሦስት ነው ማለት ስሕተት ይሆናልን?

መልስ:- አዎን ስሕተት ነው፤ መንግሥት በአካል የሚከፈል ሦስት ነው ማለት፣ ሦስት መንግሥት አስገኝቶ ዘጠኝ አካላት ማለትን ያስከትላልና፣ እንዲህም ከሆነ ሊቃውንት በየአንቀጹ አሐቲ መንግሥት[50] እያሉ የተናገሩት ቃል ሐሰት ሆነ ማለት ነው::

ማስረጃ:- አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ ፯ኛ

ንባብ:- "ሥላሴ ዕሪት ዘእንበለ ፍልጠት በ፫ አካላት ወበ፩ መለኮት፣ አሐቲ መንግሥት፣ ወአሐቲ ምልክና፣ ወአሐቲ ሥምረት፣ ወአሐቲ ኃይል፣ ወአሐቲ ስብሐት::"

ትርጉም:- "ሥላሴ ያለመለያየት በመለኮት አንዲት ትክክል ናት:: ያለመለወጥም በአካላት ሦስት ናት፤ በመንግሥት አንዲት፣ በአገዛዝም አንዲት፣ በፈቃድም አንዲት፣ በኃይልም አንዲት፣ በጌትነትም አንዲት ናት" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[51]

ሠለስቱ ምዕትም ፲፫:-

ንባብ:- “ሥሉስ ፍጹም በ፩ መለኮት እስከ ለዓለም

፩እግዚአብሔር፣ ወአሐቲ መንግሥት እንተ ኢትትከፈል

---

[50] አንዲት መንግሥት

[51] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፲፩፥ ፭–፮

ወኢትትፋለስ"

ትርጉም:- "በገጽ በአካል ፍጹማን የሚሆኑ ሦስቱ አካላት፣ እስከ ዘለዓለም ድረስ በመለኮት አንድ ናቸው:: አንድ ጌታ ከሦስት የማትከፈል ከአንድ ወደ አንዱ የማታልፍ አንዲት መንግሥት ናቸው" ብለዋል[52]

ክፍል ፮ኛ ዲዮናስዮስም:-

ንባብ:- "ኢንበውዕ ውስተ ከፈለ መንግሥት፤ አላ ንበል አሐቲ መንግሥት" ብሏል:: ፲፫ አንቀጽ እይ::

አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው:-

ንባብ፡- "መለኮትሰ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ፣ አሐቲ መንግሥት፣ ወአሐቲ ሥልጣን፣ ወአሐቲ ምኩናን"

ትርጉም:- “መለኮትስ አንድ አምላክ፣ አንዲት መንግሥት፣ አንዲት ሥልጣን፣ አንዲት አገዛዝ የሚሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው” ብሏል::

ይህን የመሰለ የተናገሩ ሊቃውንት ብዙ ናቸውና፣ ማስረጃ ሳይዙ መንግሥት በአካል ሦስት ከማለት ተጠብቆ እንዴት እንደሆነች መጻሕፍት በየአንቀጹ የመሰከርዋት

/የመሰከሩላት/ የሥላሴ መንግሥት በአካል ከሦስት የማትከፈል አንዲት መሆኗን አምኖ፣ “ትምጻእ መንግሥትከ"[53] እያሉ የዚችን አንዲት መንግሥት በአለበት እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት ይገባል::

---

[52] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፲፱፥፬–፮

[53] መንግሥትህ ትምጣ

ዳግመኛ መንግሥት ሦስት ከሆነ ዙፋን የሌለው መንግሥት የለምና ሦስት መንበር አለ ማለት የግድ ነው:: እንዲህ ከሆነ ሕዝቅኤል በፈለገ ኮቦር፣ /ሕዝ ፩፥ ፲፱ - ፳፫/ ዮሐንስ በደሴተ ፍጥሞ /ራዕ ፬ ፥ ፪ - ፫/ አራቱ ኪሩቤል ተሸክመውት ያዩት መንበር ከሦስቱ ነገሥታት የማናቸው ንጉሥ ነው ይባላል? ሦስቱ ገጻት በአንድ መንበር ላይ መታየታቸው ሦስቱ አካላት የአንድ ሕላዌ መለኮት በምትሆን በአንዲት መንግሥት አንድ መሆናቸውን ሲያስረዳ አይደለምን? መንበር ያለውም መንግሥት እንደሆነ የሚያስረዳ ነገር ነቢዩ ዳዊት

<u>ንባብ</u>:- "መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም::"

<u>ትርጉም</u>:- "አቤቱ ዙፋንህ ለዘላለም ነው" ያለውን መዝ ፺፫፥፪ ሲተረጉም ዮሐንስ አፈወርቅ፡-

<u>ንባብ</u>:- "ወዝንቱ ያሌቡ እንበይነ መንግሥቱ"

<u>ትርጉም</u>:- "ዙፋንህ ለዘላለም ነው" ያለውን "መንግሥቱ ዘለዓለም መሆኑን ያስረዳል" ብሏል:: /ድርሳን ፫/

በተረፈ ቄርሎስም ሳዊሮስ ዘገብሎን:-

<u>ንባብ</u>:- "መንበረሰ ሶበ ሰማዕከ ለብዎ ለመንበር ከመድልወተ መለኮት ዘውእቱ መንግሥት ወሥልጣን ወእግዚእና"

<u>ትርጉም</u>:- "መንበር ሲል በሰማህ ጊዜ መንበር ያለው ለመለኮት የሚገባ መንግሥትና ሥልጣን ጌትነትም እንደሆነ እወቅ፤" ብሎ ተርጉሞታል::

መንግሥትማ በአካል የሚከፈል ሦስት ከሆነ፣ ሦስቱ ገጻት በየራሳቸው በሦስት መንበር ተቀምጠው ባልታዩም ነበርን? እንኪያስ ሦስቱ ገጻት በአንድ መንበር ተቀምጠው ከታዩ፣ ነቢዩም መንበር ያለውን ዮሐንስ አፈወርቅና ሳዊሮስ መንግሥት ብለው ከተረጎሙት፣ መንግሥት በአካል የማይከፈል አንድ እንደሆነ፣ ታወቀ ተረዳም:: ኢሳይያስም:-

ንባብ:- "ርኢክዎ ለእግዚአብሔር እነዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ልዑል ወነዋኅ"

ትርጉም:- "እግዚአብሔርን ከፍ ባለ በረጅም ዙፋን ተቀምጦ አየሁት" ብሎ አንድ መንበርን አንድ እግዚእን ከተናገረ በኋላ፡-

ንባብ:- "ወሱራፌል ይቀውሙ አውዶ ይጸርሁ ወይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት መልዐ ኩሎ ምድረ ስብሐቲከ"

ትርጉም:- “ሱራፌል በዙሪያው ቁመው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ምሥጋናህ በምድር መላ እያሉ ይጮሁ ነበር" ብሏል:: ኢሳ ፮ ፥ ፩-፫

ሦስት ጊዜ መላልሶ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ማለት አካላት ሦስት መሆናቸውን፣ ምስጋናው አንድ ቅዱስ መሆኑንና መንበሩም አንድ መሆኑን፣ ሦስቱ በአንድ መንግሥት፣ አንድ እግዚእ (ጌታ) መሆናቸውን ያስረዳል:: እንዲህም መንግሥት በአካል የሚከፈል ሦስት ነው ማለት ስህተት እንደሆነ አስተውል:: አስተዋይ ልቦና ያለው ሰውም እንዲረዳው የታመነ ነው::

*፬ኛ አንቀጽ*

*አብ ማለትና ወላዲ ማለት፣ ወልድ ማለትና ተወላዲ ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ ማለትና ሰራጺ ማለት ልዩ ልዩ እንደሆነ ይናገራል*

ወላዲ መለኮት፣ ተወላዲ መለኮት፣ ሰራጺ መለኮት ማለትን ነቅፈን አብ መለኮት ወልድ መለኮት መንፈስ ቅዱስ መለኮት ማለት አያስነቅፍም ስላልነ፣ አብ ማለትና ወላዲ ማለት፣ ወልድ ማለትና ተወላዲ ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ ማለትና ሰራጺ ማለት አንድ አይደለምን? ምን ይለየዋል የሚል ሰው ቢኖር:-

መልሱ:- ይህን ለይተን በተናገርንበት በአራተኛው አንቀጽ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት የአካል ስም፣ ወላዲ ተወላዲ ሰራጺ ማለት ግን የግብር ስም እንደሆነ፣ በዚህም ልዩነት እንዳለበት ያሳየነውን ምሥጢር ቢመረምር ልዩነቱን ይረዳዋል:: አሁንም እየደጋገመነ በሚከተለው መስመር እናስጠነቅቀዋለን:: ወላዲ ተወላዲ ሰራጺ ማለት በአካል ቅሉ የማይገናዘብ ልዩ ነው:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት ግን በሕላዌ መለኮት ባለች በባሕርይ ከዊንና በሕልውና የሚገናዘብና የሚዋሐድ ነው:: መገናዘቡንም የሚያስረዳ:- ባስልዮስ ዘቂሳርያ:

ንባብ:- "ለወልድሰ ቦቱ ኵሉ ዘተናገርነ በእንተ ሕላዌ አብ ዘበድልዎት፤ ዝንቱ ውእቱ ዘተወልደ እም አብ፤ እስመ ወልድ ዋሕድ ውእቱ፣ ወቦቱ ኵሉ ኮነ ወአልቦ ዘይትከፈል ምንትኒ ማዕከሌሁ ወማእከለ አቡሁ፤ ወዝንቱ ስም ዘውእቱ ወልድ ያጤይቅ ሕብረተ ሕላዌሆሙ፣ እስመ ወልዱ ውእቱ ዘተወልደ እምኔሁ::"

ትርጉም:- "ስለ አብ ባሕርይ ጌትነት በሚገባ የተናገርው ሁሉ በወልድ ያለ ነው:: ይኸውም ከአብ የተወለደው ነው፤ በመለኮት አንድ ባሕርይ የሚሆን አንድ ልጅ ነውና፣ በመለኮት አንድ ሕልውና የሚሆን በአባቱ ያለ ሁሉ በእርሱ አለና፣ ሁሉ የተፈጠረበት አንድ ልጅ ስለሆነ፣ በእርሱና በአባቱ መካከል ምንም ምን መለየት የለም፤ ይኸም ስም ይኸውም ወልድ መባል የባሕርያቸውን አንድነት ያስረዳል፤ ከእርሱ የተወለደ የባሕርይ ልጅ ስለሆነ" ብሏል:: (ሃ. አበው ክፍል ፩)[54]

አንባቢ ሆይ በአካል ስም ወልድ ብሎ በመለኮት አንድ ባሕርይ ያለውንና "ይህን ስም ይኸውም ወልድ መባል ነው" ብሎ "የባሕርያቸውን አንድነት ያስረዳል" ያለውን ጠንቅቀህ አስተውል:: በእርሱና በአባቱ መካከል ምን ምን መለየት የለም በማለቱ በሁለቱ አካላት ያለ መለኮት ተከፍሎ የሌለበት አንድ መሆኑን ያስረዳልና::

ማስረጃ:- ቴዎዶጦስ ዘእንቆራ:-

ንባብ:- "ንነግረከ ወናሌብወከ ዘንተ ስመ ዘውእቱ ወልድ ከመ ውእቱ ፩ ሕላዌ ምስለ አብ::"

ትርጉም:- "ይህንን ስም ይኸውም ወልድ ማለት ነው ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ መሆኑን እንዲያስረዳ እንናገራለን፤" ብሏል:: (ሃ. አበው ክፍል ፩)[55]

ይኸውም የባስልዮስን ቃል የመሰለ ነው:: እንዲህ ባለ ምሥጢር የአካል ስም ከግብር ስም፣ የግብር ስም ከአካል ስም ልዩ ነውና፣ በስህተት ባሕር እንዳትጠልቅ በክህደት ገደል እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ::

---

[54] ሃይ. አበው ክፍል ፬፤ ምዕ ፴፫፥ ፴–፴፪

[55] ሃይ. አበው ምዕ ፶፫፥፲፩

*፯ኛ አንቀጽ*

*ለሥላሴ በየራሳቸው ልብ ቃል እስትንፋስ እንደሌላቸው ይናገራል*

ጥያቄ:- ለሥላሴ በየራሳቸው ልብ ቃል እስትንፋስ አለው ካልተባለ፣ አካለ ጎደሎ ያሰኛል እንጂ፣ በአካል ፍጹማን ያሰኛልን?

መልስ:- ልብ ቃል እስትንፋስ በአካል ሕልው ሆኖ ለአካል ሕይወት የሚሆን የባሕርይ ከዊን ነው እንጂ፣ እርሱ እራሱ እንደ ዓይንና እንደ ጆሮ፣ እንደ አፍና እንደ አፍንጫ፣ እንደ እጅና እንደ እግር በቅርጽ የሚለይ አካል አይደለምና አካለ ጎደሎ አያሰኝም:: ይህንም ሌላ ምስክር ሳንፈልግ በራሳችን ሕላዌ እናስረዳለን:: ሰው በሞተ ጊዜ ልቡና ቃሉ እስትንፋሱ ይለዩታል፤ በአካል ያለው ሕይወት ስለተለየው እገሌ ሞተ ይባላል እንጂ አካሉ ጎደለ አይባልም:: አካሉም ከፍጹምነቱ ሳይጎድል በአልጋ ላይ ተኝቶ ይታያል:: ኋላም በመግነዝ ተይዞ ፍጹም አካሉ ወደ መቃብር ይወርዳል:: ኋላም በትንሣኤ ዘጉባኤ ነፍሱ ካለችበት መጥታ ስታድርበት፣ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ያለው ሕያው ሆኖ ይነሣል::

ማስረጃ:- ያዕቆብ ዘሥሩግ በቅዳሴው:-

ንባብ:- "በቀዳሚ ንፍሐተ ቀርን ይትጋባእ ፀበለ ሥጋ ዘተዘርወ፤ ወበዳግም ንፍሐተ ቀርን ይሰፈያ አዕፅምት ምስለ ሥጋ፤ ወይከውን በድነ ፍጹመ ዘእንበለ አንሰሕስሆ፣ በሣልስ ንፍሐተ ቀርን ይትነሥኡ ሙታን ከመቅጽፈተ ዓይን"

ትርጉም:- "በመጀመሪያው አዋጅ ተለያቶ ተበትኖ የነበረ አጥንትና ሥጋ ይሰበሰባል፤ በሁለተኛው አዋጅ አጥንት ከሥጋ ጋር ተያይዞ የማይንቀሳቀስ ፍጹም አካል ያለው በድን ይሆናል፤ በሦስተኛው አዋጅ ሙታን እንደ ዓይን ቅጽበት ይነሣሉ" እንዳለ:: (ሐዳፌ ነፍስ)

እንዲህ ከሆነ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ በነፍስ አካል ያለ በሥጋ ሕይወት የሚሆን የባሕርይ ከዊን ነው እንጂ፤ እርሱ እራሱ አካል እንዳይደለ ይታወቃል:: "የሱስ አካል የነፍስ አካል ነው":: እንዲህም በማለት አንዳንድ ሰዎች የተሳሳቱበትን ምክንያት በሚከተለው መስመር ገልጠን እናሳያለን:: በሥጋ አካል ከደረት በታች ከሆድ በላይ ልብ የተባለ ሥጋዊ አካል አለና፣ በዚህ ምክንያት ልብ አካል ነው ይላሉ፤ ልብ የተባለበትን ምሥጢሩን ግን አልተረዱትም፤ ልብ ማለት የነፍስ ስም ነው::

ማስረጃ ዮሐንስ አፈወርቅ:-

ንባብ:- "እስመ ነፍስ ትሰመይ ልበ ወልቡና”

ትርጉም:- “ነፍስ ልብ ልቡና ትባላለች” ብሏል:: /ድርሳን ፪ኛ/

አትናቴዎስ ዘእስክንድርያም አስራ አንደኛ:-

ንባብ:- "ወልቡ ለብእሲ መንፈሱ ወውእቱ ፩ ምስለ ነፍሱ እንተ ሃለወት በሥጋሁ::”

ትርጉም:- የሰው ልቡ ነፍሱ ነው ይኸውም በሥጋው ካለች ነፍሱ ጋራ አንድ ነው" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[56]

---

[56] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፳፭ ቁ. ፳፮

እንዲህ የተባለች ነፍስ ተዋሕዶ ዕውቀትዋን ስለሣለችበት "በስመ ኀዳሪ ይጸዋዕ ማኅደር" እንደተባለ ማኅደር በኀዳሪው ስም መጠራት ልማድ ነውና፣ በማኅደርነቱ ልብ ተብሏል እንጅ፣ ልብ መባል የራሱ ስም አይደለም:: እርሱስ እንደ ሳንባና ጉበት ያለ አካል ነው:: አንዳንድ ሰዎች የነፍስ የዕውቀቷ ሰሌዳ የሆነ ይህ አካል ልብ በመባሉ ተሳስተው በየራሳቸው ልብ የሚባል አካል ከሌላቸው፣ ሥላሴ በአካል ፍጹማን አይባሉም እያሉ የስህተት ቃል ይናገራሉ፤ ይልቁንም በልብ አስጠግተው ምክንያት የሌላቸውን ቃልንና እስትንፋስን እንደ አካል አድርገው "በየራሳቸው ቃል፣ እስትንፋስ ከሌላቸው አካለ ጎደሎ ያሰኛል" ማለታቸውን አስተዋይ ልቡና ያለው ሰው እውነት ብሎ ሊቀበለው የማይቻል ነው::

፲፩ኛ አንቀጽ

*መለኮት ከአካል የማይለይ አንድ ሲሆን፣ ወልድ ሰው ሆነ በተባለ ጊዜ፣ ሦስቱ ሰው ሆኑ እንዳያሰኝ ይናገራል*

መለኮት ከአካል የማይለይ አንድ ነው ብለን፣ ወልድ ሰው ሆነ ስንል፣ ሦስቱ ሰው ሆኑ እንዳያሰኝ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር በምትባል ጥበብ ሆነን፣ የረቀቀውን በማጉላት፣ የጎደለውን ለመሙላት እየመረመርን፣ መላልሰን እናስረዳለን::

ለሥላሴ በግብር የሚጠሩባት ባሕርይ የምትባል አሐቲ ጠባይዕ አለቻቸው፤ ግብሯም ሕይወትነት ነው:: ነገሩን ኋላ በአሥራ ሁለተኛው አንቀጽ እናመጣዋለን:: የዚህችም ጠባይ ጥንታዊና መሠረታዊ የሚሆን ስምዋ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር የማይችል ነው:: አለመቻሉንም ሲአስረዳ ዮሐንስ አፈወርቅ በ፪ኛው ድርሳኑ:-

ንባብ:- "እስመ ሶበ ኢረከበ ስመ ዘይኤምር ኀበ ባሕርይሁ ብህለ በዝንቱ አስማት፤ እስመ ኢዕበይ ወኢስብሐት ይኤምሩ ኀበ ውእቱ ስም ዘፈቀደ ይዝክሮ፤ ወባህቱ ስእነ ረኪቦቶ በከመ እቤ ቀዳሚ ከመ ንሕነ ንኄሊ በእንተ ብዙኀ ግብራቲሁ ወንስዕን ፈክሮ ወነጊረ በእንቲአሁ፤ እወ ካዕበ ወኢ ዝስም ዘውእቱ እግዚአብሔር ኢይኤምር እንከ ኀበ ውእቱ ባሕርይ፣ ወፍጹመ ኢይትከሀል ይርከቡ ስሞ ለዝኩ ባሕርይ፤ ኢታንክር ኦ ፍቁር በእንተ ዝንቱ፤ ኅድግሰ ባሕርየ እግዚአብሔር ልዑል፤ ለመልአክኒ ጥቀ ኢይትረከብ ስመ ባሕርይሁ:: ወበእንተ ነፍስኒ ከማሁ ይመስለኒ፤ እስመ ብሂለ ነፍስ ኢይኤምር ኀበ ስመ ባሕርይሃ፤ ... ወአልቦ እንከ ስም ዘይትአወቅ ለባሕርይሃ"

ትርጉም:- "ባሕርዩን የሚያስረዳ ስም ባያገኝ፣ ዕበይ ስብሐት በማለት የባሕርይ ስሙን ተናገረ:: ዕበይ ስብሐት ማለት ሊናገረው የወደደውን የባሕርይ ስሙን ምንም ባያስረዳ አስቀድሜ እንደተናገርሁ እኛ ብዙውን ሥራውን እንድንመረምር ሥራውን ተረድተን መናገርም እንዳይቻለን የባሕርይ ስሙን ማግኘት ባይቻለው ይህን ተናገረ እንጅ:: ዳግመኛም ይህ ስም ይኸውም እግዚአብሔር ማለት የማይመረመር ባሕርይውን እንዳያስረዳ እውነት ነው፤ የዚያን ባሕርይ ስሙን ማወቅ ፍጹም አይቻልም:: ወዳጅ ሆይ ስለዚህ ነገር አታድንቅ የልዑል እግዚአብሔርስ የባሕርይ ስሙ ይቅርና የመላእክስ እንኳ የባሕርይ ስሙ አይታወቅም፤ የነፍስም ነገር እንደዚሁ ይመስለኛል፤ ነፍስ መባል የባሕርይ ስሟን አያስረዳምና፤ እንግዲያስ ለባሕርይዋ የሚታወቅ ስም የለም" ብሏል:: ይህችም ጠባይ በልብነቷ ከዊን ከወላዲ አካል ስትኖር መቅደም፣ መከተል፣ ጥንት፣ ፍጻሜ ሳይኖርባት፣ በቃልነቷ ከዊን በተወላዲ አካል፣ በእስትንፋስነቷ ከዊን በሰራጺ አካል የነበረች ያለች የምትኖር ናት::

ማስረጃ:- ከአረጋዊ መንፈሳዊ

ንባብ:- "አብሰ ጠባይዕ ውእቱ፤ ወልድኒ ወመንፈስ ቅዱስ ኃይላቲሁ፤ አልቦኬ ዘይኄሊ በእንተ አካላት ስቡሓት ከመ ፩ዱ ይቀድም እምነ ፩ዱ እስመ ጠባይዒሆሙ ሀሎ ዕሩየ እንበለ ጥንት"

ትርጉም:- "አብ የእውቀትና የሕይወት መገኛ ልብ ነው፤ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን ኃይሉን የሚገልጥባቸው አእምሮና ሕይወት ናቸው፤ ከሚመሰገኑ አካላትም አንዱ ከአንዱ እንዲቀድም፣ የሚያስብ አይኑር፤ መገኛቸው አብ ሳይቀድም ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዕሩይ ሆኖ ነበርና (ኑሯልና)" ብሏል:: ይህ ዕሪና የዘመን ነው:: /ድርሳን ፳፪ኛ/

የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ኬራኮስም ፴፫ኛ:

ንባብ:- "ወ፫ቱ አካላት ዕሩያን በኩሉ ግብር፤ እስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እምኔሁ ለአብ፣ ወጥንተ ቅድምና እሙንቱ ዘከመ አብ፣ ወአሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ"

ትርጉም:- "ሦስቱ አካላት በሥራው ሁሉ አንድ ናቸው፤ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ተገኝተዋልና፣ እንደ አብ ቅድምና ያላቸው ጥንት ናቸውና፣ የሦስቱም ቅድምና አንዲት ናት" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[57]

በሦስቱ አካላት አለች ማለታችንም በራስዋ መከፈል፤ በከዊንዋ መለየት ሳይኖርባት፤ በሕልውና ነው፤ ሕልውናውም ሦስቱን አካላት ማገነዘብ ነው::

[57] ሃይማኖተ አበው ዘኪራኮስ ምዕ ፺፩ ቁ. ፰

ማስረጃ ከዮሐንስ አፈወርቅ

ንባብ:- "እስመ አርአያ ባሕርይ ካልዕ ውእቱ እም ቀዳሚ ሥርው፤ ወባህቱ ኢፍሉጥ ውእቱ ከዋኔሁ በግዕዘ ጠባይዕ ወስምረት፣ ዘእንበለ በአካል ባህቲቱ"

ትርጉም:- "አብን የሚመስል ወልድ፤ በቅድምና ከተገኘበት ከአብ ልዩ ነው፤ ነገር ግን ልዩነቱ በአካል ብቻ ነው እንጂ፤ በባሕርይ ሥራና በፈቃድ አይደለም" እንዳለ:: /ድርሳን ፪/

ማስረጃ ከአረጋዊ መንፈሳዊ

ንባብ:- "ወአልቦ ጊዜ አመ ነበረ እንበለ አእምሮ ወሕይወት::"

ትርጉም:- "ያለ እውቀትና ያለ ሕይወት የኖረበት ጊዜ የለም" ብሏል:: /ድርሳን ፳፪ኛ/

ዳግመኛም

ንባብ:- ዳግመኛም "ነጽርኬ ዘተብህለ በእንተ አበ ኩሉ ከመ መሰልዎ በዛቲ ባሕር እንተ ትትገሠሥ፤ ለወልድኒ ዘይሴባህ በኀበ ኩሉ መሰልዎ በርጥበተ ማይ፤ ወለመንፈስ ቅዱስኒ ዘይሴባህ በሁከተ ማይ በውስተ ባሕር፤ ለመኑ ይትከሀሎ ከመ ይፍልጥ ኃይለ ባሕር እምነ ጠባይዒሁ፤ ይተከሀሎኑ ከመ የሀሉ ባሕር እንበለ ርጥበት፤ ወዘእንበለ ተሀውኮ:: ወለመኑ ይተከሀሎ ይፍልጥ ሁከተ እምነ ማይ ወባሕር ወያቅማ በባህቲታ፤ ለማይኒ ወለርጥበት በበባህቲቶሙ:: አው መኑ ዘርእየ አሐደ እምኔሆሙ እንዘ ይቀውም በባህቲቱ፣ ዘእንበለ በትሥልስቱ፤ እስመ ፩ እሙንቱ እንዘ ፫ቱ:: ወእንዘ ፫ አሐዱ ይትበሀሉ:: ወሶበሂ ይትኔጸር ወይትሌለይ በ፫ አካላት፣ ይትሔለይ ምስለ ኃይላቲሁ፤ ወኢይትሌለዩ ኃይላቲሁ እምጠባይዒሁ፤ ወጠባይዒሁ እምኃይላቲሁ፤ ወከመዝ እሔሊ በእንተ ጠባይዓት ስቡሐት::"

ትርጉም:- "የሁሉ መገኛ አብን ነፋስ በሚያማታት ባሕር ባለች በውሃ እንደ መሰሉት እወቅ፤ በሁሉ ዘንድ የሚመሰገን ወልድንም በውሃ እርጥበት እንደመሰሉት፤ በሁሉ ዘንድ የሚመሰገን መንፈስ ቅዱስንም፣ በባሕር ባለ በውሃ ሁከት ይመሰላል (ይመስላል):: የባሕርን ኃይል ከጠባዩ መለየት ለማን ይቻለዋል? ባሕር ያለ እርጥበትና ያለ መታወክ ሊኖር ይቻላልን? ሁከትን ከእርጥበትና ከስፋት ለይቶ ለብቻዋ ማቆም ለማን ይቻለዋል? ስፋትንና እርጥበትንስ ከሁከት ለይቶ ለብቻቸው ማቆም ለማን ይቻለዋል? ከእነዚህስ አንዱን ብቻውን ቁሞ ያየው ማን ነው? በሦስትነቱ ነው እንጂ:: ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸውና፣ ሦስት ሲሆኑም አንድ ይባላሉና፣ ሦስት ኩነታት እንዳለ ቢታይ ቢታሰብም፣ ስፍሐት ኃይሉን የሚገልጥባቸው እርጥበትና ሁከትም ከስፍሐት አይለዩም:: ስፍሐትም ከርጥበቱና ከሁከቱ:: ስለተመሰገኑ ጠባያትም እንዲሁ እናገራለሁ” ብሏል:: /ድርሳን ፴፷ኛ/

በዚህ ጊዜ ጠባይዓት የተባሉት ኩነታት እንደሆኑ፤ አንዲት ጠባይም ሦስትነት ባለው ከዊን፣ በሦስት አካላት እንዳለች ያስተውሏል:: እንዲህም ሲሆን፣ ተወላዲ ቃለ እግዚአብሔር በተወላዲነት ፀንቶ ቢኖር አካሉ ባለች የጠባይ ከዊን ሰው ሆነ እንላለን ጠባይ የሌለው አካል የለምና::

ይህንም የሚያስረዳ ኪራኮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያ:-

ንባብ:- "ኢይደሉ ይኩን ሕላዌ ዘእንበለ አካል፤ ወኢይደሉ ይትረከብ አካል ዘእንበለ አምሳሉ፤ ዘውእቱ አርአያሁ::"

ትርጉም:- "ባሕርይ ያለ አካል ሊኖር አይችልም፤ አካልም አካልን ከሚመስለው ከጠባይ ጋር ነው እንጂ፣ ብቻውን ሊገኝ አይችልም፤ ይኸውም መታወቂያው ነው" ብሏል:: (ክፍል ፩ ሃ. አበው)[58]

እንዲህም ባልን ጊዜ ጠባይ ተከፍሎ ባይኖርባት፣ በከዊን በሦስቱ አካላት ትገኛለች ብሏልና፣ ሦስቱ አካላት ሰው ሆኑ እንዳያሰኝ ማስተዋል ነው:: መለኮት፣ አምላክ ማለት፣ የጠባይ ስማቸው አይደለም:: በአንድነት ፈጥረው ስለገዙ መለኮት ስለተመለኩም አምላክ የሚያሰኛቸው በአንድነት የሚጠሩበት የባሕርይ ግብር ስማቸው ነው እንጅ:: እንዲህም ከሆነ ዘንድ ዮሐንስ አፈ-ውርቅ:- "የእግዚአብሔር የባሕርይ ስሙ አይገኝም" ብሎ ነግሮናልና፣ ልዩነት እንዳለበት በሰባተኛው አንቀጽ ለይተን ካሳየነው ምክንያት በቀር፤ እግዚአብሔር ማለትና መለኮት ማለት ምስጢሩ አንድ ነው:: ይህንም የሚያስረዳ ዮሐንስ ዘእስክንድርያ:-

ንባብ:- "እኁዛን እሙንቱ በጽምረተ ፩ መለኮት ወበዝንቱ ፩ መለኮት ይሰመዩ እግዚአብሔር”

ትርጉም:- በአንድ መለኮት አንድ አድራጊነት የተገናዘቡ ናቸው፤ በዚህ በአንድ መለኮት እግዚአብሔር ይባላሉ" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩ ፸፩ ኛ)[59]

ማስረጃ ከባስልዮስ ዘአንጾኪያ:-

ንባብ:- “አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር፤ እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ እስመ ፩ ውእቱ መለኮተ ሥላሴ፤ ወሠለስቲሆሙ ፩ እሙንቱ በመለኮት”

---

[58] ሃይማኖተ አበው ዚኪራኮስ ምዕ ፺፩፥፳፰ ክፍል ፩
[59] ሃይ. አበው ምዕ ፺፩፥፲-፲፩

<u>ትርጉም</u>:- "እኔ እግዚአብሔር ባልሁ ጊዜ እግዚአብሔር ማለትን ስለ አብ፣ ስለ ወልድ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ፤ የሦስቱ መለኮት አንድ ነውና፤ ሦስቱም በመለኮት አንድ ናቸውና" ብሏል:: (አንቀጽ ፩ እይ)[60]

እግዚአብሔር ማለትና መለኮት ማለት አንድ ከሆነ አፈወርቅም "እግዚአብሔር ማለት የባሕርይ ስሙን አያስረዳም" ካለ ፣ መለኮት ማለት ስሙ ለማይታወቅ ባሕርይ መጠሪያ ሊሆን የሚነገር ስሙ እንጂ፣ የጠባይ ስሙ እንዳይደለ በዚህ እንረዳለን:: መጻሕፍትም "መለኮት አምላክ ሰው ሆነ" ማለታቸው የጠባይ ስሙን ባያገኙት በግብር ስሙ ጠርተውት ነው:: ዳግመኛም "ወልድ ቃል ሰው ሆነ" ብለው አምላክ መለኮት ባይሉት፣ "ፍጡር" የሚሉ እነ አርዮስ፣ "ከመ፩ እም ነቢያት" የሚሉ እነ ንስጥሮስ፣ "ዝርው" የሚሉ እነ መርቅያን፣ ባልተረቱም ነበርና፤ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ በሚያደርገው፤ ሦስቱን በሚያገናዝባቸው ስም ጠርተውታል እንጂ፤ መለኮት በሦስት ይከፈላል ማለታቸው እንዳይደለ ጠንቅቆ ማስተዋል ነው::

*www.kidusyared.org*

60 ሃ.አበው ዘባስልዮስ ምዕ ፺፮፥፮

*፲፪ኛ አንቀጽ*

*የመለኮት ንባቡ አንድ ትርጓሜው ብዙ እንደሆነ ይናገራል:: መለኮት ንባቡ አንድ ሲሆን፣ ትርጓሜው ብዙ ነው*

<u>፩ኛ ብርሃን ይሆናል::</u>

ማስረጃ:- አግናጥዮስ:-

<u>ንባብ</u>:- "እጉዛን እሙእንቱ በፅምረተ ፩ መለኮት ዘውእቱ ብረሃን ዘይሰርቅ እምኔሁ ሥላሴ" እንዳለ:: [61]

<u>ጥያቄ</u>:- በዚህ አንቀጽ ብርሃን የተባለ መለኮት ከሦስት የሚከፈል ከሆነ፣ አንዱን ልብስ ሦስት ሰዎች ከሦስት እንዲለብሱ፣ ሦስቱ አካላት አንዱን ብርሃን ከሦስት ተካፈሉት ሊባል ይገባልን?

<u>መልስ</u>:- እኛስ በአብ አካል ያለች ብርሃን በወልድ አካልና በመንፈስ ቅዱስ ያለች አንዲት ብርሃን ናትና፣ "በአንድ መለኮት አንድ አድራጊነት፤ የተገናዘቡ ናቸው፤ ይህም መለኮት የአካል ሦስትነት የሚገኝለት አንድ ብርሃን ነው" ብሎ አግናጥዮስ ስለነገረ፤ ከሦስት የማይከፈል አንድ ብርሃን በሦስቱ አካላት እንዳለ እናምናለን::

*www.kidusyared.org*

[61] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፲፩፥ ፰-፱

ማስረጃ:- ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ፶፩ኛ

<u>ንባብ:</u>- "አብ ብርሃን ወልድ ብርሃን መንፈስ ቅዱስ ብርሃን ዳዕሙ ውእቱ ፩ ብርሃን ዘኢይትከፈል ወኢይትዌለጥ በህላዌ መለኮት"

<u>ትርጉም</u>:- "አብ ብርሃን ነው ወልድ ብርሃን ነው መንፈስ ቅዱስ ብርሃን ነው፤ ነገር ግን በመለኮት ሕላዌ የማይለወጥ የማይከፈል አንድ ብርሃን ነው" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[62]

## <u>፪ኛ ሕይወት ይሆናል</u>

ማስረጃ:- አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ:-

<u>ንባብ</u>:- "ኢተአምርኑ ከመለእመ ትቤ መለኮት ሞተ፣ ትከውን ቀታሊሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ እስመ ባሕርየ ሥላሴ ፩ ውእቱ  ዘውእቱ ፩ መለኮት"

<u>ትርጉም:</u>- "መለኮት ሞተ ብትል አንተ የሥሉስ ቅዱስ ገዳያቸው እንድትሆን አታውቅምን? የሥላሴ ባሕርይ አንድ ነውና፤ ይኸውም አንድ /ሕይወት/ መለኮት  ነው" ብሏል:: (ሃይ. አባው ክፍል ፩)[63]

በዚህ አንቀጽ መለኮት የተባለ ባሕርይ ሦስቱን አንድ የሚያደርግ አንድ ሕይወት እንደሆነ ያስተውሏል:: ሕይወት የተባለ መለኮት በአካል

[62] ሃይማኖተ  አበው ምዕ  ፻፲፬፥፪

[63] ሃይ.  አበው ምዕ  ፲፩፥፲፫-፲፬

ከሦስት የሚከፈል ከሆነማ አንዱ ቢሞት ሦስቱ ሞቱ እንደምን ባላሰኛቸውም ነበር? አንድ ቢሆን አይደለምን? በሕይወት ከሚመሳሰሉ ብዙ ሰዎች አንዱ ቢሞት ሁሉም ሞቱ ያሰኛልን::

፫ኛ አገዛዝ ይሆናል::

ማስረጃ:- ነቢዩ ዳዊት

ንባብ:- "ውስተ ኩሉ በሐውርት መለኮቱ"

ትርጉም:- "አገዛዙ በሀገሮች ሁሉ ነው" እንዳለ:: መዝሙር ፻፪፥፳፪

፬ኛ ጌትነት ይሆናል::

ማስረጃ:- ጳውሎስ

ንባብ:- "ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም"

ትርጉም:- “የዘለዓለም የሚሆን ኃይሉ ጌትነቱም እንዲህ ይታወቃል" እንዳለ:: (ሮሜ ፩፥፳)

ቅዱስ ጴጥርስም

ንባብ:- “ዘበኃይለ መለኮቱ ወኀበ ለነ ኩሎ ምግባረ ዘይወስድ ኀበ ሕይወት ወጽድቅ"

ትርጉም:- "በጌትነቱ ኃይል ወደ ሕይወትና ወደ ጽድቅ የሚወስድ ምግባርን የሰጠን" ብሏል:: (፪ኛ ጴጥ ፩፥፫)

ኄሬኔዎስም ፫ኛ:-

ንባብ:- ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ ዘሐመ ተሰቅለ በድካም፤ ሕያው ውእቱ በኃለ እግዚአብሔር"::

ትርጉም:- “ደክሞ የተሰቀለውና የሞተው በእግዚአብሔር ኃይል ሕያው ነው” ያለውን (፪ኛ ቆሮ ፲፫ ፥፬-፭) ሲተረጉም:-

ንባብ፡- "ወሐይወ በኃይለ እግዚአብሔር ዘውእቱ መለኮት"::

ትርጉም:- "በእግዚአብሔር ኃይል ተነሣ፣ ይኸውም መለኮቱ ነው" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[64]

በዚህ መለኮት የተባለ ጌትነት ወይም ሥልጣን እንደሆነ ማስተዋል ነው::

፫ኛ ክብር ይሆናል::

ማስረጃ:- ሐዋርያው ጴጥሮስ

ንባብ:- "ከመ በእንተ ዝንቱ ትኩኑ ሱቱፋነ ለመለኮተ ዚአሁ"

ትርጉም:- "ስለዚህ ነገር የክብሩ ተካፋዮች ትሆኑ ዘንድ ለምግባር ለትሩፋት ሁሉ" ፪ኛ ጴጥሮስ ፩፥፬ ባለው መረዳት ነው::

፬ኛ ባሕርይ ይሆናል::

ማስረጃ:-(፶፪ኛ) ዲዮናስዮስ ሊቀ ዻዻሳት ዘአንጾኪያ:-

ንባብ:- "ይሴለሱ በአካላት ወይትወሐዱ በመለኮት" እንዳለ አንቀጽ ፪ እይ::

*www.kidusyared.org*

[64] ሃይ. አበው ምዕ ፬፥ ፴

፯ኛ አምላክነት ይሆናል::

ማስረጃ (፹፫ኛ)/ዮሐንስ ዘአንጾኪያ

ንባብ:- "ይገብር መንክራተ በመለኮቱ፤ ወይትዌከፍ ሕማማተ በትስብእቱ"

ትርጉም:- “በአምላክነቱ ተአምራትን ያደርጋል፣ በሰውነቱ መቀበል” አንዳለ (ክፍል አንድ) እመልክተ ሲኖ. በ፲፭ኛው አንቀጽ፤ ነገሩን ኋላ በ፲፪ኛ አንቀጽም እናመጣዋለን ያልነው ይህ ነው::

ሲኖዲቆን ይህ ሁሉ አንድ የሚሆኑበትና የሚገናዘቡበት ነው እንጂ፤ የሚለያዩበት አይደለም:: ይህን ያህል ስህተት የሚያመጣ የመለኮትን የሚስጢሩን ስልት አስተውሎ አለመመልከት ነው:: መለኮት በአካላት የሚለይ ቢሆንስ፣ ሦስቱ ባልተጠሩበትም ነበረ:: ወላዲ፣ ተወላዲ፣ ሰራጺ ማለት በግብር፤ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ማለት በአካል፤ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ማለት በከዊን፤ የሚለያዩባቸው ስሞች ስለሆኑ፤ እየራሳቸው ተጠሩባቸው እንጂ ሦስቱ ሁሉ አልተጠሩባቸውም፤ አምላክ፣ መለኮት፣ ከዊን ማለት ነው:: እግዚአብሔር ማለት ግን በባሕርይ አንድ የሚሆንበት በሕልውና የሚገናዘቡበት በመሆኑ ሦስቱ ተጠሩበት::

ሐተታ:- ሦስቱ መለኮት ለማለት፤ ሳዊሮስ ዘገብሎን በተረፈ ቄርሎስ "እስመ ፫ቱ ኈልቄ መለኮቱ" ያለውን የሚጠቅስ ቢኖር፣ መልሱ ምሥጢሩን ባይመለከት ነው እንጂ ቢመረምረውስ ይህን ምስክር አድርጎ ባልተነሣም ነበር፤ አሁን በአርእስቱ እንደተናገርነው፤ሦስቱ ስለተጠሩበት "፫ ኈልቀ፦ መለኮቱ" አለ:: የሚዋሕዱበት አንድ እንደሆነ ሲያስረዳ መለኮቱ ብሎ በአንድ አንቀጽ ተናገረው:: እንደ

እነሱ አነጋገር ቢሆን ኖሮ ግን “መለኮታቲሆሙ” ባለ ነበረ እንጂ፣ መለኮቱ ባላለም ነበር::

ምሥጢሩም አትናቴዎስ ዘእስክንድር:-

ንባብ:- "አምላክ ውእቱ አብ፣ አምላክ ውእቱ ወልድ፣ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፤ ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ፤ አላ ፩ አምላክ"::

ትርጉም:- “አብ አምላክ ነው፣ ወልድ አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው፤ ነገር ግን አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ፣ ሦስት አምላክ አይባሉም” (ሃይ. አበው ክፍል ፬)[65] ብሏል::

ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ማለት በከዊን የሚለያዩበት በህልውና የሚገናዘቡበት እንደሆነ ከዚህ አስቀድመን በ፪ኛው አንቀጽ ተናግረናል:: ይህውም ሕያዋን የሚያሰኛቸው ሕይወት ነው፤ ሕይወትም እንደሆነ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ" ባለው በሰው ይታወቃል:: ሰው አእምሮው ንባቡ እስትንፋሱ የተለየው እንደሆነ ሞተ ይባላል፤ ካልተለየው ግን ሕያው ነው ይባላል እንጂ ሞተ አይባልም:: የእግዚአብሔር የባሕርዩን ከዊን ከሚመሰክሩ መጻሕፍት አንድ ደገኛ መጽሐፍ ሰው ነውና::

ማስረጃ:- ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስትጉቡዕ

ንባብ:- "ወኮንኩ መጽሐፎ ለክርስቶስ"

ትርጉም:- "የክርስቶስ መጽሐፍን ሆንኩ::"

ንባብ:- "ወየአምር መጽሐፈ እግዚአብሔር"

---

[65] ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ ምዕ ፷፰፥ ፬

ትርጉም፡- የእግዚአብሔር መጽሐፍ ሰው ያውቃል" እንዳለ፤ በ፲፩ኛው አንቀጽ ነገሩን ኋላ በ፲፪ኛ አንቀጽም እናመጣዋለን ያልነው ይህ ነው::

፲፫ኛ አንቀጽ

*ሥላሴ ዓለምን በአንዲት ቃል እንደፈጠሩ*

"ለሥላሴ በየራሳቸው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ አላቸው ካልተባለ፣ ሥላሴ በአካል ፍጹማን ናቸው አያሰኝም" ለተባለው ጥያቄ መልሱን ከነምስክሩ በ፲ኛው አንቀጽ አስረድተናል፤ ከዚያ የቀረውንም በዚህ አንቀጽ እንናገራለን:: ለሦስቱ አካላት በየራሳቸው ቃል አላቸው ማለት እንዳይገባ ቃላቸውም አንድ ወልድ ብቻ እንደሆነ የሚያስረዳ ነገር በሥነ-ፍጥረት እናሳያለን:: እግዚአብሔር በዕለተ እሑድ "ለይኩን ብርሃን" ካለ ጀምሮ፤ በዕለተ ዓርብ፣ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ" እስኪል ድረስ በነቢብ የፈጠረው ፍጥረት ብዙ ነው:: በማንኛቸው ቃል ተፈጠረ ይባላል በአብ በተለየ ቃሉ እንዳይባል ፍጥረት የተፈጠረ በወልድ ቃልነት እንደሆነ መጻሕፍት በብዙ አንቀጽ ይመሰክራሉ:: ከብዙም በትቂቱ የሚያስረዳ ዮሐንስ ወንጌላዊ:-

ንባብ:- "ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ"

ትርጉም:- "አስቀድሞ ቃል ነበረ" ብሎ ተነሥቶ

ንባብ:- "ወቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ እምዘኮነ"

ትርጉም:- "ሁሉም በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን የሆነ የለም ምንም ከሆነው ሁሉ" ብሏል:: ዮሐ ፩፥ ፪-፫

ቅዱስ ጳውሎስም:-

ንባብ:- "ወአሐዱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኲሉ በእንቲአሁ ወንሕነኒ ቦቱ"

ትርጉም፡- "አንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ እኛም በእርሱ" ብሏል:: ፩ቆሮ ፰፥፮

ዳግመኛም

ንባብ:- "ወበድኅሪሰ መዋዕል በወልዱ ዘረሰዮ ወራሴ ለኩሉ፤ ወቦቱ ፈጠሮ ለኩሉ"

ትርጉም:- “እርሱ በኋለኛው ዘመን በልጁ ነገረን፤ ሁሉን ወራሽ ባደረገው፣ ዓለሙንም ሁሉ በፈጠረበት" ብሏል:: ዕብ ፩፥ ፪

ከአረጋዊ መንፈሳዊ ማስረጃ

ንባብ:- "ወዓዲ ይሰመይ ወልድ በእንተ ዘተፈጥረ ቦቱ ኩሉ፤ ወካዕበ ወልድ ይሰመይ ቃለ፣ እስመ አእምሮቱ ለእግዚአብሔር ውእቱ"

ትርጉም:- “ዳግመኛ ሁሉ በእርሱ ስለተፈጠረ ወልድ ይባላል፤ ወልድም ቃል ይባላል፣ የእግዚአብሔር መታወቂያው ነውና" ብሏል:: /ድርሳን ፳፪/

አትናቴዎስም ዘእስክንድሪያ ፲፩ኛ ወደ አክኒጦስ በጻፈው መጽሐፍ[66]

[66] አክኒጦስ የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ ነበር። ሃ. አበው ምዕ ፳፱፥፩ ገጽ ፺

ንባብ:- “ኢንፈልጦ ለወልድ እምቃል፣ ከመ ካልእ ውእቱ፤ ወባሕቱ ንብል እስመ ቃል ውእቱ ወልድ ዘቦቱ ኩሉ ኮነ"

ትርጉም:- "ወልድን ከቃልነቱ ልዩ አድርገን አናወጣም፤ ወልድ ዓለም ሁሉ የተፈጠረበት ቃል ነውና፣ ወልድ ቃል ነው እንላለን እንጂ" ብሏል:: (ድርሳን ፲፰)[67]

ይህን የመሰለ በየአንቀጹ የተናገረው ብዙ ነው:: ደግሞ ይህን ተመልክተን በወልድ ቃልነት ብቻ ተፈጠረ እንዳንል፤ አብን ከፈጣሪነት ማውጣት ይሆናል፤ በዚኸውም ቃል አልፈጠረም እንዳንል ገንዘቡ ባልሆነ በሌላ ቃል ተናገሮ ፈጠረ ማለት ለልቦና አይረዳም:: ይህ ካልሆነ ብለን አብን ከፈጣሪነት እንዳናወጣውም በየአንቀጹ መጻሕፍት ይመሰክሩብናል::

ማስረጃ:- ሙሴ እስራኤልን /ንባብ/ "አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ፤ ፈጠረከሂ ወገብረከ"

ትርጉም:- "ይህ አብ የፈጠረህ አይደለምን? ፈጥሮ ወገን ያደረገህ አይደለምን? ብሎታልና::

ዘዳ ፲፪፥፮

በዚህ አንቀጽ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" ያለው የአብ ቃል እንደሆነ ያስረዳል:: ነቢይም

ንባብ:- "ወበቃለ እግዚአብሔር ፀንዓ ሰማያት፣ ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎሙ"

ትርጉም:- "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ተሠሩ፤

---

67 ሃ. አበው ምዕ ፴፩፥ ፵፩

ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ" ብሏል:: መዝ ፴፫ : ፮

ዮሐንስ ወንጌላዊ በቅዳሴው

ንባብ:- "ወኩሎ ተግባረከ ፈጠርከ በቃልከ"

ትርጉም "ፍጥረትህን ሁሉ በቃልህ ፈጠርህ" ብሏል::

አትናቴዎስም ዘእስከንድርያ

ንባብ:- "ፈጠረ አብ ኩሎ ፍጥረተ በቃሉ፣ ዘውእቱ እምነ መለኮቱ ወበመንፈሱ ቅዱስ"

ትርጉም:- "አብ ፍጥረቱን ሁሉ ከባሕርይው በተገኘ በቃሉና በቅዱስ መንፈሱ ፈጠረ" ብሏል:: (ሃይ. አበው ፲፫ ክፍል)[68]

ሠለስቱ ምዕትም ፫ኛ በፀሎተ ሃይማኖት

ንባብ:- "አብን ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ

ወዘኢያስተርኢ"

ትርጉም:- "ሰማያትና ምድርን የሚታየውንም የማይታየውንም የፈጠረ::"

ወልድንም

ንባብ:- "ዘቦቱ ኩሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ፣ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ"

ትርጉም:- "ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ በሰማይም በምድርም ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም" ብለዋል::

---

[68] ሃ. አበው ምዕ ፴፩÷ ፵፩

ይህን የመሰለ በየአንቀጹ የተነገረው ብዙ ነው::  ነገር ግን መጻሕፍት ፍጥረት ሁሉ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ገንዘብ በሚሆን በአንድ ቃል ተፈጠረ ሲሉ፣ ሦስቱን አካላት በአንድ መለኮት የማያገናዝቡ ሰዎች በየራሳቸው ሦስት ቃሎች አሉ ባሉ ጊዜ፣ በማናቸውም ቃል ተፈጠረ ይሉት ይሆን ወይስ በሠርግ፣ በዱለት፣ በገበያ የተሰበሰበ ሰው፣ ሁሉም በየቃሉ እየተናገረ፣ በአንድነት ሲጮህ እንዲሰማ፣ ሦስቱ አካላት በየቃላቸው አንድ ጊዜ ሲናገሩ ተሰሙ ይሉ ይሆን፣ መጻሕፍት በመሰከሩ ነው እንጂ፤ በጉሥዓተ ልብ አይደለምና፣ ይህ ከብዙ ስህተት የሚያደርስ ስለሆነ፣ ይህን ነገር ጠንቅቀን እናስተውል::

ክፍል ፩

ሦስቱን በአንድ ልብ እንዲያውቁ፣ በአንድ ቃል እንዲናገሩ፣ በአንድ እስትንፋሰ የሕይወት ሥራ እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው፣ ሦስቱን የሚያገናዝብ መለኮት አንድ ቢሆን ነበረ፤ መለኮት በአካል የሚለይ ሦስት ከሆነ ግን፣ ለሦስቱ በየራሳቸው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ አላቸው ማለት ግድ ነው::  እንዲህም ከሆነ መጻሕፍት የተናገሩት ቃል ሁሉ ሐሰት ሆነ ማለት ነው:: እኛስ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ብለው አብን ልብ፣ ወልድን ቃል፣ መንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ በማለት መጻሕፍት የመሰከሩት እውነት እንደሆነ አውቀን ተረድተን እናምናለን፤ ይህንም የሚያስረዳ አቡሊድስ:- "ወልድሂ ቃሎሙ ለአብ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ወመንፈስ ቅዱስሂ መንፈሶሙ ውእቱ ለአብ ወወልድ፤ ወበዝንቱ አእመርነ ከመ ፩ዱ ውእቱ መለኮተ ስላሴ፣ ወሎቱ ንሰግድ:: ወአበዊነሂ እለ ተጋብኡ በኒቅያ ይቤሉ እመቦ ዘይፈልጥ

መለኮቶ ለእግዚአብሔር አብ እም ወልድ ወእም መንፈስ ቅዱስ ውጉዘ ለይኩን ብለዋል"[69] ብሏል:: (አንቀጽ ፴፰ኛ ፩ እይ)[70]

የሐንስ ዘእስክንድርያም:-

<u>ንባብ:-</u> "አአምን በ፩ዱ አምላክ፤ ወአአምር ተዋሕዶተ ሥላሴ፤ ወሥላሴ በተዋሕዶ፤ ወተዋሕዶትኒ በእንተ ፩ መለኮት ዘ፫ አካት በአሐቲ ክብር፤ ወሥላሴኒ ዓዲ በእንተ ተዋሕዶተ አምላክኒ ዘ፫ አካላት ዘውእቶሙ:- አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ:: እስመ ምሥጢረ ሥላሴ ይትሌለይ በአካላት ወኢይትሌለይ በመለኮት፣ ወለእመኒ ንስምዮሙ ለ፫ አካላት በ፫ አስማት ኢንሬስዮሙ ሠለስተ አማልክተ፤ ወኢይከውን ዝንቱ፤ አላ ፩ አምላክ፤ ዘውእቱ አብ ምስለ ወልዱ ወመንፈስ ቅዱስ እምቀዲሙ እንበለ ፍልጠት::"

<u>ትርጉም</u>:- "በአንድ አምላክ አምናለሁ፤ አንድነት በሦስትነት፣ ሦስትነትም በአንድነት እንዳለም አውቃለሁ፤ አንድነትም በአንዲት ክብር ያሉ የ፫ቱ አካላት መለኮት አንድ ስለሆነ ነው:: ዳግመኛም በአምላካችን ተዋሕዶ ላይ የሚነገር ሦስትነትም አካላት ሦስት ስለሆኑ ነው:: እነሁም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: የሥላሴ ምሥጢር በአካል ይለያያል፤ በመለኮት ግን አይለይምና፣ ሦስቱን አካላትም በሦስት ስሞች ብንጠራቸው፣ ሦስት አማልክት አናደርጋቸውም:: ሦስት አማልክት ማለት አይገባምና፣ አንድ አምላክ ናቸው እንጅ:: ይኸውም ከጥንት ጀምሮ ያለመለየት ከልጁና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ የነበረ አብ ነው ብሏል::" /ሃይ. አበው ድርሳን ፩/ [71]

---

69 ወልድም ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ለአብ ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው፤ የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ በዚህ አወቀን ለርሱ እንሰግዳለን። በኒቂያ የተሰበሰቡ አባቶቻችንም አንዱን የእግዚአብሔር አብን መለኮት ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የሚለይ እንደኛ በአብ ትእዛዝ እንደተፈጠሩ የሚናገር፤ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከዚህ ከአንዱ ከአብ ባሕርይ አልተገኙም የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን ብለዋል።

70 ሃ. አበው ገጽ ፻፴፰ ምዕ ፴፱፥፰

71 ሃ. አበው ምዕ ፺፥፲

ዳግመኛም

<u>ንባብ:</u>- "እንዘ ሊሉያን እሙንቱ ይከውኑ ፩ እስመ መለኮተ ሥላሴ ፩ ወበሰለስቲሆሙ ሀሎ ፩ መለኮት::"

<u>ትረጉም</u>:- "ልዩ ሲሆኑ በአንድነት ይኖራሉ:: የሦስቱ መለኮት አንድ ነውና፣ በሦስቱም አካላት አንድ መለኮት አለና ብሏል::" /ሃይ.አበው ድርሳን ፩/[72]

፴፭ኛ ዮሐንስ ዘእስክንድርያም

<u>ንባብ</u>:- "ንሕነሰ ነአምን ከመ ወልድ ይትዋሐድ በመለኮት ምስለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ:: ወእመቦ ዘኢየአምን ከመ ፩ መለኮት ንሕነ ናውግዞ”

<u>ትርጉም</u>:- "እኛስ ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በመለኮት እንዲዋሐድ እናምናለን:: መለኮት አንድ እንደሆነ የማያምን ቢኖር ግን እኛ እናወግዘዋለን"[73] ብሏል:: ኪራኮስም ፴፮ኛ

<u>ንባብ:-</u> "ወእሙንቱ ይነብቡ በዘያብህም ልሳናቲሆሙ እንተ ኢኮነት ግሥጽተ:: አኮ ከመዝ ሃይማኖትነ ለነሰ ለርቱዓን፤ አላ ፩ አምላከ ንሰብክ፣ ወ፩ ሕላዌ ወ፩ መለኮተ፣ ወ፩ ኃይለ፤ ወኢንብል ከመ በዝየ ሱታፌ ለ ፫ አካላት፣ በከመ ይቤ ዮሐንስ ዘይሰመይ ተዐቃቢ ዘይትሜካህ በእበዱ ምስለ እለ ይብሉ ሠለስቱ አማልእከት ወሠለስቱ ሕላዌ ዘሠለስቱ አካላት:: አኮ ዝንቱ ንባበ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን::"

<u>ትርጉም</u>:- "ያልተሠራች ያልተቀጣች አንደበታቸውን ምላሽ የሚያሳጣ ነገርን ይናገራሉ:: የቀና እምነትን የምናምን የእኛ ግን፣ እምነታችን አንድ አምላክ ብለን ነው እንጅ፣ ሦስት አማልክት ብለን አይደለም:: በአንድ ኃይል ያለ አንድ ባሕርይ አንድ መለኮት እንደሆነ

---

72 ዝኒ ከማሁ ቁ. ፲፫

73 ዝኒ ከማሁ ምዕ ፺፥ ፲፭

እናስተምራለን:: በዚህ አንቀጽ መለኮትን አንድ ነው እንዳልነ፣ ልዩ ልዩ የሚሆኑ አካላትን አንድ የምንል አይደለንም:: በስንፍናው የሚመካ ተዐቃቢ የሚባል ዮሐንስ ሦስት አማልክት ከሚሉ ሰዎች ጋራ የሦስቱን አካለት በባሕርይ ሦስት እንዳለ፣ መለኮትን አንድ በማለታችን አካላትን አንድ አንልም:: ይህ የቅድስት ቤተክርስቲያን አነጋገር አይደለምና" ብሏል:: (ሃይ. አበው መልዕክት ፩)[74]

ዳግመኛም:-

ንባብ፡- "ንትዐቀብ ከመ ኢንምሀር በልሳናቲነ በዝንቱ መካን ከመ ንብል ሠለስቱ አማልክት ወ፫ ሐላውያት እስመ ዘይብል ዘንተ ናሁ ተሀበለ ያስተጋብዕ ሎቱ ብዙኃነ አማልክተ::"

ትርጉም:- "ሦስት አካላት በማለታችን ሦስት አማልክት ሦስት ሐላውያት የማለትን ትምህርት ለአንደበታችን ልማድ ከማድረግ እንጠበቅ:: ይህን የሚል ሰው እነሆ ብዙ አማልክትን ይሰበስብ ዘንድ ይደፍራልና" ብሏል:: (መልእ. ና. አበ)[75]

ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ፵፫ኛ

ንባብ:- "ንህነሰ ናሰትት[76] ቃሎሙ ለአላውያን እለ ይትአመኑ ብዙኃነ አማልክተ ወሐላውያተ ፍሉጣነ ለ፩ እግዚአብሔር ዘኢይትከፈል በሕላዌ መለኮት:: ወናወግዝ ዓዲ እለ ይብሉ ሠለስቱ መለኮት እንተ ዘአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ::"

ትርጉም፡- "እኛስ በመለኮት ባሕርይ ለማይለይ ለአንድ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ሐላውያትን የሚሰጡ ብዙ አማልክትን የሚያመልኩ የአላውያንን ትምህርታቸውን እንነቅፋለን:: ዳግመኛም የአብ የወልድ

---

74 ሃ.አበው ምዕ ፺፩፥ ፲-፲፩ ገጽ ፫፻፺፱
75 ዝኒ ከማሁ ቁ. ፲፮
76 የታተመው "ናዓትት" ይላል

የመንፈስ ቅዱስ የሚሆን መለኮትን ፫ የሚሉትን እናወግዛለን" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[77]

*ዳግመኛም:-*

<u>ንባብ</u>:- " ወሶበሂ ንቤ ሠለስቱ አካላት በበአካላቲሆሙ ንቤ ፩ ባሕርየ ፍጹመ፣ ወ፩ ሕላዌ ወ፩ መንግሥት ወ፩ እበይ ወ፩ ክብር ይትበሀሉ በእንተ እሉ ሠለስቱ አካላት አብ ብርሃን ወልድ ብርሃን መንፈስ ቅዱስ ብርሃን እንዘ ፩ ብርሃን ዘኢይትከፈል ወዘኢይትዌለጥ በሕላዌ መለኮት:: ወዓዲ ንብል አብ ሕይወት ወልድ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ሕይወት እንዘ ፩ ሕይወት:: ወካእበ ይተበሀል አብ ፩፤ ወልድ ፩ መንፈስ ቅዱስ ፩ ወለለ ፩ እምአካላት ፩ ሕላዌ ወ፩ አምላክ እሙንቱ:: ወኢይትበሀሉ ፫ አማልክተ አኮ ዘንተአመን በ፫ እደው ወ፫ አማልክት ወኢበ ፫ መለኮት:: አላ ንትአመን በ፫ አካላት ወ፫ ገጻት እንተ ፩ ባሕርየ መለኮት::"

<u>ትርጉም</u>:- "፫ አካላት በየአካለቸው አሉ ብንል፣ ፍጹም ባሕርይን ፩ ፣ ሕልውናንም አንድ ብለን፣ ፩ መንግሥት አንድ እበይ /ጌትነት/ አንድ ክብር ነው እንላለን:: አካላት ፫ ስለሆኑ በመለኮት ሕላዌ /አኗኗር/ የማይከፈልና የማይለይ አንድ ብርሃን ሲሆን፣ አብ ብርሃን፣ ወልድ ብርሃን፣ መንፈስ ቅዱስ ብርሃን ይባላሉ:: ዳግመኛም በመለኮት አኗኗር አንድ ሕይወት ሲሆኑ አብ ሕይወት፣ ወልድ ሕይወት፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው እንላለን:: ዳግመኛም አብ አንድ ይባላል፣ ወልድ አንድ ይባላል፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ ይባላል:: ከአካላትም እያንዳንዱ አንድ ሕላዌ አንድ አምላክ ናቸው:: ሦስት አማልክት ግን አይባልም:: መገናዘብ እንደሌላቸው ሰዎች አድርገን በሦስት ሰዎች በሦስት አማልክት፣ በሦስት መለኮት፣ የምናምን አይደለንም:: ባሕርየ መለኮት

---

77 ሃይማኖተ አበው ምዕ ፶፫፥፬

አንድ በሚያድርጋቸው በሦስት አካላት፣ በሦስት ገጻት እናምናለን እንጂ" [78] ብሏል::

ዳግመኛም:- ፵፫ኛ ዲዮናስዮስ ዘአንጾኪያ:-

ንባብ:- "ወንትአምን በዝንቱ ሕላዌ፣ ወንሰግድ አሐተ ስግደተ፤" ብሎ ተነሥቶ /አንቀጽ ፩

አይ/ "ንህነሰ ንሰብክ ከመዝ ወንሰግድ ለ፩ አምላክ ባሕቲቱ፣ ወንትአመን ከመ ፩ መለኮት ዘሠለስቱ አካላት፣ ወኢንበውእ ውስተ ከፊለ መለኮት ወመንግሥት:: አላ ንብል ፩ ሕላዌ፣ ወ፩ መንግሥት፣ ወአሐቲ ሥምረት፣ ወ፫ አካላት ወ፫ ገጻት እንበለ ተዘርዎ::"

<u>ትርጉም</u> "እኛስ እንዲህ እናስተምራለን፤ ለአንድ አምላክ ብቻም እንሰግዳለን:: የ፫ አካላት መለኮትም አንድ እንደሆነ እናምናለን:: መለኮትንም መንግሥትንም ወደ መክፈል አንገባም:: አንድ ሕልውና፣ አንድ መለኮት፣ አንድ መንግሥት፣ አንድ ፈቃድ፣ ያለመለያየትም፣ ሦስት አካላት፣ ሦስት ገጻት እንላለን እንጂ" ብሏል:: (እመልዕክተ ሲኖዲቆን)

ዳግመኛም:-

<u>ንባብ</u>:- "ውእቱሰ ፩ አምላክ ወአኮ ፫፡ ፩ እግዚእ ወአኮ ብዙኃን:: ወክብረ ምልክናሂ ልዑል ለመለኮት፤ ወበመለኮት ምልክና፤ ወቅድስት ሥላሴ ይእቲ ትትመለክ፤ ወትትአመር በ፫ አካላት:: ወተዋሕዶተ መለኮቶሙ ርሑቅ እምኩሉ ክፍለት፤ ወእመኩሉ ፍልጠት::"

---

[78] ሃ. አበው ዘዮሐንስ ምዕ ፻፲፬፥፬-፮

ትርጉም:- "እርሱስ አንድ አምላክ ነው እንጂ ፫ አማልክት አይደለም፤ አንድ ጌታ ነው እንጅ ሦስት ጌቶች አይደለም:: ከፍ ያለ የአምላክነት ክብርም ለመለኮት ነው፤ መግዛትም በመለኮት ነው:: ልዩ ሦስትነትም በሦስት አካላት እንዳለች ታውቋል፤ በአንድነትም ትመለካለች:: የመለኮታቸውም አንድነት ከመከፈል ከመለየትም የራቀ ነው" ብሏል:: (፳፫ኛ እመልዕክተ ሲኖዲቆን)

ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም:- "ወኢይትህበሉ ኅጉላን ያብኡ ውስተ ቅድስት ሥላሴ ፍልጠተ መለኮት" ብሏል:: (አንቀጽ ፩ እይ ሃይ. አበው ፪)

ሱኑትዮስ ዘእስክንድርያ:-

ንባብ:- "ዘኢየአምን ወዘኢይትአመን ከመ ፩ መለኮቶሙ፤ ወ፩ ህላዌሆሙ፤ እንተ ሠለስቲሆሙ፣ ወ፩ ቃሎሙ፣ ወ፩ ምግባሮሙ ውጉዘ ለይኩን::"

ትርጉም:- "ሦስት ሲሆኑ መለኮታቸው አንድ፣ ሕልውናቸውም አንድ፣ ቃላቸውም አንድ፣ ምግባራቸው አንድ እንደሆነ የማያምንና የማያሳምን የተለየ ይሁን" ብሏል:: (ሃይ. አበው ክፍል ፩)[79]

፴፱ኛ አትናቴዎስ ዘአንጾኪያም:-

"ወሶበሂ ንቤ ፩ እግዚእ ወ፩ ህላዌ ወ ፩ መለኮት"[80] ብሏል:: (አንቀጽ ፪ እይ)[81]

[79] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፻፲፥፴፩
[80] አንድ ጌታ አንድ አኗኗር አንድ ማለኮት ባልን ጊዜ
[81] ሃይማኖተ አበው ምዕ ፻፮፥፰

ባለቤቱም ጌታ በኦሪት:-

<u>ንባብ</u>:- "ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ" ብሏል::

<u>ትርጉም</u>:- "ከእኔ በቀር ሌላ ባዕድ አምላክ አታምልክ" አለ:: ዘጸ. ፳:፫፤ አንድ አድርጎ በአንድ አንቀጽ "ዘእንበሌየ" አለ እንጂ ከሦስት ለይቶ "ዘእንበሌነ" አላለም::

ዳዊትም:-

<u>ንባብ</u>:- "ወኢትስግድ ለአምላክ ነኪር፤ እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክ፤ ዘአውጻእኩከ እምድረ ግብፅ"

<u>ትርጉም</u>:- "ለባዕድ አምላክ አትስገድ፣ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና ከግብጽ ምድር ያወጣውህ አለ እግዚአብሔር" ብሏል:: መዝ. ፹፩፥፱ አንድ አድርጎ በአንድ አንቀጽ "አነ አምላክከ" አለ እንጅ፤ ከሦስት ከፍሎ አብዝቶ "ንሕነ አማልክቲከ" አላለም፤

ሙሴም በኦሪት:-

<u>ንባብ</u>:- "ስማዕ እስራኤል ፩ እግዚአብሔር አምላክከ"::

<u>ትርጉም</u>:- "እስራኤል እግዚአብሔር አምላክህ አንድ እንደሆነ ስማ ዕወቅ" ብሏል:: ዘዳ ፮፥፬

ጌታም በወንጌል

<u>ንባብ</u>:- "አነ ወአብ ፩ ንሕነ"

<u>ትርጉም</u>፡-"እኔና አብ አንድ ነን" ብሏል:: ዮሐ ፲:፴፩

*ዳግመኛም*

<u>ንባብ</u>:- "ለግብርየ እመኑ አንትሙ፤ ከመ ታእምሩ ወትጠይቁ፤ ከመ አነ በአብ፣ ወአብ ብየ"

<u>ትርጉም</u>:- በሥራየ እመኑ ታውቁ ትረዱም ዘንድ፣ አብ በእኔ እንዳለ፤ እኔ በአብ" ብሏል ዮሐ ፲:፴፰:: ይህ ሁሉ ቃል መለኮትንና አምልኮትን ከሦስት የማይከፍል ሦስቱን አካላት የሚያዋሕድና የሚያገናዝብ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው:: ይህንም የመሰለ በየአንቀጹ የተነገረው ብዙ ነው፤ ነገር ግን ሁሉን ልንጽፈው አይቻለንምና ከባሕሩ ገብቶ በየአንቀጹ መመልከት ነው::

<u>፲፬</u>ኛ አንቀጽ

*ኃይልና ክሂል ሥልጣንም በአካል የማይከፈሉ አንድ እንደሆኑ ይናገራል*

<u>ጥያቄ</u>:- የሥላሴ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን፣ በአካል ከሦስት ይከፈላል ማለት ይገባልን?

<u>መልስ</u>:- አይገባም፤ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን፣ በአካል የሚከፈል ሦስት ከሆነ፣ አእምሮ ንባብ ሕይወት የሌለው፤ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን የለውምና፤ አእምሮም ንባብም ሕይወትም ከሦስት ይከፈላል ያሰኛልና፤ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን የሚባል፤ አእምሮ ንባብ ሕይወት

እንደሆነ፣ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ"[82] በተባለው በሰው እንዲታወቅ፤ ከየመጻሕፍቱ እያመጣን በብዙ አንቀጽ እናስረዳለን::

<u>ንባብ</u>:- "እግዚአብሔር ገብሮ ለእጓለ እመሕያው ርቱዕ፤ ወገብረ ሕላዌሁ ከሀሌ"

<u>ትርጉም</u>:- "እግዚአብሔር ሰውን የቀና አድርጎ፤ ባሕርዩንም አዋቂ አድርጎ ፈጠረው"[83] ብሏል::

ይህንንም ንባብ ዮሐንስ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም ሲተረጉም ፳፬ኛ

<u>ንባብ</u>:- "ይብል ዘንተ ከመ ቦቱ ሥልጣን በርእሱ ባሕቲቱ፤ ወይክል ያቅም ትሩፋተ"

<u>ትርጉም</u>:- "ከሃሊ ማለትን በራሱ ብቻ ሥልጣን እንዳለው፣ ትሩፋቱን መፈጸም እንዲቻለው ሲያስረዳ ይህን ተናገረ ብሏል::" (ክፍል ፩ ብቻ)[84]

ማቴዎስም በወንጌል ጌታችን ለሐዋርያት ምሳሌ መስሎ ሲያስተምራቸው ሰምተው ቤተ አይሁድ እንዳደነቁ ሲጽፍ:-

<u>ንባብ</u>:- "እምአይቴ ሎቱ ዝንቱ ኵሉ ጥበብ ወኃይል"

<u>ትርጉም</u>:- "ለእርሱ ከወዴት ተሰጠው፤ ይህ ሁሉ ጥበብ ኃይልስ አሉ" አሉ:: ማቴ ፲፫:፶፬

ኃይል ያለውን ንባብ አእምሮም እንደሆነ ያስተውሏል::

[82] ዘፍ ፩፥ ፳፮
[83] ጥበበ ሰሎሞን ፪፥፳፫
[84] ሃ.አበው ምዕ ፺፪፥ ፲፭

ቅዱስ ጳውሎስም

<u>ንባብ</u>፡- "ወብነ ዝንቱ መዝገብ ውስተ ንዋየ ልሕኩት፤ ከመ ይኩን ዕበየ ኃይል ዘእምኀበ እግዚአብሔር፤ ወአኮ ዘእምኀቤነ"

<u>ትርጉም</u>፡- "ይህም መዝገብ /ነፍስ/ በሸክላ ዕቃ አለን::፡የኃይል ታላቅነት ከእኛ ያይደለ ከእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ" አለ:: (2 ቆሮ ፬፥፯-፰)

የዚህም ምሥጢሩ ከእግዚአብሔር የተገኘ ብዙ እውቀት ይሰጠን ዘንድ፣ በሥጋችን ነፍስ አለች ማለት ነው:: ኃይል ያለው ለነፍስ የተሰጠ እውቀት መሆኑን ያስተውሏል::

አሞንዮስና አውሳብዮስም፤ የአዳምን ተፈጥሮ ሲናገሩ፣ በመቅድመ ወንጌል

<u>ንባብ</u>፡- "ወተፈጸመ ፍጥረቱ ለአዳም በዝንቱ ዘቦ ውስቴቱ ፫ ኃይል፤ ኃይለ ዘርዕ፤ ኃይለ እንስሳ፤ ወኃይለ ንባብ፤ ወኃይል እንስሳዊት ህውከት ይእቲ ዘበስምረት ወይእቲ ባ እምነ አእምሮ

ወበዘባቲ ኃይል ዘይእቲ እንስሳዊት ወውስቴታ ይትረከብ ነጽሮ ወሰሚዕ"

<u>ትርጉም</u>፡- "የአዳም ተፈጥሮ ኃይለ ዘርእ፣ ኃይለ እንስሳ፣ ኃይለ ንባብ ባለው በዚህ በሦስቱ ኃይል ፍጹም ሆነ:: ኃይለ እንስሳ የተባለችው እንስሳዊት እውቀት በፈቃድ የምትነሣሣ ናት:: ለዚህችውም ከእውቀት ወገን አላት፤ ባላትም እውቀት ይችውም እንስሳዊት ናት:: በእሷም ማየት መስማትም ይገኛል፤" ብለው ሁሉን ቆጥረው ተናግረዋል:: (መቅድመ ወንጌል)

"ኃይለ ንባብ" ያሉትንም:-

ንባብ፡- "ዛ ይእቲ ማኅተመ ሕይወት መንፈሳዊት፣ እንተ ባቲ አክበሮ እምኵሉ ፍጥረት ዘታሕተ ሰማይ፤ ወትትዐወቅ በኃይለ ንባብ:: ዛ ይእቲ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር ወአምሳሊሁ፤ ኩናኒተ ሥጋ ወኃይሉ፤ በእንተ ዘኮነት አሐተ ውስተ ኵሉ፤ ወባቲ ይትረከብ ጥበብ ዘየሐስብ ወየኀሪ ልብ፤ ወአእምሮ አዝማን፤ ወመካናት፤ ወኵሉ ምግባራት እንተ ትከውን በዘይእቲ ላዕሌሁ:: በሥልጣን ባሕታዊት ሥዕልት ዘእንበለ ገቢር:: ወገብረ ላቲ ሥልጣነ ውስቴታ ትግብር ዘከመኀርየት፤ እንዘ አልቦ ዘይኴንና ወዘይሄይላ፣ ከመ ትኩን ሠናያቲሃ ወእከያቲሃ በስምረተ ኀሊናሃ፤ በአምሳለ መላዕክት"

ትርጉም፡- "ይህችም መንፈሳዊት የምትሆን ከሰማይ በታች ካለው ፍጥረት ሁሉ ለይቶ እርሱን ያከበረባት የሕይወት ፍጻሜ ናት:: ምሥጢርንም በመናገር ትታወቃለች፤ የእግዚአብሔር መታወቂያው፤ የምትመስለውም ናት:: ሥጋን የምትገዛው ዕውቀቱም ናት:: በሥራው ሁሉ አንድ ስለሆነች ልብ የሚሻው የሚመረጠውም ጥበብ ዘመኖችንና ቦታቸውን ማወቅ በእርሷ ይገኛል:: የሚሠራውም ሥራ ሁሉ ሥጋን በተዋሐደች በእርሷ ነው:: በዕውቀት ልዩ ናት፤ ግብር እመግብር ያልተፈጠረች ናት:: በጐነቷም ክፉነቷም በመላዕክት አምሳል በራሷ ፈቃድ ይሆን ዘንድ፤ የሚገዛት የሚያዛትም ሳይኖር እንደወደደች ልትሠራ:: የምትሠራበትንም ስልጣን/ዕውቀት/ ለእርሷ ሰጧት ብለዋል"[85] ብሏል::

ፊልክዩስም

ንባብ፡- "ወእንተሰ እምፍጥረታ ባቲ ሥምረት፣ ክሂል፣ ወፍትወት፣ ለገቢረ ጽድቅ ወአእምሮ ዘበአማን"

[85] ዝኒ ከማሁ መቅድመ ወንጌል

ትርጉም፡- "ከተፈጠረች ጀምሮ የተሰጣት ፈቃድ ዕውቀትም መሻትም ጽድቅን ለመሥራትና እውነተኛውን እውቀት ለማወቅ ነው" ብሏል::

አሁን ከዚህ በላይ እንደተናገርነው፣ ኃይልም ክሂልም ሥልጣንም የተባለ፣ አእምሮና ንባብ ሕይወትም እንደሆነ፤ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" በተባለ በሰው የታወቀ የተረዳ ሲሆን፣ ኃይል ስልጣን ክሂል እንደ አካል ከሦስት ይከፈላል ማለት፤ በሦስቱ አካላት በየራሳቸው ሦስት ልብ፣ ሦስት ቃል፣ሦስት እስትንፋስ አሉ ማለት እንደሆነ ታወቀ ተረዳ፤ እንዲህም ከሆነ፣ የዚህ ሃይማኖት መንገድ የዮሐንስ ተዐቃቢ መንገድ መሆኑ የማይጠረጠር ነው::

ክፍል ፩

አንዳንድ ሰዎች እንደሚናገሩት ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን፣ በአካል ከሦስት የሚከፈልና የሚለይ ከሆነ፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ በእመቤታችን በድንግል ማሕፀን ሥጋን ፈጥሮ በተዋሐደ ጊዜ የተዋሐደውን ሥጋ በማን አካል ባለ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን ፈጥሮ ተዋሐደ ይባላል፤ በራሱ ስልጣን ብቻ ፈጥሮ ተዋሐደ እንዳይባል፤ አብም መንፈስ ቅዱስም፤ ፈጥረው እንዳልተዋሐዱት መጻሕፍት በብዙ አንቀጽ ይመሰክራሉ::

/ማስረጃ/ ሰሎሞን

ንባብ፡- "ትቤ ጥበብ ፈጠረኒ እግዚአብሔር መቅድመ ተግባሩ"
ትርጉም፡- “ጥበብ ከፍጥረቱ ሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር ፈጠረኝ አለች" ብሏልና:: ምሳ ፰:፳፪

ይህንም ሲተረጉም ባስልዮስ ዘቂሣሪያ ፲፪ኛ

ንባብ፡- "ይብል ዘንተ በእንተ ልደቱ በሥጋ ከመ ውእቱ ፍጡር ወግቡር"

ትርጉም፡- “በሥጋ ስለተወለደው ልደት ፍጡር ግቡር እንደሆነ ሲያስረዳ "ፈጠረኒ" አለ” ብሏል:: (ሃይ አበው ክፍል ፩)[86] ዳግመኛም

ንባብ፡- "እስመ ብሂለ ወለደኒ ይተረጉም በእንተ መለኮት፤ ወብሂለ ፈጠረኒ ይትረጉም በእንተ ትስብእቱ"[87]

ትርጉም፡- "ወለደኒ ያለው ስለ መለኮቱ ይተረጉማል" ብሏላ:: (ሃይ አበው ክፍል ፪)[88]

ቴዎዶስዮስ ተአማኒ በጽድቅም ፴፩ኛ

ንባብ፡- "ወበእንተዝ ይቤ፤ ዝኩ ሥጋ ቅዱስ ጸርሐ እንዘ ይብል፤ ሊተ ለጥበብ ፈጠረኒ እግዚአብሔር እምቅድመ ተግባሩ፤ እስመ ዝኩ ሥጋ ቅዱስ ጥበብ ውእቱ ዘተነግረ በብዙኀ መክፈልት"

ትርጉም፡- "ያ ክቡር ሥጋ፣ ጥበብ እንደሆነ፣ በብዙ አንቀጽ ተነግርዋልና፣ ስለዚህ ያ ቅዱስ ሥጋ፤ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ አስቀድሞ፤ ጥበብ እኔን ፈጠረኝ ሲል አሰምቶ እንደ ተናገረ ሰሎሞን ተናገረ" ብሏል:: (ሃይ አበው መልዕክት ፪ኛ)[89]

---

86 ሃ. አበው ምዕ ፶፪፥፲፫

87 “እማሰ ለሊሁ ወልደ እግዚአብሔር ይቤ እስመ እግዚአብሔር ፈጠረኒ ለምንትኑ ይትማሰክ እንከ እስመ ብሄለ ወለደኒ ይተረጎም በወልደ እግዚአብሔር ውብሂለ ፈጠረኒ በእንተ ትስብእቱ”
ትርጉም፡- እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ፈጠረኝ ካለ እንኪያ ለምን አምሳክ ይባላል? ቢሉ ወለደኝ ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆኑ ፈጠረኝ ማለትም ሰው ስለሆኑ ይተረጎማልና”

88 ዝኒ ከማሁ ፶፪፥፲፰

89 ሃ. አበው ምዕ ፹፫፥፬-፮

ኢሳያስም

ንባብ፡- "ፈጠረኒ በውስተ ከርሥ ከመ እኩን ገብሮ"

ትርጉም፡- "አገልጋዩ እሆን ዘንድ በማሕፀን ፈጠረኝ አለ" ብሏል:: ኢሳ ፵፱:፫

ቅዱስ ጳውሎስም

ንባብ፡- "ምእመን ለዘፈነዎ"

ትርጉም፡- "ለላከው /ለሾመው/ የታመነ ነው" ያለውን ዕብ ፫:፪::

ኤጲፋንዮስም ፳፯ኛ

ንባብ፡-"ምእመን በኀበ ዘገብሮ"

ትርጉም፡- "በፈጠረው ዘንድ የታመነ ነው" ብሎታል:: (መልዕክት ፫)[90]

ቴዎዶስዮስም በ፫ኛው መልዕክት ፴፩ኛ

ንባብ፡- "በኀበ ዘፈጠሮ"

ትርጉም፡- "በፈጠረው ዘንድ" ብሎታል::

በማቴዎስ ወንጌልም

ንባብ፡- "እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ"

ትርጉም፡- "ከእርሷ የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ ነው" ያለውን ማቴ. ፩:፳:: ዮሐንስ አፈወርቅ ሲተረጉም:-

---

90 ሃ. አበው ምዕ ፺፬፥፺፱

ንባብ፡- "እስመ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ዘፈጠረ ውስተ ከርሠ ድንግል ሥጋሁ ለቃል፤ ውእቱ እምግብረ ስምረቱ ለመንፈስ ቅዱስ" /ትርጉም/ "በድንግል ማሕፀን ሥጋን የፈጠረ መንፈስ ቅዱስ ከፈቃዱ ሥራ የተገኘ ነው" ብሏል::

ዳግመኛ:-

ንባብ፡- "ፈጠረ ሎቱ እግዚአብሔር መቅደሰ ሕያወ በመንፈስ ቅዱስ"

ትርጉም፡- "እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሕያው መቅደስ ሥጋን ፈጠረለት" [91] ብሏል:: (ክፍል ፩)[92]

ይህን የመሰለ በየአንቀጹ የተናገረው ብዙ ነው፤ ይህን በመመልከት በአብ አካል ብቻ ወይም በመንፈስ ቅዱስ አካል ብቻ ባለ ሥልጣን ተፈጠረ እንዳይባል፣ ወልድ በገዛ ሥልጣኑ ሥጋውን ፈጥሮ እንደተዋሐደ መጻሕፍት ይመሰክራሉ::

/ማስረጃ/ ዘቂሣርያ ባስልዮስ ፲፪ኛ

ንባብ፡- "ወኢንብል እስመ አብ ፈጠረ ሎቱ፤ ከመ ኢንረስዮ ነኪረ እምነ መለኮቱ፤ አላ ለሊሁ ፈጠረ ለርእሱ፣ እስመ ቦቱ ምልክና ምስለ አብ በኵሉ ግብር"

ትርጉም፡- "አብ ብቻ ሥጋን ፈጠረለት አንልም፤ ከመለኮቱ ልዩ እንዳናደርገው እርሱ እራሱ ሥጋን ፈጠረ እንላለን እንጅ፣ በሥራ ሁሉ ከአብ ጋራ ሥልጣን አለውና" ብሏል:: (ድርሳን ፩ ማሪ ኤፍሬም)[93]

---

91 በታተመው ሃይማኖተ አበው ያለው ዘር ትንሽ ይለያል በምሥጢር ግን አንድ ነው

92 ሃ. አበው ምዕ ፷፯፥፯

93 ሃ. አበው ዘባስልዮስ ምዕ ፴፬፥፲፩

ንባብ፡- "ወእምኔሃ ነሥአ ሥጋ ዘውእቱ ፈጠረ፤ ወለሊሁ ፈጠረ ዘነሥአ"

ትርጉም፡- "እርሱ የፈጠረውን ሥጋ ከእርሷ ነሣ፤ የነሣውንም ሥጋ እርሱ ፈጠረ"[94] ብሏል:: (ድርሳን ፩)[95]

አውክንድዮስም

ንባብ፡- "ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጢረ ሥጋሁ አላ ለሊሁ ፈጠረ ለባሕቲቱ"

ትርጉም፡- "ሥጋውን በመፍጠር ማንም አጋዥ አልሆነውም፤ እርሱ ብቻ ሊዋሐደው፣ እርሱ ፈጠረው እንጂ" ብሏል:: (መልዕክት ፩)[96]

አትናቴዮስም ዘእስክንድርያ:-

ንባብ፡- "ወሥጋሁሰ ለእግዚእነ ግቡር ውእቱ እስመ ለሊሁ ገብሮ ለርእሱ"

ትርጉም፡- "የጌታችን ሥጋስ ፍጡር ነው፤ እርሱ ለራሱ ፈጥሮታልና" ብሏል:: (ሃ. አበው)

ክፍል ፲፬: ይህን የመሰለ የተናገሩ ሊቃውንት ብዙ ናቸውና፣ በየአንቀጹ እየገቡ መመልከት ነው:: ኃይል፤ ክሂል፤ ሥልጣን፤ በአካል ከሦስት የሚለይ ከሆነ፤ ይህ ሁሉ ንባብ በምን ምሥጢር ተስማምቶ ይገኝ ይሆን? እኛስ አባቶቻችን እንደነገሩን፣ ይህን ሁሉ ንባብ በምሥጢር በማስማማት፤ ወልድ በአካሉ ባለች በገዛ ሥልጣኑ

94 ከታተመው ሃይማኖተ አበው ዘር በቃል አገባቡ ይለያያል
95 ሃ. አበው ዘኤፍሬም ምዕ ፵፺፡፬
96 ሃ.አበው ምዕ ፵፬፡፫

ሥጋውን ፈጥሮ ተዋሐደ ብለን እናምናለን:: አምነን በወልድ አካል ያለች ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን፣ በአብና በመንፈስ ቅዱስ አካል ያለች አንዲት ናትና:: መጻሕፍት አንድነታቸውንና ሕልውናቸውን ለመንገር አብ ፈጠረው፤ መንፈስ ቅዱስ ፈጠረው እርሱ፤ እራሱ ፈጠረ ያሉትን የመጻሕፍትን ቃል አስማምተን፤ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን፣ ከሦስት የማይከፈል አንድ እንደሆነ እናምናለን::

*ክፍል ፪*

ዳግመኛ:- ጌታችን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሙቶ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በተነሣ ጊዜ፣ በማናቸው ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን ተነሣ ይባላል ይሆን? በወልድ አካል ብቻ ባለ ኃይልና ክሂል ሥልጣን ተነሣ እንዳይባል፤ እግዚአብሔር ከሙታን ለይቶ እንዳስነሣው፤ በእግዚአብሔር ኃይልና መንፈስ እንደተነሣ፤ መጻሕፍት ይመሰክራሉ::

/ማስረጃ/ ብፁዕ ጳውሎስ፤

ንባብ፡- "ወአርአየ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ውእቱ በኃይሉ ወበመንፈሱ ቅዱስ ከመ ተንሥአ እሙታን ኢየሱስ ክርስቶስ"

ትርጉም፡-"በኃይሉ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አሳየ፤ በቅዱስ መንፈሱም ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ" ብሏል:: ሮሜ ፩:፬

ዳግመኛም:-

<u>ንባብ</u>፡- "በከመ ውእቱ ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በስብሐተ አቡሁ፤ ከማሁ ንሕነኒ ናንሶሱ ውስተ ሐዳስ ሕይወት"

<u>ትርጉም</u>፡- "ክርስቶስ በአባቱ ጌትነት ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ እኛም እንደሱ ተነሥተን በአዲስ ሕይወት እንኖራለን" ብሏል:: ሮሜ ፮:፬

ዳግመኛም

<u>ንባብ</u>፡- "እመሰ መንፈሱ ለዘአንስኦ ለኢየሱስ እሙታን ዘኀዱር ላዕሌክሙ፤ ውእቱ ዘአንስኦ እሙታን ለኢየሱስ ያሐይዋ ለነፍስትክሙኒ በውእቱ መንፈሱ ዘየኀድር ላዕሌክሙ" <u>ትርጉም</u>፡- "ኢየሱስን ከሙታን ለይቶ ያስነሣው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ካደረባችሁ ኢየሱስን ከሞታን ለይቶ ያስነሣው እሱ መንፈስ ቅዱስ አድሮባችሁ ባለ በሕይወትነቱ ሥጋችሁን ሕያው ያደርጋታል" ብሏል:: ሮሜ ፰:፲፩

<u>ንባብ</u>፡- "እመ ከመ ተአምን በአፉከ ከመ ክርስቶስ ውእቱ እግዚእ፤ ወተአምን በልብከ ከመ አንሥኦ እግዚአብሔር እሙታን ተሐዩ"

<u>ትርጉም</u>፡- "በአፍህ ብትናገር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ፤ በልብህም ብታምን እግዚአብሔር ከሙታን ለይቶ እንዳስነሣው ትድናለህ" ብሏል:: ሮሜ ፲:፱

ይህን የመሰለ በየአንቀጹ የተነገረው ብዙ ነውና፣ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ምዕራፍና ቁጥር እየገቡ መመልከት ነው::

፩ኛ ቆሮ ፲:፲፬

ኤፌ ፩:፳

፩ኛ ጴጥ ፩:፳፩

የሐዋ ፪:፳፬

የሐዋ ፬:፲

የሐዋ ፳:፫

የሐዋ ፲፫:፴፬-፴፯

የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስም:-

ንባብ፡- "ተብህለ በእንቲአሁ ከመ አንሥኦ አብ እሙታን"

ትርጉም፡- “አብ ከሙታን ለይቶ እንዳስነሣው ስለ እርሱ ተነገረ" ብሏል::

ዮሐንስ አፈወርቅም

ንባብ፡- "ዘከመ ገብረ እዘዘ ኃይሉ ዘገብሮ በክርስቶስ ዘአንሥኦ እሙታን"

ትርጉም፡- "ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በክርስቶስ እንዳደረገው ተአምራቱ ብዛት" ያለውን ኤፌ ፩:፲፱-፳:: ሲተረጉም

ንባብ፡- "ትርጓሜሁ ለዝ እስመ በኃይል ዘቦቱ  አንሥኦ ለክርስቶስ ይስሕበነ ኀቤሁ"

ትርጉም፡- “የዚህ ትርጓሜው ክርስቶስን በአስነሣበት ኃይል አስነሥቶ ወደ እርሱ አቅረቦናል ማለት ነው" ብሏል:: /ድርሳን ፫/

ዳግመኛ:-

<u>ንባብ</u>፡- "ዘንተ ንብል በእንተ ዘውእቱ እምኔነ፣ ዝንቱ ዘአንሥአ እግዚአብሔር እምነ ሙታን" ትርጉም፡- "ከእኛ ባሕርይ ስለተገኘ ሥጋ ይህን እንናገራለን፤ ይኸውም እግዚአብሔር ከሙታን ለይቶ ያስነሣው ነው" ብሏል:: /ድርሳን ፫/

ዳግመኛም:-

<u>ንባብ</u>፡- "ወሶበ ትሰምዑ ቃለ ዘይብል ከመ እግዚአብሔር አንሥአ ለክርስቶስ፤ ኢተሐልዩ ከመ ውእቱ ይብል ዘንተ በእንተ ቃል አላ ይቤ በእንተ ሥጋ እግዚእነ"

ትርጉም፡- "እግዚአብሔር ክርስቶስን እንዳስነሣው የሚናገር ቃል ብትሰሙ፤ እርሱ ይህንን ስለ ቃል እንደተናገረ አታስቡ የተናገረ አይምሰላችሁ፤ ከእኛ ባሕርይ ስለነሳው ሥጋ ተናገረ እንጅ" ብሏል:: /ድርሳን ፬/

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሁሉ ተመልክተው በአብ አካል ብቻ ወይም በመንፈስ ቅዱስ አካል ብቻ ባለ ኃይል፣ ክሂል፣ ሥልጣን ተነሣ እንዳይሉ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ሥልጣኑ እንደ ተነሣ ሲመሰክር ቤተ አይሁድን:-

<u>ንባብ</u>፡- "ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሥሉስ ዕለት አነሥኦ"

<u>ትርጉም</u>፡- "ይህን መቅደስ አፍርሱት እኔ በሦስተኛው ቀን አስነሣዋለሁ" ብሏል ዮሐ ፪፥፲፱::

ይህንም ወንጌላዊ:-

<u>ንባብ</u>፡- "ውእቱሰ በእንተ ቤተ ሥጋሁ ይቤሎሙ"

ትርጉም፡- "እርሱ ግን መቅደስ ስለሚባል ሥጋው ነገራቸው" ብሎ ተርጉሞታል:: ዮሐ ፪፥፳፩

ዳግመኛም:-

ንባብ፡- "ወበእንተ ዝንቱ ያፈቅረኒ አብ እስመ አነ እሜጡ ነፍሰየ ከመ ካዕበ አነሥአ፤ ወአልቦ ዘየሀይደንያ ለልየ እሜጥዋ በፈቃድየ፤ እስመ ብውህ ሊተ አንብራሂ ወብውህ ሊተ ካዕበ አንሥአ"

ትርጉም፡- "ስለዚህ አብ ይወደኛል እኔ ነፍሴን እሰጣለሁና፣ ደግሞ አስነሳት ዘንድ ማንም ከኔ የሚወስዳትም የለም፤ እኔ በፈቃዴ እሰጣታለሁ እንጅ:: ለእኔ ችሎት አለኝ እሰጣት ዘንድ፣ ዳግመኛም ችሎት አለኝ አሥነሣት ዘንድ" ብሏል:: ዮሐ ፲፥፲፯-፲፰

ዳግመኛ:-

ንባብ፡- "አነ ውእቱ ትንሣኤ ወሕይወት"

ትርጉም፡- "እኔ ነኝ ትንሣኤ ሕይወትም" ብሏል ዮሐ ፲፩፥፳፭:: በመጻሐፈ ኪዳንም

ንባብ፡- "ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ"

ትርጉም፡- "በኔ ብቻ ሥልጣን ተነሣሁ" ብሏል::

እኛም ይህን ሁሉ ተመልክተን ወልድ በአካሉ ባለች በገንዘቡ ኃይል፣ ከሂል፣ ሥልጣን ተነሣ ብለን አምነን፤ በወልድ አካል ያለች ኃይል፣ ከሂል፣ሥልጣን በአብና በመንፈስ ቅዱስ አካል ያለች አንዲት ናትና፣ መጻሕፍት አንድነታቸውንና ሕልውናቸውን ለመንገር አብ አንሥአ፣ መንፈስ ቅዱስ አንሥአ እያሉ ስለመሰከሩ፣ "ወተንሣእኩ በሥልጣነ ባሕቲትየ" አለ ብለው ስለአስረዱ ኃይል፣ ከሂል፣ ሥልጣን ከሦስት የማይከፈል አንድ እንደሆነ እምነታችንን እንገልጻለን፤ በዚያውም ላይ

የአብ ኃይሉ ጥበቡ የሚባል እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ የሚያስረዳ ቅዱስ ጳውሎስ:-

ንባብ፡- "ክርስቶስ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ ወጥበበ እግዚአብሔር ውእቱ"

ትርጉም፡-"ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይል ነው፤ የእግዚአብሔር ጥበብም ነው" ብሎ ነግሮናል:: ፩ኛ ቆሮ ፩፥፳፬

*ክፍል ፫*

በኃይል፣ በክሂል፣ በሥልጣንም በሚሠራ በባሕርይ ሥራ በሦስቱ አካላት መለያየት እንደሌለ የሚያስረዳ ነገር፤ ከሙታን ተለይቶ መነሣት የክርቶስ አካል ብቻ ግብር ሲሆን፣ ማስነሣት የሦስቱ አካላት የባሕርይ ግብር ነው:: ስለዚህ ከሦስቱ አካላት ለሰው ሁሉ የሚሰጥ ሕይወት በአንድነት በሚሠራ በባሕርይ ግብር እንደሆነ መጻሕፍት ያስረዳሉና::

ቄርሎስ:-

ንባብ፡- " ፩ ሕላዌ ዘሥሉስ ቅዱስ ኲሉ ዕበይ ወኲሉ ክብር ይደሉ ለባሕቲቶሙ፣ ወኲሉ ዘኮነ በአምላክነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወለእመኒ ተብህለ በእንተ አብ ከመ ውእቱ ማሕየዊ፤ ዘእንበለ ኑፋቄ፤ እስመ ለዝንቱ ግብር ወልድኒ ይገብር፤ ወዓዲ ይገብሮ መንፈስ ቅዱስ፤ ወለእመኒ ወልድ ሕይወት በእለ ይፈቅድዎ ለሕይወት፣ እስመ ኢይገብር ዘንተ ዘእንበለ ፈቃደ አቡሁ፣ ዘይትዔረዮ፤ እስመ ቦቱ ለርእሱ ዘአብ ወላዲሁ፣ ወለሊሁኒ ይቤ ክሡተ ኢይገብር ግብረ ምንተኒ ዘእምኀቤየ አላ እገብር ግብሮ ለአቡየ ዘሀሎ ብዬ፤ ወለእመ

ተብህለ በእንተ መንፈስ ቅዱስ ከመ ውእቱ ማሕየዊ ዘእንበለ ኑፋቄ ይገብር ዘንተ እስመ መንፈሰ ሕይወት ውእቱ፤ ንሕነሰ ንብል እስመ ሕይወት ውእቱ በህላዌሁ እግዚአብሔር አብ:: ወወልድ ዋሕድ ዘተወልደ እምኔሁ፤ በዝንቱ አምሳል ሶበ ይትበሀል ከመ አብ አንሥአ ለክርስቶስ፣ ንሕነሰ ንረክብ ከመ ለሊሁ አንሥአ ርእሶ፣ ወይቤሎሙ ለአይሁድ ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወአነ አነሥኦ በሠሉስ መዋዕል"

<u>ትርጉም</u>፡- "በአካል ልዩ የሚሆን የሥላሴ ባሕርይ አንድ ነው፣ ፍጹም ጌትነት ፍጹም ክብርም ለሦስቱ ብቻ ይገባል፤ ፍጥረት ሁሉ በአምላካችን በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ተፈጠረ:: አብ ያለ ጥርጥር ያለ መለየት ማሕየዊ እንደሆነ ምንም ቢነገር ይህን ሥራ /ማዳኑን/ ያለመለየት ወልድ ይሠራዋልና፣ ወልድም ሕይወትን በሚሹ ሰዎች የሕይወትን ሥራ ቢሠራ በማስነሣት ሕይወት በሚተካከለው መተካከል በአካል ነው በአባቱ ፈቃድ ነው እንጅ ያለ አባቱ ፈቃድ ይህን አይሠራምና:: የወለደው የአብ ገንዘብ የእርሱ ገንዘብ ስለሆነ፤ እርሱም እራሱ በሕልውናየ ያለ "አባቴ የሚሠራውን እሠራለሁ እንጅ እኔ ከራሴ ብቻ አንቅቼ ምንም አልሠራም" ብሎ ገልጾ ተናግሯልና፣ መንፈስ ቅዱስም ማሕየዊ እንደሆነ ቢነገር ያለ መለየት ይህን ይሠራል የሕይወት መንፈስ ነውና፣ እኛ ግን እግዚአብሕር አብ በባሕርዩ ሕይወት እንደሆነ እንናገራለን:: ከእርሱ የተወለደ አንድ ልጁም በዚህ አምሳል/ማሕየዊ/ በመባሉ አብ ክርስቶስን አስነሣው ቢባል እኛ እርሱ ራሱ ራሱን እንዳስነሣ ከመጻሕፍት እናገኛለን:: አይሁድን "ይህን መቅደስ አፍርሱት እኔ በሦስተኛው ቀን አስነሣዋለሁ ብሏቸዋልና" እንዳለ:: /ክፍል ፶ ለጎበ ነገሥት ሄራን/

ዳግመኛ:-

<u>ንባብ</u>፦ "እግዚእነ ክርስቶስ ያነሥአነ ለኵልነ እስመ ሕያው ውእቱ በእንተ አቡሁ እስመ ዘተወልደ እምአብ ሕያው ዘለዓለም ወበእንተዝ ደለዎ ሎቱኒ ዓዲ ይኩን ሕይወተ፤ እስመ ዘተወልደ እምሕይወት ማሕየዊ"

<u>ትርጉም</u>፦ "ጌታችን ክርስቶስ ሁላችንን ያስነሣናል አባቱ ሕያው ስለሆነ እርሱም ሕያው ነው፤ ለዘለዓለም ሕያው ከሚሆን ከአብ ስለተወለደ ስለዚህም ሕይወት ይሆን ዘንድ ዳግመኛም ለእርሱ ተገባው፤ ሕይወት ማሕየዊ ከሚሆን ከአብ ተወልዷልና" ብሏል:: /ክፍል ፶/

ኪራኮስም ፻፷ኛ

<u>ንባብ</u>፦ "ንሕነሰ ፅኑዐን በጽድቅ ወንሰብክ እንዘ ንትአመን በሥሉስ ቅዱስ እለ ሕልዋን ቅድመ፣ ወይሄልው ለዓለም፣ ንጹሐን ፫ አካላት ፍፁማን፣ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ ሕላዌሆሙ ወ ፩ መለኮቶሙ ወ ፩ ግብሮሙ ወአሐቲ ሥምረቶሙ ወአሕቲ ክሂሎቶሙ ሕልዋን በዘዚአሆሙ:: ወአኮ አብ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር ዓዲ አኮ ወልድ ዘይገብር በርእሱ ባሕቲቱ ወአኮ መንፈስ ቅዱስኒ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር፣ አላ ዳዕሙ ለዘፈቀደ አብ ይፈጽምዎ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወምግባሮሙኒ ፩ እስመ ፩ ውእቱ መለኮቶሙኒ፤ አካላት ዕሩያን በአርአያ ወአምሳል ወመልክዕ"

<u>ትርጉም</u>፦ "በእውነት የፀናን እኛ ቅድመ ዓለም በነበሩ ለዘለዓለም በሚኖሩ በልዩ ሦስት አካላት አምነን፣ ፍጹማን የሆኑ ሦስቱ አካላት፣ ከመለየት ከመለወጥ ንጹሐን እንደሆኑ እናስተምራለን:: እኒሁም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: በሕልውና አንድ፣ በባሕርይም አንድ፣ በግብርም አንድ፣ በፈቃድም አንድ፣ ሁሉን ማድረግ በመቻልም አንድ

እንደሆኑ እናስተምራለን:: /በዘዚአሆሙ/ በሚገናዘቡበት በልብነት፣ በቃልነት፣ በእስትንፋስነት በየራሳቸው፣ በወላዲነት በተወላዲነት በሠራጺነት የሚኖሩ ናቸው:: አብ በተለየ አካሉ ብቻውን ሥራ የሚሠራ አይደለም፣ ወልድም በተለየ አካሉ ብቻውን ሥራ የሚሠራ አይደለም፤ አብ ያሰበውን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ይሠሩታል እንጅ፣ ግብራቸውም አንድ ነውና፤ ሦስቱ አካላት በግብርና በመመሳሰል በቅርጽም የተካከሉ ናቸው" ብሏል:: /ክፍል ፩/

ከዚህ በላይ እንደተነገረ ከሦስቱ አካላት ለዓለሙ ሁሉ የሚሰጥ የዘለዓለም ሕይወት በአንድነት በሚሠራ ግብር ከሆነ፣ ይህን የሚያደርጉበት ኃይል ክሂል ሥልጣን ከሦስት የተከፈለ ነው ማለት አይገባምና፣ ይህን በአስተዋይ ልቡና መመልከት ያሻል:: አንዳንድ ሰዎች በሚናገሩት በሦስቱ አካላት ላይ የሚገኝ ዕሪና ብቻ ነው እንጅ ሕልውናም ዋሕድና/መገናዘብም አንድነትም/ አይገኝበትም ይላሉ:: እንዲህም ማለታቸው መጻሕፍት ስለ ዕሪና እና ስለ ሕልውና ስለ ዋሕድናም የተናገሩትን ምሥጢር አስተውሎ ባለመመልከት ነው:: ዕሪና የሚነገር በአካል ላይ በሚወድቅ ምሥጢር ነው:: ሕልውናም የሚነገር በከዊን ላይ በሚነገር ምሥጢር ነው:: ዋሕድናም የሚነገር ስለ ባሕርይ ነው:: ወይም ስለ ጠባይዕ በሚነገር ምሥጢር ነው:: ስለዚህ ከዚህ በላይ ዘርዝረን ያሳየናቸውን ነገሮች ማሳሳትን የሚያመጣ ስልት ስልታቸውን ለይቶ ሳያውቁ የሃይማኖትን ነገር ማስተማር፣ መጻሕፍትንም መጻፍ ምሥጢረ ሥላሴን ያፋልሳል:: መጻሕፍትንም ያጣላል:: ሰሚንና ተመልካቹንም ገደል ይሰዳል:: ማቴ ፲፰:፲፬

ስለዚህ ጠንቅቆ ማስተዋል ይገባል:: የዚህን ነገር በሰፊው ልናስረዳ በቻልን ነበር:: ነገር ግን በብዙ ዘመን አንፈጽመውም::

ባስልዮስ ዘቂሣርያ:-

<u>ንባብ</u>፡- "ወይእዜኒ ናሕፅር ነገረ ወንፈጽም ዘንተ ክፍለ ወንኅድግ ኩሎ አእምሮ ለእግዚአብሔር ዘይመውዕ ኩሎ ግብራተ"

<u>ትርጉም</u>፡- "ነገርን በማሳጠር ይህን ምሥጢር ፍጹም ዕውቀትንም ሥራን ሁሉ፣ ድል መንሣት ለሚቻለው ለእግዚአብሔር እንተው" ብሎ እንደተነገረን /ኢ. ክፍል ፩/ ነገራችንን በማሳጠር እንወሰን::

፲፰ኛ አንቀጽ

*ምዕዳንና አኩቴት*

<u>ንባብ</u>፡- "እንከሰ የአክል ኀዳጠ ዘተናገርነ እምብዙኅ እስመ ለለባዊ ኀዳጥ የአክሎ፣ ወለዘኢኮነሰ ለባዊ ወኢያርትዐ ልቡናሁ ኀበ ነገረ ጽድቅ እመ ውኅዘ ቃለ መጻሕፍት ከመ ማየ ፈለግ፣ ወለእመኒ ዘንመ ከመ ዝንቱ ክረምት፣ ኢይከውን በኀቤሁ ከመ አሐቲ ነጥበ ጠል ወኢይርሕስ ሥርወ ልቡናሁ፤ ወኢያለመልም አዕፁቂሁ ወኢይሥርፅ ቈፅሉ:: ወእምከመ ኢለምለመ ዐፅቅ፣ ወኢሠረፀ ቈፅል ኢይትረከብ ፍሬ፤ ወለእመ አልቦ ፍሬ ምንትኑ ረባሑ ለተይህዶ"

<u>ትርጉም</u>፡- "እንግዲህስ ከብዙ በጥቂቱ የተናገርነው ቃል ይበቃል፤ ለአስተዋይ ልቦና ጥቂት ቃል ይበቃልና፤ አስተዋይ ላልሆነ እግረ-ልቦናውንም ወደ እውነት ነገር ላላቃና ሰው ግን፣ የመጻሕፍ ቃል እንደ

ወንዝ ውኀ ቢፈስ፣ እንድ ክረምት ዝናብምም በዝቶ ቢዘንም፣ በእርሱ ዘንድ እንደ አንዲት ጠብታ አይሆንም:: ልቦናውም ምሥጢር አይረዳም፤ ሕሊናውም አይመለስም፣ ሃይማኖቱ አይቀናም:: ሕሊናውም ካልተመለሰ፣ ሃይማኖቱ ካልቀና፣ ፍሬ ክብር ካልተገኘ፣ አማኒ የመባል ጥቅሙ ምንድን ነው?”

ንባብ፡- "ኦ አሐውየ ፍቁራን ንፍራህ ወንኅዝን፤ ከመ ኢይብጻሕ ላዕሌነ ቃል ነቢይ ዘይቤ ዐፀደ ወይን ኮነ ለፍቁር በብሔር ጥሉል፤ ወእምዝ ጸሕናከዎ ይፈረይ አስካለ ወፈረየ አሥዋከ"

ትርጉም፡- “የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ እንፍራ፣ አንዘንም:: ለወዳጄ የወይን ቦታ ነበረው በሰባ ኮረብታ ላይ:: ከዚህ በኋላ ፍሬ ያፈራል ብዬ ተስፋ አደረግሁ:: ነገር ግን እሾህን /መጻጻ ፍሬን/ አፈራ" ብሎ ነቢዩ የተናገረው ቃል /ኢሳ ፭:፩-፪/ በእኛ እንዳይደርስብን እንፍራ እንዘንም::

ንባብ፡- "ወዓዲ ቃለ እግዚእነ ዘይቤ ቦ ዘወድቀ ውስተ ሦከ ወበቊሎ ጠበቆ ሦከ ወሐነቆ"

ትርጉም፡- “ዳግመኛም ጌታችን በእሾህ ላይ የወደቀ ከበቀለ በኋላ እሾህ ያጫነቀው ያጣበቀውም ዘር አለ" ብሎ የተነናገረው እንዳይደርስብን:: ማቴ ፲፫:፯

ንባብ፡- "ወዓዲ ቃለ ጳውሎስ ዘይቤ እመሰ አውጽአት ሦከ ወአሜከላ ዘቅርብት ለመርገም ወደኃሪታ ለአንድዶ"

ትርጉም፡- "ዳግመኛም ምድር እሾህን አሜከላን ያበቀለች እንደሆነ፣ ለመርገም የቀረበች ናት፤ ፍጻሜዋም መቃጠል ይሆናል" ብሎ ጳውሎስ የተናገረው ቃል እንዳይደርስብን:: ዕብ ፮፥፰

ንባብ፦ "አ አኃው ንሑር በተዐቅቦ በዛ ፍኖት ሠናይት፤ እስመ ፍኖት ሠናይት ጥቀ ፀባብ ወመቅዓን ወፅዕቅት ይዕቲ፣ እንተ ትወስድ ውስተ ሕይወት:: ለእለ ይበውዕዋ በትሕትና ወበፍርሃት ወለዕለሰ ይበውዕዋ በትዕቢት ታውድቆሙ ውስተ ጸድፈ ሞት"

ትርጉም፦ "ወንድሞች ሆይ በዚች በቀናች ጎዳና በጥንቃቄ ሆነን እንሂድ፤ ይህች እጅግ ጭንቅና ጠባብ የሆች በጎ ጎዳና በፍርሃትና በትሕትና ሆነው የሚገቡባትን ሰዎች ወደ ሕይወት  የምትወስድ ናትና:: በትቢዕትና በድፍረት ሆነው የሚገቡባትን ግን ሞት ሰውን እየገደለ ወደሚጥልባት ወደ ገሃነም የምታወርድ ናትና::"

ንባብ፦ "እንከሰ ናርትዕ አእጋሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም እንተ ይእቲ አሚን፣ ከመ ፩ መለኮት በ፫ አካላት"

ትርጉም፦ "እንኪያስ እግረ ልቡናችንን ወደ ሰላም ጎዳና እናቅና፣ ይህችውም የሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ ማመን ናት::

ወእግዚአብሔር አምላከ ሰላም የሀበነ ሰላመ፤ በብሂለ ዋሕድ መለኮቱ፤

በእግረ ልቡና ንትልዋ ለአሠረ ሠናይት ፍኖቱ፤

ለበዊዕ በጽድቅ ቤተ አሐቲ መንግሥቱ፤

ዘብዙኅ ማኅደረ ክብር ወምዕራፍ ቦቱ፤

ወኬንያሁ ለሊሁ ውእቱ[97]

[97] ትርጉም –
የሰላም አምላክ እግዚአብሐር ሰላምን ይስጠን፤ አንድ ነው እያልን በማለኮቱ፤
በእግረ ልቦናችን እንከተላት ሜልካም ፍለጋ ያላት መንገዱን በ እውነት ለመግባት
ወደ አንዲቱ ቤተ መንግሥቱ፤
ብዙ መኖሪያና ክብር ሚፈያም ያለባቱ፤
ሠሪዋ የተጠበበባት እርሱ ነው ባለቤቱ፤
ማለት ነው።

ንባብ፡- "አ አኃው አንብብዋ ለዛቲ መጽሐፍ በተዓቅቦ ወበኀድዓት፣ እመኒ ኀዳጥ በንባብ፤ ብዝኀት ይእቲ በረባሕ፣ ወበቁዔት"

ትርጉም፡- "ወንድሞች ሆይ ይችን መጽሐፍ በጥንቃቄና በጸጥታ ተመልከቷት፤ በንባብ ጥቂት ብትሆን፣ ረብሕ ጥቅም በመሆን ብዙ ናትና።”

አሞንዮስና አውሳብዮስ እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑት እኛም ከአንድነቱና ከሦስትነቱ ምሥጢር ጥቂት ስለ ገለጽን፣ ለእግዚአብሔር ያቀረብነው ምስጋና:-

ንባብ፡- "አኰቴት ለእግዚአብሔር ሠዋሪ፣ ወከዳኒ፣ ነባቢ ወከሃሊ፣ ሕያው ወማሕየዊ፣ ወመዋዒ፣ ዘአንቅሐ አልባቢነ ኀበ ዝክሩ፣ ወመርሐ ልሳናቲነ ኀበ አኰቴቱ ወስብሐቲሁ፣ ንሰብሖ እንከ በእንተ ዘወሀበነ እምነ ሠናይት ኂሩቱ፤ ወናእኩቶ እንበይነ ዘፀገወነ እምዕበየ ጸጋሁ፤ ወንቀድስ ስሞ ክቡረ ድልወ በእንተ ዘከሰተ ለነ እምነ ምሥጢራተ ሃይማኖት በተዋሕዶተ ባሕርዩ ለሊሁ፤ ወትሥልስተ አካላቲሁ ወገጻቲሁ ወመልክዑ ወንሰብሖ ስባሔ ፍጹመ:: በእንተ ዘወሀበነ ቦቱ:: ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለመ ዓለም"

ትርጉም፡- "ባሕርዩን በባሕርዩ ለሚሰውር፣ በመምህራን አድሮ ምሥጢርን ለሚናገር፣ ሁሉንም ለማድረግ ለሚቻለው፣ ለራሱ ሕያው ሆኖ ሌላውን ሕያው ለሚያደርግ፣ ሕሊናትን ድል ለሚነሣ፣ ልቡናችንን እርሱን ወደማሰብ ላነቃቃ፣ አንደበታችንንም ጌትነቱን ወደማመስገን መርቶ ላደረሰን እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል:: በቸርነቱ ከሚሰጠው ከበጎው ሀብት ወገን ስለሰጠን እናመስግነው:: በለጋስነቱም ከሚያድለውም ክብር ወገን ስለሰጠን እናመስግነው:: ክቡር ስሙንም በሚገባ ምስጋና እናመስግን:: ከሃይማኖት ምሥጢር ወገን በባሕርይ አንድነቱን በአካልና በገጽ ሦስትነቱን፣ አንድ አድራጊ ሕልውናውንም ስለገለጸልን፣ ይህንም ሁሉ ስለ አደረገ፣ ፍጹም

ምስጋና እናመስግነው:: ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይግባው ለዘለዓለም አሜን::”

*www.kidusyared.org*

**መፍትሔ ቃላት**

ሁከት - ሁልጊዜ የሚከናወን የባሕር እንቅስቃሴ

ሃይማኖት አበው - የመጽሐፍ ስም፣ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፣ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ የቀድሞ ሊቃውንት ያስተማሩትን ትምህርት የያዘ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ

ሕልው ነዋሪ፣ ቋሚ

ለባዊያ= የሚያስቡ

ሕላዌ አኗኗር

ሕያዋን በማይለወጥ ሕይወት የሚኖሩ ሕይወትያላቸው

መለኮት የእግዚአብሔር የአንድነት መገለጫ እና

የግዛትና የጌትነት መጠሪያ ስሙ

መልክአ መልክ

መቅድመ ወንጌል -የመጽሐፍ ስም፣ የአራቱ ወንጌላት መቅድም፣ አሞንዮስ፣ አውሳብዮስ በሚባሉ ሊቃውንት እንደተጻፈ የሚነገርለት ስለ ጥንተ ተፈጥሮ ስለ ሰው ጠባይና በተፈጥሮው ስለተሰጠው ነጻነት በሰፊው የሚናገር

| | |
|---|---|
| መንፈስ ቅዱስ | ከሦስቱ አካላት የሦስተኛው አካል የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ስም |
| ማሕደር | ማደሪያ፣ ቤት |
| ምሥጢረ ሥላሴ | ስለ እግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረው ትምህርት |
| ምዕዳን - | ምክር |
| ሥላሴ | አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ |
| ሥልጣን | የበላይነት፣ አገዛዝ |
| ርጥበት | ውኃ ያለበት የባሕር አካል |
| ስመ አካል | የአካል ስም |
| ስመ ኩነት | የመሆን፣ የአኳኋን ስም |
| ስመ ግብር | የግብር ስም |
| ሰራጺ | የመንፈስ ቅዱስ የግብር ስም፣ ከአብ የወጣ የተገኘ |
| ሰብእ | ሰው |
| ስፍሀት | ስፋት |
| ቅሉ | ቢሆን፣ ጨምሮ፣ ከዚያም በላይ፣ ለነገሩ |
| ቅጥነተ ሕሊና | የረቀቀ አስተሳሰብ፣ ረቂቅ አእምሮ፣ ጥልቅ አስተሳሰብ፣ ምርምር፣ ርቃቄ. |

ባሕርይ ትርጉሙ ብዙ ነው እንደ ሁኔታው ይለያያል፣ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እግዚአብሔር በባሕርይው አንድ ነው።

ተረክቦ መገኘት

ተወላዲ የወልድ የግብር ስም፣ ከአብ የተወለደ

ተድኅሮ ወደ ኋላ መቅረት

ተፈልጦ መለየት

ትርጉም በግዕዝ የተጠቀሰው ንባብ ፍቺ

(በአማርኛ) ማለት ነው፤

ትስብዕት ሰው መሆን፣ የሰውነት ባሕርይ፣ ሰውነት

ትንሣኤ ዘጉባኤ ጌታችን ሁለተኛ ሲመጣ ሁሉም ሰው ተነሥቶ በአንድነት በፊቱ የሚቆምበት የትንሣኤ ጊዜ፤

ኃይለ ዘርዕ እንደ ሰው አራቱን ባሕርያት ነሥቶ ተወልዶ በየደረጃው ማደግ

ኃይለ እንስሳ እንደ ሰው መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መነሳት፣

ኃይለ ንባብ እንደ ሰው ደረጃ በደረጃ አፍ እየፈቱ አከናውኖ የመናገር ችሎታ

ኃይል ብርታት፣ ኃይል

ኃዳሪ አዳሪ፣ ኗሪ፣ በውስጥ የሚኖር

ነባብያን የሚናገሩ

| | |
|---|---|
| ንባብ | ነገር፣ የመናገር ችሎታ |
| ንባብ | በግዕዝ፣ ቃል በቃል ከአንድ መጽሐፍ የተወሰደ ጥቅስ ማለት ነው በዚህ መጽሐፍ |
| አሐቲ ጠባይዕ | የሕይወትነት ጠባይ |
| አማልእክት | አምላኮች |
| አሥረ ፍኖት | ፈለግ፣ ፍለጋ፣ የመንገድ ፈለግ ወይም ኮቴ |
| አስማት | ስሞች |
| አስራጺ | የአብ የግብር ስም፣ መንፈስ ቅዱስን የሰረጸ ወይም ያስገኘ |
| አቃኒም | አካላት |
| አብ | ከሦስቱ አካለት የአንዱ መጠሪያ ስም፤ በዚህ ስም ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አይጠሩም፤ |
| አእምሮ | ዕውቀት፣ ማስተዋል |
| አኮቴት | ምስጋና |
| አንቀጽ | መክፈያ፣ የመጽሐፍ ክፍለ ሐሳብ ተጠናቆ ሌላ ሲጀመር እንደ ንዑስ ምዕራፍ ወይም ክፍል የሚያገለግል። |
| እዝነ ልቡና | የውስጥ የአእምሮ ግንዛቤ፣ አእምሮ ላይ የተመሠረተ፣ በደንብ የሚሰማ ውሳጣዊ አካል |

| | |
|---|---|
| ከዊን | መሆን ከዊነ ልብ ልብ መሆን፣ የልብን ቦታ መያዝ፣ ወይም የአእምሮን የዕውቀትን ቦታ መተካት፣ ይህ ስም የአብ የከዊን ስሙ ነው። |
| ከዊነ ቃል | የወልድ የከዊን ስሙ ነው፣ ቃል መሆን፣ በቃልነት መገለጥ ማለት ነው፣ ወልድ ለአብም፣ ለመንፈስ ቅዱስም፣ ለራሱም ቃል ነውና |
| ከዊነ እስትንፋስ | -የመንፈስ ቅዱስ የግብር ስሙ ነው፣ ለአብና ለወልድ እስትንፋስ፣ ሕይወት ሆኖ በራሱም ሕያው ነውና. |

ከርሠ መቃብር - የመቃብር ሆድ

| | |
|---|---|
| ክሂል | ችሎታ |
| ወላዲ | የአብ የግብር ስም፣ ወልድን የወለደ በመሆኑ “ወላዲ” ይባላል “ወላጅ” ማለት ነው |
| ወልድ ስም | ከሦስቱ አካላት የሁለተኛው አካል የወልድ መጠሪያ |
| ዋሕድና | አንድነት |
| ዋዕይ | ሙቀት |
| ዕሪና | እኩልነት፣ መተካከል |
| ዝኒ ከማሁ | ይህም እንደዚያው ነው፡ ምንጩ መገኛው ከላይ ከተጠቀሰው ጋር አንድ ነው ማለት ነው፤ |

ዮሐንስ ተአቃቢ-　　　እግዚአብሔርን በአካልም በመለኮትም ሦስት ብሎ ያስተምር የነበረ ዘጠኝ መለኮት ይላል የሚባል መናፍቅ ስም ነው። ትምህርቱ በደብረ ሊባኖስ ገዳም እና በዋልድባ አካባቢ ተስፋፍቶ ነበር። አሁን ግን የጠፋ ይመስላል። ምንጩ ግን ትግራይ ነው ይባላል። ስሜን ሸዋ ነው የሚሉም አሉ።

ደብር　　　ተራራ

ገጽ　　　አካል፣ መልክ

ገጻት　　　አካላት

ፍኖት መብዕሰ　　ያልተስተካከለ ወጣ ገባ መንገድ

www .kidusyared.org

ተፈጸመ:::::::::::::::::::

ዋቢ መጻሕፍት


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት) የኢትዮጵያ ጥንታዊ ትምህርት። በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ጠባቂ በ፳ኛው ዘመነ መንግሥት ይህ መጽሐፍ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ሃይማኖተ፡ አበው፡ (1986) ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት። አዲስ አበባ።

መሐሪ (ሊቀ ሊቃውንት):: (፲፱፻፺፩) መጻሕፍተ ሠለስቱ ሐዲሳት ንባቡ ከነትርጓሜው(ከገጽ 484-486) "የጎንደሩ ሊቅ ታላቁ አለቃ ኀሩይ" ዓ.ም አዲስ አበባ ።

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ የቃል ምስክርነት 1999 ዓ.ም ኦክላንድ ካሊፎርኔያ ዩስኤ።

አድማሱ ጀንበሬ (መላከ ብርሃን) (በ፲፱፻፷፫) <u>መጽሐፈ ቅኔ</u>

(ዝክረ ሊቃውንት)። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ ።

<u>የግእዝ ቅኔያት የሥነ-ጥበብ ቅርስ ንባብና ትርጓሜው</u> (1980)

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ 1980 አዲስ አበባ።